3ኛ– የጊ ወ ክ ደርግና ቢሮክራሲው በአሁኑ የኢት ሁኔታ ያላቸው ፍሳንት የዲርጊት አገዶነት ከፍተኛ በመሆኑ ይህ ጉባኤ ያላንዳች ማወላወል በጥብቅ ያወግዛል፡፡ ይህንንም የረከሰ የደርግና የቢሮክራሲው አገዶነት ያላንዳች ርህራሄ ያጋልጠዋል፡፡ ይታገለዋልም፡፡

ስለ ዲሞክራሲ

ዛሬ በኢት ምድር ላይ የሚያካሄደው የፀረ—አብዮት ከፊያ በተራማጆች መገደልና መታሰር፣ በአድሃሪያች መጠናከር፣ የህዝባዊ ድርጅቶች መፈራረስና የዲሞክራቲክ መብቶች መታፈን ያገፀበር ታል፡፡ ይህ የፀረ—አብዮት ሃይል የጭቁኖችን ትግል ለማፋከምና ሃይሉን ለማጠናከር የተጠቀመባቸው ዘዴዎችና ሁኔታዎች አንዱና ገገበር ቀደም የሰፊው ህዝብ የመናገር፣ የነፃ እርምጃ መብቶችን አፍኖ በመያዝ ነው፡፡ በመጠኑም ቢሆን የዲሞክራሲ መብቶች አስተፃደር በጭላንጭል ይታይባቸው የነበሩ በታዎች በፀረ—ዲሞክራቲክ አስተዳደርና ድርጊቶች ተከተዋል፡፡ የጊ ወ ክ ደርግም ለሰፊው ህዝብ አቁቲ እኔ ብቻ ነኝ በሚለው ነበዝ ፈሌው ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝን በበዙሃኑ ላይ በሳበረነ በገበር የፀረ—አብዮት ሃይልን የተነኮለ ዘዴ በፊና ወነከሬ አድርጎታል፡፡

1ኛ– ይህን የፀረ—አብዮት ተንኮል ለመቋቋምና ለማጋለጥ ሰፊው ህዝብ ሃሳቡን መግለጽ፣ በነፃ እርምጃዎችና ድርጊቶች ነፃ ድርጅቶችን ማስተዳደር ስለሚያስፈልገው፣

2ኛ– በብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት ፕሮግራም የሰፈረውንና በዚህ ፕሮግራም የገባውን ቃል ኪዳን የጊ ወ ክ ደርግ በወረቀት ላይ ብቻ ሳይሆን በተግባር መግለጽ ስለሚያስፈልገው፣





3ኛ– የኢት ህዝቦች ትግል የደረሰበት ደረጃና የትግል አሳብ ሲነፃፀር የዲሞክራቲክ ጥያቄዎች አሁኑኑ መለቀቅ አይነተኛ መሣሪያዎች መሆናቸውን በማሰብ የዲሞክራሲ ጥያቄዎች አሁኑኑ እንዲለቀቁና በህግ እንዲረጋገጡ ጉባኤው ያስገነዝባል፡፡ የጊ ወ ክ ደርግንም እስከ አሁን በፈጸመው ፀረ—ዲሞክራቲክና ፀረ—አብዮት ድርጊቱ ጉባኤው በጥብቅ ያወግዘዋል፡፡

ስለ ታሰሩት ተራማጆች

ዛሬ በየቦታው በሚታሠሩ ጓዶች ላይ እንደ ወንጀል ተቆጥሮ የሚቀርብባቸው ክስ ሃቀኛና አብዮታዊ መሆናቸው ብቻ ነው፡፡ የጊ ወ ክ ደርግ እስከ አሁን የእነኙህን ሃቀኛ ተራማጆች መታሠርን ለማስተማመን የሚሰጧቸው ክሶች በሙሉ በሃሰት ላይ የተመሰረቱና መሠረተቢስ የፈጠራ ወሬ ከመሆናቸውም አልፎ እርስ በርሳቸው የማይጣጣሙ ናቸው፡፡ ይህ አይነቱ መሠረተቢስ ክስ ሊቀርብ የሚችለው በዛሬይቱ ኢት ሁኔታ ከእውነተኛ ተራማጆች ባይሆን ከፀረ—አብዮት ሃይሎችና ከተነፃፊታቸች ብቻ ነው፡፡ ድርጊቱ በመረመርና የሚሰጡት መሠረተቢስ ምክንያቶች ሲነፃፀሩ እርምጃው የፀረ—አብዮት ሃይሎችን ያስደሰተና ያጠናከረ መሆኑን ይህንንም የፀረ—አብዮት እርምጃ ሆነ ብሎ ለማጠንከር የታቀደ መሆኑ ነው፡፡ ተራማጆችን ማሰርና በየእስር ቤቱ ማሰቃየት፡—

1ኛ– የተራማጆችን ቅረል ለመስበርና ለማዳከም ከሚመኘ ደከማ አእምሮ የመነጨ በመሆኑ፣

2ኛ– በመጠናከር ላይ ላለው አድሃሪ ቢሮክራሲ ጊዜን ለመግዛት የሚያገለግል በመሆኑ፣

3ኛ– በጋንግስተሪዝም የትግል ዘዴ ተራማጆችን አስረኛ በማድረግ (ሆስቴጅ) ሌሎች ተራማጆችን በደርግ ፍሳንት ሥር ለማንበርከክ ከሚመኘ ደከማ የነውስ ከበርቴ አድሃሪነት የመነጨ በመሆኑ ይህ ጉባኤ የድርጊቱን አድሃሪነት እያጋለጠ በጽኑ ይታገለዋል፡፡ የታሰሩት ተራማጆች አሁኑኑ እንዲፈቱ ይህ ጉባኤ ያልተቆጠበ ጥሪውን ያቀርባል፡፡ በተጨማሪም የታሰሩት ተራማጆች በእስር ቤት መቆየትና ያሉበት ሁኔታ ለህይወታቸው በምንም አይነት መንገድ አስተማማኝ ሊሆን አይችልም፡፡ እንዲያውም በእስር ቤት ውስጥ የሞታሰፈው አያ ነገንዷ ደቂቃ ለህይወታቸው ጥበትና በእዛው መጠን ታበጥረቀለች፡፡ በዚህም መሠረት የተራማጆችን አሁኑኑ መፈታት ይህ ጉባኤ በድጋሚ ያስሰባል፡፡ በዚህም አንጻር የጊ ወ ክ ደርግ ተራማጆችን ለመፍታት የሚያደርገውን ጊዜ መጎተት እዝማሚያ በተራማጆች ህይወት ላይ አደጋ ማብዛት መሆኑን እንዲገነዘብና በሃላፊነት የሚጠየቅ መሆኑን እንዲያውቅ ይህ ጉባኤ ያስገነዝባል፡፡

ስለ አድርባይ ድርጅቶች

ዛሬ የኢት አብዮት እንደገና በድጋሚ የተራማጆችን ሰፈር በአዲስ ዙር እያጠራ በመሄድ ላይ ነው፡፡ ለነዋ፣ ለተደረጀና ለታወቀ ትግል በተጠበቀ የሚታገሉትን ይህ መፈክር በገበር

እንዲመነዘር በሚያፋጥና ይህንን መፈክር በአፍ እየደገፈ በድርጊት ግን በሚያወጡት መሃል ያለው ን ሰፊር ከምን ጊዜም ይበልጥ አጥር ቶታል። በዛሬው ጊዜ ሁኔታ የፀረ—አብዮት ሃይል ሃይሉን እያረጋገጠ በሚሄድበት ሰዓት የጭቁን ዱሎች በገሃዱ እየተሰረዙ በሚገኙበት ጊዜ የሰፊውን ህዝብ ትግል ዱሎች ከዚህ ወጥረት ማውጫና ወደፊትም የሚራመድበትን መንገድ መሸት ያስፈልጋል። ስለሆነም የዚህን ፀረ—አብዮት ቡራ ለመቋቋምና ህዝባዊ ዱሎችን ጠብቆ ወደፊት በማራመድ የሚ ከፈቢ ጥያቄ አስቸኳይነት አመራር የሌለው ነገበር የለም ጥያቄ ይሆናል። የነፃ፣ የተደራጀ የታጠቀ የህዝቦች ትግል በተገበር የሚመነዘረው ምንም አደራቅ በሌለው በዚሁ ባይገበቂና አብዮ ታዊ ንዓና ብቻ ይሆናል። ገና ይህ ሆና ባለ አደርበይ ድርጅቶች ወዝ፣ ማሌሬዶና ሰደድ በጊወአ ደርገና ከበርክራሲው ጋር በማበር የነፃ፣ የተደራጀና የታጠቀ ትግል እየተያወ ናቸው። ከዚህም አልፍ ለዚህ ጥያቄ በተገበር መተርጎም በየፊቅነት በሚታገሉት አገዶ መኢሶን ብሎ ሃተኛ ተራማጅ ድርጅቶችና ገለሰቦች ላይ ታላቅ የፀረ—አብዮት ቡራ አያቤፈ ናቸው። እነኒህ አደርበይ ድርጅቶች ከደርገና ከበርክራሲው ጋር በማበር ተራማጅ ድርጅቶችን ለመጨረስና ለማስጨረስ ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ ናቸው። በጥቂቱ ስራ በመስማረት በሬወሬ ወሬ ተራማጆችን በማስመታት ፀረ—አብዮት ተገበር ያከናውናሉ። እነኚህ አደርበይ ድርጅቶች የኢትን ህዝብ ትግል አፍና የያዘው የዲሞክራሲ ጥያቄ አንገብጋቢነት ሲክዱና ሲነቻሬተቱ፦

1ኛ— ስብሰራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮገራም ላይ በገልጽ የሰፈረውን፤

2ኛ— በአምስት ድርጅቶች መሃል በጥርሃ ንብሩ ላይ የተቀመጠውን ገልጽ ስምምነት በመካዱና በመ ጣስ ነው።

ይህ ፀረ—ዲሞክራቲክና ፀረ—አብዮት አርምኛ ከከሃዲ የነውስ ከበርቴ አደርበይነት የመነጨ/መሆኑን ዝብ ኤው ያለማወላወል ያምናል። በተለይ በሰፊው ህዝብ ዘገዱ ተቀባይነት ከማጣታቸው የተነሳ አዱኅቸውን ለማስረዘም ከሚመኙው ፍላጎታቸው የመጣ በመሆኑ የማይታበል ሃቅ ሆና አገኘቶታል። ከዚህም አልፍ የዲሞክራሲ ጥያቄ የሰፊው ህዝብ የትግል መሰፊያ በመሆኑ በዚህ በመባፊያው ሰፊው ህዝብ የአነሱን ፀረ—አብዮት ተገኩል አነዓይደረም ያቀዋት አይነተኛ ዘዴ መሆኑን በተጨበጭ መስከርች ተመልክቶታል። ስለሆነም እነዚህ አደርበይ ድርጅቶች፦

1ኛ— የመርሃ ገብሩን በመጣሳቸው፤

2ኛ— የብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት ላይ የሰፈረውን የዲሞክራሲን ጥያቄ ቢሉም የተደራጀና የታ ጠቀ፣ የነፃ የህዝብ ትግል በመከዓታቸው፤

3ኛ— ዛሬ በወቅላላው በሚያደርጉት የቀየማና የፕርፓከቲር ድርጊታቸውና ከፀረ—አብዮት ሃይሎች ከበርክራሲው ጋር በመሰለፋቸው ይህ ንብኤ ይህንን አዱሃሪ ድርጊታቸው አጥብቶ ያወግዛል።





## ተቋሞር ስለነበረው ህብረት

የኢት አብዮት በፈነዓበት ወቅት ሥልጣን ለመያዝ የተዘጋጀ የሠራተኛ ፖርቲ በለመኖሩ ጊወአ ደርን ከሥልጣን ኮርቻ ላይ መፈናጠጡንና በአሰሩት 3 ዓመታት ውስጥም ተራማጅ ድርጊቶችን እን ደዚሁም ፀረ—ህዝብ ድርጊቶች ያከሄደ መሆኑን ድርጅቶቻችን በወበቅት በአሰሩት የሁለት ዓመታት የፖለቲካ ወበኔ አስቤተዋል። ይሁን እንጂ ተራማጅ ተገበሮችን ስንደገፍ ሰምን እንደሆነም በልገባዊ ምርምርና ጥናት ምርኩዜ እንደነበረም ደጋገመን ገልጸናል። የቀራኒያች ህጋጋትም ከህዜ ወደ ጊዜ እንደሚለዋወጡ ሁሉ በስልጣን ላይ ያለውን ጊወአ ደርን የህዝቡም ቅራኔ ሊታወ የሚገበው በአዛው በሰነበዊ ትንተና ረገዱ ስለሆነ በተጨበጭ ሁኔታ ላይ ይህንን ሁኔታ በነመሬምረው ደርጉ ከህዝብ በመቀረረብ ፈንታ ወደ መሬሬቅ ሆኗል። ከዚህም አልፍ ሃቀኛ ያልሆነ በወዝአደሩ ስም የሚሀሰቅ አወናበጅ ፖርቲ ወደማቷቷም አቅራቢያ መሆኑን በምናያቸው ሁነሞች አይተናል። በዚህም ዝንጅት የአብዮቱን ሂደት በመመርኮዝና የተራማጆችን ብቅ ብቅ ማለት በማየት ከአሁን በፊት በመኢሶን አማካኝነት ህብረት ፈጥረው የነበሩትን ድርጅቶች በህብረት ደረጃ ደገፈናቸው ነበር። ዓፉ ግን ከቅቲት ጊዜያት ጃምሮ በሚያከሄዱት የፖለቲካ ቅስቀሳ ላይ ከከሰኛ ያልሆነ አይዲዮሎጂ ቢያስፈሩ በማየታችን ከበዱ ቅሬታ ላይ ጥለውናል። የሚያራምትትንም የቀኝ አዓፊነት ተገበር አንዱ ማሊ ድርጅት ሊያራምዱ የሚገበው እንዓልሆነ በጥብቅ እያስጠነቀቅን በተለይም እነኚሁን ድርጅቶችንም ምክንያት በማድረግ የገል ጥቃቶውን የሚያራምትትን የቀኝ አዱሃሪያች በጥብቅ እናወግዛለን። በተጨማሪም ይህንን ህብረት ተገን በማድረግ የመንገሥትን አውታር ተገን በማድረግ የራሱን ጥቅም የሚያስከብር ሃይል በማዘጋጀት ላይ ባለው አንደኛው ሃይል ልናደርግ የምንወደው በአሁኑ ተጨበጭ ሁኔታ ማውገዝ እንጂ ሂስ እንዓልሆነ እንሊታወቅ እንወዓለን። ዲሞክራሲን በሚመለከተው በኩል እነኙሁ ከላይ የተጠቀሱት ድርጅቶች ዝብ ተውት የነበረውን ቃል ስሳጠሩ በዲሞክራሲ ላይ የወሰዱትን አቋም እናወግዛለን። አሁንም ቢሆን የሃቀኛ ተራማጆች ህብረት ለኢት አብዮት አስከል ከመሆኑ ሌላ ወደፊት ለሚመሰረተው ሃቀኛ የወዝ አደር ፖርቲ ሸንስ እንደመሆኑ መጠን አሁንም ህብረቱ በሃቀኛ ተራማጆች እንዲመሠረት አብዮታዊ ጥሪያችንን እያቀረብን ህብረቱንም ተገን በማድረግ በሃቀኛው ድርጅት መኢሶን ላይ የሚደረገው የስም ማጥፋት ዘመቻም ሆነ አበሉች ወይም ደጋፊያች ናቸው ብለው በሚጠረጠፉት ላይ የሚደረገው ዘመቻ እንዲቆም በጥብቅ እንጠይቃለን።

United Progressive Ethiopian
UPESUNA
Students Union in North America
EXECUTIVE COMMITTEE
BOX 11218 BALTIMORE, MD. 21239

Ethiopian Women's Democratic Union
in Europe

THE ETHIOPIAN STUDENTS UNION IN EUROPE

## ለ ሠ ራ ዊ ቱ ጥ ሪ

ጭቁን የኢት. መለዮ ለባሽ የጭቁኑ ሰፊ ህዝብ አካል ነው። ራሱ መለዮ ለባሹ ጭቁን እንደ መሆኑ መጠን የበዝባዡ ሥርዐት አገልጋዮች በየካቲት 66 በተለይ ከ1ኛ እስከ4ኛ ክፍለ ጦር ከተሰለፉት የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር በመሰለፍ በየካቲቱ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ትልቅ ሚና እንደተጫወተ የሚታወቅ ሀቅ ነው። ከጊዜ ወደ ጊዜ አብዮቱ እየገፋ በሄደበት ወቅት ጭቁኑ መለዮ ለባሽ ከአብዮቱ ሂደት ጋር በመራመድ በየጊዜው አብዮቱን ለማፋፋም ከተነሱት ፀረ-አብዮት የውስጥና የውጭ ኃይሎች ጋር በአብዮቱ በረር ከጭቁን አርሶ አደሮች፣ ወዝ-አደሮችና እንዲሁም ከሌሎች የአብዮቱ ወገኖች ጋር በመሆን አብዮቱንና አብዮታዊት የኢት. ህልውና ለማዳን ያለማቋረጥ በቦታው ደሙን አፍሷል። ዛሬም እያፈሰሰ ነው። ይህንንም ትግሉን እንደሚቀጥል እንጠራጠርም። በተለይም አብዮቱን ከውስጥ ሆኖ ለመቦርቦር ተርዐው ተነስተው በነበሩት አገልጋይ ህብረተሰብ እንዲሁም በተፈፀ ባንቲ፣ ከለማየሁ ኃይሌ እዷሃፊ በዶኖች የተወሰደውን አብዮታዊ እርምጃ በመደገፍ ለአብዮቱ ያለውን ተቆርቋሪነት አሳይቷል። ዛሬ የአብዮታዊት እናት አገሩን ዳር ድንበር ለማስጠበቅ ብሔራዊ ክብሯን ሳያስደፍር በተለይም በብዙ ትግልና መስዋእትነት እዚህ ደረጃ ላይ የደረሰው አብዮት እንዳይቀለበስ በታላቅ ቆራጥነት ያደረገውና የሚያደርገው ተጋድሎ በኢት. ጭቁን ህዝቦች የትግል ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው ነው። ሠራዊት ይህንን ተጋድሎውን እንደሚቀጥል በለመቆረጥ በእለት ከእለት ትግሉ ከኢት. ጭቁን ህዝቦች ጋር ተሰልፎ በይበልጥ ትግሉን እንደሚያፋፍም ከዚህ የሚከተሉትን ጥሪ እናቀርባለን።

1ኛ- ዛሬ ሰፊው ህዝብና ሃቀኛ ተራማጆች ከዳር እስከ ዳር አብዮቱን ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ለማሸጋገር የብሔራዊ ዲሞክራሲ አብዮት ፕሮግራም በሥራ ላይ እንዲውል የሚያካሂዱት ትግል ግቡን እንዲመታ ሠራዊቱ ከሰፊው ህዝብና ከሃቀኛ ተራማጆች ጋር በዚህ ወሳኝና አንገብጋቢ ጥያቄ ላይ አብሮ የመሰለፍ ሃላፊነቱን ተረድቶ ትግሉን እንዲያፋፍም።—

2ኛ- አብዮቱ ከሚገኝበት ውጥረት ለመውጣት፣ የሰፊውን ህዝብ ነፃነት፣ ዲሞክራሲና ትቀቅ በተሟላ አኳኋን ለማረጋገጥ፣ እንዲሁም አብዮቱ በአሁኑ ወቅት ካሉበት ችግሮች መፍትሄ ለመስጠት፣ በዚህም አገር ለመፀየት፣ ለመበበስና አብዮቱ በሰፊ መሠረት የሆነው ሰፊ የኢት. ጭቁን ህዝብ የዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ አሁኑኑ እንዲሰጡ ይጠይቃል። ይህ ጥያቄ የኢት. ጭቁን ህዝቦች አንዱ አካል የሆነው የጭቁን ሠራዊትም ጥያቄ በመሆኑ ጭቁን መለዮ ለባሽ ዛሬ ዲሞክራሲ ለጭቁኖች ያለገደብ አሁኑኑ እንዲሰጥ የሚደረገውን ትግል በይበልጥ እንዲያፋፍም።—





3ኛ- ከዉሃሬው በርከሬቢና ሌሎች ፀረ-አብዮት ሃይሎች በአንድ ወገን የሰፊው ህዝብ በሌላ ወገን በመሆን ለሚደረገው አብዮታዊ ትግል ሠራዊቱ በሰፊው ህዝብና በተራማጆች ላይ በሚደረገው ፀረ-አብዮት ሴራ ነቅቶ እንዲጠባበቅና እቅዱም እንዳይነሳ ማገቢያም እንደ ሌለበት ከጭቁኖችና ከተራማጆች ጋር አብሮ በመሰለፍ ይህንን ፀረ-አብዮታዊ ሴራ እንዲያደም።—

4ኛ- በአብዮቱ ሠፈር የሚገኙ ከበርከሬቢው ወገን የህዝብ ወገንን መሪዎችና አብዮቱን በማንም መንገድ ከቀልበሳ ለማዳን የሚታገሉት ሃቀኛ ተራማጆችን ማሰደድ፣ ማሠርና መግደል እንዲቆም ሠራዊቱ ከህዝብ ወገኖች ጋር በመሆን በቆራጥነት እርምጃው እንዲቆምና የታሠሩት ሃቀኛ ተራማጆች በአስቸኳይ እንዲፈቱ የሚደረገው ትግል በይበልጥ እንዲፈፅም።—

5ኛ- ''ህዝባዊ ሠራዊት'' የገባውን ቃል:—

"እኛ የህብረተሰባዊት ኢትዮጵያ መለዮ ለባሾችና የሕዝባዊ ሠራዊት አባሎች:—

"የኢትን ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም በተግባር እንዲተረጎምና እስከ መጨረሻው የደም ጠብታ ለመታገል ቆርጠን መነሣታችንን በአንድ ድምፅ አብዮታዊ ቃል ኪዳን እንገባለን።

"የአገራችንን ክብርና ነፃነት የጭቁን ህዝቦቻችን መብት፣ አብዮቱ ያስገኘላቸውን ድሎችና አዲስ ህብረተሰብ ለመመስረት የሚያደርጉትን ትግል ለመደገፍና ከግቡ ለማድረስ የተጣለብንን ወታደራዊ፣ ፖለቲካና በህላዊ እውቀት ሥራ ላይ ለማዋል በአንድ ድምፅ አብዮታዊ ቃል ኪዳን እንገባለን" ወዘተ የሚለው በተግባር እንዲተረጎም ጥሪ እናቀርባለን።

United Progressive Ethiopian
UPESUNA
Students Union in North America
EXECUTIVE COMMITTEE
BOX 11218 BALTIMORE, MD. 21239

Ethiopian Women's Democratic Union
in Europe

THE ETHIOPIAN STUDENT'S UNION IN EUROPE

## ስሎ ኢ ክ ወ ን

ኢሰወን ገቶና ዘሬ ወጣትን ኃይል በአብዮት በፈር እንዲሰባሬ ለማድረግ ከሚተረት ገሥበር የደም የወጣት ድርጅቶች ውስጥ እንዱ ነው፡፡ ይህ ድርጅት የኢትዮጵያ አብዮት አቀጣጠን በይበት በማይዘበው የነፃነት ጉዳና ላይ ተዝዞ የመጠረሽ ዱላን እንዲተዳቹ ላሰሩት ቦሰት አመታት በሰማይረዋና መታከት የታገለ አብዮታዊ ድርጅት ነው፡፡ ለዚህም፡—

1ኛ— በልባት በአብዮት ፋና አማከኝነት በየጊዜው ያስተጋበቸው ቀስተበያችና ፕሮፖጋንዳዎች

2ኛ— ወጣትን በዙሪያውና በአብዮት በፈር ለመሰብሰብ ያደረገው ያልታከተ ተረትና ያገኘው ውጤት በቂ ማረጋገጫዎች ናቸው፡፡

በሰፈት አመታት ማለት ወጣቱ በሙሉ እንደአብዮታዊ ተየቀር በሚታይበት ጊዜ ኢሰወን ይህ የተ ሳሳተ አስተያየት ትክክለኛና መደበኛ ይዘት እንዲኖረው ያደረገው ትግልና አስተዋጽኦ የማይዘ ነጋና ፍጹም ሀያውነት ያለው ነው፡፡ ይህ ወዥገበር በወቅላላው ህበረተሰብ ውስጥ በተለይም በሬቡ በወጣቱ ውስጥ ስር የሰደደና አዱሃሪያችና በተለይም ለኢህአፖ አመቺ ሁኔታ ፈጥሮ በነበረ በት በዓት ይህንን የተሳሳተ አስተያየት ለመሰበርና ትክክለኛ አብዮታዊ ይዘት እንዲኖረው ለማ ድረግ ያደረገውን ጥረት ንብረው በአድናቆት ይመለከተዋል፡፡

ትሳነት በኢህአፖ ቀጥጥር ስር የነበረውን ወጣት ዘሬ ወደ አብዮት በፈር ሊቀሳቀል የቻለውም ከዚህ ፅኑ የርእቀተሰም ትግል በኋላ መሆኑን ይህ ንብኢ ያለ እንዳች ማወላወል ያምናል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ይህ ንብኢ የኢሰወንን ፕሮግራም በሚገባ ከመረመረና ከተወያየበት በኋላ ፕሮግራሙ ፍጹም አብዮታዊ፣ የኢትን አብዮታዊ ወጣት የደረሰበትና ከዚም አልፍ ኢሰወን ላሰፈት በሰት አመታት ያስተጋበውን የፖለቲካ መስመር የሚያንፀባርቅ ሆኖ አገኘቶታል፡፡ በተለይም ይህ የወጣት ድርጅት የመኢሶን ወጣት ክንፍ በመሆኑ ንብኢው ለዚህ አብዮታዊ ድርጅት የሚሰጠውን አብዮታዊ ድጋፍ ልቀ ክበደት እንዲይዝ አድርጎታል፡፡

መኢሶን በኢት አብዮት ውስጥ ትልቅ አብዮታዊ ሚና የተጫወተና አብዮታዊነትም በመከራም ሆነ በሰላም ጊዜ አያረጋገጠ በመጊዜ ላይ ያለ እንጋፉ የማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅት መሆኑን ንብኢው ያምናል፡፡ ስለሆነም ዘሬ ንብኢው የመኢሶን ወጣት ክንፍ ከመኢሶን ፖለቲካና የትግል ውጤት ለይቶ የማያየው በመሆኑ ይህ ንብኢ ለዚህ የወጣት ገቶና የሚሰጠውን ድጋፍ ፍጹም አስተማማኝ አድርጎታል፡፡ ንብኢው የኢትን ጭቁኖች ትግል በመደገፍ ፀረ—ቢሰት የሆነ የፖለቲካ መስመሩን ቀይስ ከተነሳበት ጊዜ ጀምሮ የኢት ጭቁኖችን ትግል አቀመ የፈቀ





ዘለቶን ያህል ለማገልገል ተረቀል፡፡ እንኚህን ፀረ—ህዝብ ኃይሎች ከሚያጋከሙና በተፈቀ አብዮታዊነት ከሚታገሉት ኃይሎች ጋር በሙሉ በየጊዜው የትግል አንድነትን አበጀተቀል፡፡ ወደፊትም ያበያል፡፡ ንብኢው ለኢሰወን የሚሰጠውን ሙሉ ድጋፍ ከዚህ አብዮታዊ ክያም ቀመነጩ ለወደፊትም ተፈማጆች በኢሰወን ማህል ለሚደረግ የትግል ክበር ትልቅ በር ከፋች መሆኑን ያምናል፡፡

## ፖ ፊ ሰ ፀ ደ ት

ጭቁና ብዝበዛ በሰፈነበት ስርአት ውስጥ ለፍትህ፣ ለነፃነትና ለእኩልነት ጭቁኖች በሚያ ደርጉት ትግል የወጣት ትውልድ ታሪካዊ ሚና ይኖረቀል፡፡ በጭቁኖች ህዝቦች ላይ የተዘረ ጋውን ኢምፔሪያሊዝም በመቃወምና የጭቁኖችን ብሶት በማስተጋባት በተለያዩ ጊዜያት ወጣት ትውልድ በግንባር ቀደምትነት ይታገላል፡፡

ኢት ወጣቶች ለረጅም ገዜያት በኢት ጭቁን ህዝቦች ላይ በፍኖ የኖረውን የሃይለስላሴ የፊውዳ ሬሽስታዊ አገዛዝ በመታገል በኢት ጭቁን ህዝቦች ላይ የነፃነት ትግል ታሪክ ውስጥ በግንባር ቀደምትነት ሲታገሉ እንደየቁ አመን ነው፡፡ በተለይም የተማሪው ገቶና በፀረ—ፊውዳል በ ፀረ—ኢምፔሪያሊስት የትግል መድረክ ከተጠበት ጊዜ ጀምሮ ከእንዝዚህ የኢት ሰፊ ህዝብ ጭቁ ወሳቶች ጋር በከፊት መሪራ ትግል መሰዋእትነት የተሳበት ከፍተኛ ዝናን ያተረፈው በአገር ቤትና በውጭ ያለው የተማሪያች ገቶና እንደሆነ ማንም የማይክደው ሃቅ ነው፡፡ በተለይም ለየካቲት 66 አብዮታዊ ገቶና ከፍተኛ አስተዋጽኦ ከማድረጉም በላይ አብዮቱ ከፈነዳበት ጀምሮ የወጣቶች ገቶና ተፈማጅ ክንፍ የረጅም ጊዜ የተማሪው ገቶና መርህ ተማሪና መሁር ከገበሬውና ከሰራተኛው ጋር ተዋህዶ፣ ከእነሱን ተግር መልሰህም አስተምሬቸው፣ አብረህ በመሰለፍም አቢቢቷን ኢት መምርት በተግባር ለመተርጎም አጋጣሚ ሁኔታን የፈጠረው የእድገት በህብረት ዘመቻ ጭቁን አርሶ አደሮች፣ ወዝአደሮችና ሌሎችም የአብዮት ኃይሎችም በማነቃቃት፣ በማደራጀትና በማስታጠቅ ከኢት ጭቁን ህዝቦች ጎን ተሰልፍ በከፍተኛ መስዋእትነት ታገለቀል፡፡ በተለይም የህዝቡን ወገን የመረጡ ተፈማጅ ወጣቶች ፀረ—አብዮት ኃይሎችን በመታገል ትምህርት ቤቶችንና የህዝብ ድርጅቶችን በአድሃሪያች ለማጽዳት ከፍተኛ አብዮታዊ ሚና እንደተጫወቱ እንደሚጠወቱ ማንም ሊክደው የማይችል ሃቅ ነው፡፡

— በአሁኑ ወቅት ተፈማጅ ወጣቶች ከጭቁኖች ጎን ተሰልፈው ዘሬ በመከናዉ ላይ የሚገኘው የነፃ፣ የተደራጀና የታጠቀ ትግል ትክክለኛ ፈፋን ባይለቅ ከግቡ እንዲደርስ የሚያደርጉትን ትግል ከመቸውም ጊዜ በበለጠ እንዲያፋፍሙ፡—

- ደርግና የተኝ አደርበቶች በአጊሎ ፕሮግራም ላይ የሰፈረውን አሳማ በመከዓት ዘሬ የሚያከሄዱ ትን ፀረ—አብዮት ቢፊ ከበረው ህዝብና ከተፈማጆች ጎን በመሰለፍ አብዮትን ከቀልበሰ ለማዳን

በሚደረገው ትግል ውስጥ በታሪክ ፊት ከፍተኛ ኃላፊነት እንዳለባቸው ተገንዝበው ትግሉን እንዲያፋፍሙ፡—

— ዛሬ ደርግ በተራማጅ ወገኖች ላይ የሚያካሂደውን ጭፍጨፋ እያወገዝን ተራማጅ ወገኖች አብዮቱ ከቀልበሳ ለማዳንና ወደፊት ለማራመድ የዴሞክራሲ መብቶች ያለገደብ ለጭቁኖች አሁኑኑ የታሰሩት የጭቁን ህዝብ ወገኖች በአስቸኳይ እንዲፈቱና በሃገሪቱ ተራማጆች ላይ የሚደረገው አሰቃቂ ቶርቸር ጭፍጨፋ በአስቸኳይ እንዲቆም፤ አድሃሪው ቢሮክራሲ እንዲደመሰስ፤ ደርግና የቀኝ አድርባዮችን ለማጋለጥ የሚያካሂዱትን ትግል ከመቸውም ጊዜ የበለጠ እንዲያፋፍሙ አብዮታዊ ጥሪ እናደርጋለን፡፡

የአብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም በሥራ ይተግበር!!

ዴሞክራሲ ለጭቁኖች ያለገደብ አሁኑኑ!!

የታሰሩት ሃቀኛ ተራማጆች በአስቸኳይ ይፈቱ!!

የሃቀኛ ጓዶች ገዳዮች ለፍርድ ይቅረቡ!!

ሶሊሰን ይለመልማል!!

ሰፊው ህዝብ ያሸንፋል!!!

United Progressive Ethiopian
UPESUNA
Students Union in North America
EXECUTIVE COMMITTEE
BOX 11218 BALTIMORE, MD. 21239

Ethiopian Women's Democratic Union
in Europe

THE ETHIOPIAN STUDENT'S UNION
IN EUROPE



31—3—78

ከ22/3/78 — 25/3/78 በችኮዝላቫኪያ ተሰብስቦ የነበረው 7ኛው የምሥራቅ አውሮፖ የኢት ተማሪዎች ሪጂናል ሰሚናር ያስተላለፈው የፖለቲካ ውሳኔ፡፡

ህሊያዊ የዓለም አቀፍ ሁኔታ

ህዝቦች ለዲሞክራሲ፣ ለብሄራዊ ነፃነታቸውና ለሶሻሊዝም የሚያደርጉት ትግል እየተፋፋመ በሄደ ቁጥር የነፃነትና የዲሞክራሲ ጠላቶች ሁሉ፣ዘዴና ጠባያቸውን በመቀያየር የተቀጣጠለውን የነፃነት ችቦዎችን ለማዳፈን የሚያደርጉት ፕሮፖጋንዳና የሚፈጽሟቸው ተንኮሎች በየጊዜው በይዘታቸውና በመልካቸው እንደሚቀያየሩ የጊዜው የዓለም ተጨባጭ ሁኔታዎች ምስክሮች ናቸው፡፡ በዓለም ላይ በሚወድቀውና የወደፊት የመኖር ተበሩው በተገፈፈው ኢምፔሪያሊዝምና፣ ለብሔራዊ ነፃነታቸው በሚታገሉ አገሮች፣ በካፒታሊስት ሀገሮች ባሉ ወዝአደሮችና ከበርቴዎች መሃል የሚደረጉት ትግሎች ያለማቋረጥ ይገሰገሳሉ፡፡ በአንድ ቦታ ለጊዜው የጭቁን ህዝቦች ትግል ቢዳፈንና በሌላ ቦታ ዱል በመታም የኢምፔሪያሊዝም የወረራና የጦርነት ኃይል በየጊዜው እየቀነሰና እየተዳከመ ቢሄድም ኢምፔሪያሊዝም ዘረም ቢሆን የማይናቅ የጭቁን ህዝቦች ጠላት በመሆኑ በሚገኙ ህሊያዊ ድሎች ተራማጅ ኃይሎች ሊዘናጉ አይገባም፡፡

ሌኒን "የኢምፔሪያሊዝም የሰላም ጊዜ አንዱን፣ጦርነትን ሲያዘጋጅ፣ከጦርነት ደግሞ ሌላው የሰላም ጊዜ ይወለዳል" እንዳለው ሰላምና ጦርነት ሁለቱም የኢምፔሪያሊዝም ከተፈጥሮው የበቀሉ የወረራ ጠባዩ በመሆናቸው ኢምፔሪያሊዝም ከዓለም ገጽ ጠቅልሎ እስከወደመ ድረስ ተራማጆችን የዲሞክራሲና የሶሻሊዝምን ኃይሎች ሁሉ በአጠቃላይ እያስተባበረን ዓለም የሰላም መዲና እንድትሆን የጋራ ግንባር በመፍጠር ትግላችንን ማፋፋም አለብን፡፡ ኢምፔሪያሊዝም በተለይም የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም እንደሰነበለት በተያያዘው መላው ዓለም አቀፋዊ የአብዮት ቀለበስ ሴራው በመካከለኛው ምሥራቅ በሰባት መሣሪያነት፣ በአፍሪቃ ቀንድ በኑሜሪና በባሬ ወኪልነት፣ በደቡብ አሜሪካ በፒኖቸት የፋሺስት መንግሥት አማካይነት፣ በደፋር፣ በናቢያ፣ በደቡብ ኮሪያ፣ በታይላንድ ዲክታተሮችና ፀረ—ህዝብ ኃይሎች መሣሪያነት የህዝቦችን ነፃነትና ሰብአዊ መብት እየገፈፈና ህዝባዊ ጭፍጨፋንም እያካሄደ፣ በደቡብ አፍሪቃ ገናና ነጭ ያለውን የጥቂት ነጮችንም የዘረኞች አገዛዝና በተለይም በዝንባዊ ያለውን የኢያን ስሚዝ መንግሥት በፖለቲካና በኢኮኖሚ በጦር አቅፎና ደግፎ የኖረው ኢምፔሪያሊዝም ታክቲኩን በመቀየር በቀኝ እጁ የህዝቦችን ደም እየመጠጠ በግራው ደግሞ ይህን የጥቂቶችን ጋንጭ ሊያዳፍኑ የሚታገሉትን የሰዎችንና የዘኑ የጀግኖች ግንባር ኃይል ለመከፋፈልና ለማጥፋት ከልሆነም ራሱ የሚጠቀሙ ያሸነጉሊት መንግሥት ለማቋቋም "የኤዌን የኪስንጀር" "ፕላን እየተበጀና እየተቀበ በመቅረብ የዓለምን ህዝብ በተርቡም ጥቆር አፍሪቃን በዘረኛነትና በነፃነት መሀል ሄዘ እያታለለ ለመግዛት የሚያደርጠ

ነገሩ ግን አሁንም እንደተዘረጋ ነው::

የፓለስቲናውያንም ህዝቦች ትግል ለማውደም በገብጽና በእስራኤል መሀል መሳው የመካከለኛውን ምሥራቅን ችግር ሊፈታ የማይችል አንዱ ዐገናዊ ስምምነት ለማድረግ ቀምር ስሳል ተባከላት የፓ ሊስቲናውያን ህዝቦች ከመሬት ገጽ ለማጥፋት የእሥራኤልን የጦር ኃይል በደቡብ ሊባኖስ በሉት መጠለያና መከላከያ በሌላቸው ህፃናት፣ አሮጊቶችና ሽማግሌዎች ሳይ የቦንብና የርኩት ናዓ እየ ወረደባቸው ነው:: ቀይ ባህርንም ''የአረብ ሐይቅ''በተሰኘ መርሆ ስር የጦር ቃል ኪዳን ስምምነት በአካባቢው አድሐሪያች መሀል እንዲደረግና በአብዮታዊት ኢትዮጵያም ሳይ እንዲዘመት የሚያስፈልገውን ዝግጅት በማጠናቀቅ ሳይ ነው:: ምናልባትም ይህን ፕላን የኢት ህዝቦች ትግል ኢስከል ተጠነገሬ ድረስ በሥራ ሳይ ለማዋል እንደሚሞከር ጥርጥር የለውም::

የፈረንሳይ ኢምፔሪያሊዝም ከምእራብ አፍሪቃ በሰሐራ ዲሞክራቲክ ሪፓብሊክ ህዝቦች ሳይ የሞሮ ኮና የሞሪታንያ አድሐሪ የገዥ መደቦች በፈጸሙት የወረራም ተግባር በቀጥታ ተካፋይ ሆኗል:: ስለሆነም ይህ ሰበሰብ ዓለም በሁለት ተፃራሪ ጎራዎች በተከፈለችበትና ለዲሞክራሲና ለሶሻሊዝም የሚደረጉት ትንቅንቆች በተጋጋሉበት ሰዓት የአድሐሪያን የጋራ ግንባር ሊሰበር የሚችለው በተራ ማጆች የጋራ ግንባር በመሆኑ፣ በዚህ የጋራ ግንባር ውስጥ ተራማጆች ሁሉ እንዲሰለፉ ጥሪ ያደ ርጋል:: ከናሚቢያ፣ ከዚንባቤ፣ ከፓሊስታይን፣ ከደፋር፣ ከዲሞክራቲክ ሰሐራ፣ ከኢስት ቲሞር ከሱዳን፣ ከግብጽ፣ ከሶማሊና ጭቁንና ብዝበዛን በአጠቃላይ ከሚታገሉ ኃይሎች ጋራም ያለውን የትግል አንድነት መልስ ያረጋግጣል:: ኢምፔሪያሊዝም እንዲወድም፣በዓለም ፍትህ፣ እኩልነት ነፃነት፣ ዲሞክራሲና ሶሻሊዝም እንዲነገስ የሚቻለውን ድርሻ ለማበርከትም የሚያስችሉትን ተግ ባራት ሁሉ ይፈጽማል::

## የ ኢ ት ዮ ጵ ያ ጊ ዜ ያ ዊ ሁ ኔ ታ

ኢትዮጵያ ሐገራችን ሳይ የሚካሄደው አብዮታዊ እንቅስቃሴ በቀጥታና በተዘዋዋሪ የዓለም ኢምፔሪ ያሊዝምንና በአጠቃላይም አድሃሪ ኃይሎችን ሲጉዳ ቢያዳክም በሌላው አንፃር ደግሞ የአብዮታዊ እንቅስቃሴዎችን ሐደት በመልኩና በይዘቱ እንደሚያሰፋና እንደሚያበለጽግ ከዚያም በላይ እንደ ኪዩባ፣ እንደቬትናም፣ እንደካምቦዲያና እንደላኦስ አብዮቶች ሁሉ ምሳሌና አርአያ በመሆን ለዓ ለም፣ ቀረብም ቢል ለአፍሪቃ፣ተገቢውን ድርሻ እንደሚያበረክት ጥርጥር የለውም::

የኢምፔሪያሊዝምና የአካባቢው አድሐሪ የአረብና የአፍሪቃ ገዥ መደቦች የዚህ አብዮት መፈንዳትና ገቡንም መምታት ያለቀጥ ስለአስቦጋቸው በየጊዜው አብዮቱን በኢህአፓ፣ በኢዲዩ፣ በኤርትራም ተገንጣይ አድሐሪ ቡድኖችና በቢሮክራሲው አማካይነት ለመቀልበስና በለጋነቱ ለማነቅ የፈጸሟቸው ሴራዎች እንዲጨናገፉ በየ ጊዜ በደቡብ ምሥራቅና በምሥራቅ በሰሜን ኢትዮጵያ የሶማሊያን የረጅም





ሁኔ የመሰረቱት አሳማ ''ታላቋ ሶማሊ''በሚል መርህ ስር በመንተራሰና በዚህም አካባቢ ያለ ውን የብሔረሰቦች ችግር በማስታከክ የሰሜኑን የተገንጣዮችና የደቡብና የደቡብ ምሥራቅን የ ጦር ፕላን ሚዛን በከርቱም ካገናዘበ በኋላ አብዮታዊት ኢትን አስወረረ:: በቢሮክራሲው አሻጥርና የብሔረሰቦችም ችግር በዲሞክራቲክ መንገድ ባለመፈታቱ ጊዜያዊ ድሎችን እንዲጎናፀፉ መልካም አጋጣሚ ሆናቸው:: ይህም የኢትን ሰፊ ህዝብ ከማስቆጣቱም በላይ ሰፊው ህዝብ በዚህ የተወጣ ተን አብዮቱንና ብሔራዊ ነፃነቱን ለመጠበቅ ሚሊሺያልና በጉልበቱ ታላቅ መስዋእትነት በማድረግ አኩሪና የማይረሳ ድሎችን ተጎናጽፏል:: ምንም እንኳን እነዚህ የተገኙት ድሎች የ መጀመሪያው እንጂ የመጨረሻ ባይሆኑም ከአለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝምና ከቡችሎቹ ጋር የሚደረገ ውም ትግል መራራ ቢሆንም ይህ ድል የተገኘው ከወዝ አደር፣ ከገበሬና ከመሳውም ዲሞክራቲክ ኃይሎች በተውጣጡ ህዝባዊ ጦርና መደበኛ ሰራዊት በመሆኑ ወደፊት ለምንመሠረተው ዲሞክራቲክ ኢት የትግል ጉዳና ሳይ በሚደረገው ኅሥጋቢ ለአብዮቱ የማይናቅ የትግል ስሜት ቀስቀሳ አድር ጓል::

በሰሜን ኢትም ይህንኑ የመሰለ ሁኔታ የያዘ ከመሆኑም በላይ ከላይ በተጠቀሰው የብሔሮች ችግር ያለመፈታትና በአካባቢውም የጦርና የስትራተጂ ሁኔታዎች ምቹነት ሰበብ ሌላ የአብዮቱ አስጊ ነጥብ በመሆን አብዮቱን ለመቀልበስ ከሚያሰጉት አስጊ ቦታዎች አንዱ ሆኗል::

በመሀል ሀገርም በቢሮክራሲው፣ ኢዲዩ፣ ኢህአፓና አድሐሪ ኃይሎች በፈጠሩት አሻጥር ብዙዎች ተራማጆች በእስር ቤት ሲማቀቁ፣ ከዚህም በላይ የገድያ ዘመቻ እያየለ ብዙ ታጋዮች በአድሃ ሪያን እጅ ከመውደቃቸውም በላይ አብዮቱን ለማፈን ከዳር ካሉት ሁኔታዎች ጋር በመሆን የራ ሱን ሚና እየተጫወተ ነው::

ኢምፔሪያሊስት ኃይሎች በቀይ ባህር አካባቢ ካላቸው የኢኮኖሚና የፖለቲካ ጥቅም የተነሳ በአካ ባቢው ሰላም እንዲደፈርስና ብሎም የሚገቡበት ቀዳዳ እንዲሰሩ በጣም እየጣሩ ናቸው:: ይህም ፍላጎታቸው በሚገባ እንዲረጋገጥና ሥራ ሳይ እንዲውል ባካባቢው የጦር ደጀናቸውን ለማጠናከር እየታገሉ ናቸው:: ስለሆነም ይህን ተንኰል ያካባቢው ጭቁን ህዝቦች ነቅተው እንዲጠብቁና እንዲከላከሉ ይህ ጉባኤ በጥብቅ ያሳስባል::

## በዚህ የፖለቲካ መነኔ ታበቃ የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ወዳጆች ተብለው የሚጠቀሱ መደቦች::

### ሀ— አርሶ አደር

የኢት የኢኮኖሚ መሠረት እርሻ በመሆኑና 90 በመቶ የሚሆነው የሀገሪቱ ህዝብ የሚኖረውና የሚተዳደረው በእርሻ ነው:: ከየካቲቱ የመሬት አዋጅ በፊት ከእርሻ ከሚገኘው ምርት ተጠቃሚው 90 በመቶ የሚሆነው ሰፊው የኢት ገበሬ ሳይሆን ጥቂት የመሬት ባለቤቶችና ከበ ርቴዎች ነበሩ:: ሰፊው የኢት ገበሬ በረጅም ጊዜ ትግሉ በገኘው ድሉ የተነሳ ለአብዮቱ

ግን ያህል እንደሆነ በብዙ ቦታዎች በተግባር አያረጋገጠ ነው:: ለወደፊቱም ለድሉ በቂ ዋስትና ሊያስጡት የሚችሉ አስፈላጊ ዝግጅቶች በይበልጥ እንዲሟሉ ታሳቢ ትንቅንቅ እያደረገ ነው:: በኢት የሚካሄደው የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፀረ-ፊውዳል፣ ፀረ-ኢምፔሪያሊዝምና ፀረ-ቢሮክራቲክ ኃይሎች በሙሉ የሚያቅፍ በወዝአደሩ መሪነት በአርሶ አደሩ አጋሪነት የሚመሠረት የፀረ-ቢስቶን አምባገነንነት የሚያረጋግጥ መንግሥት መሆን ይገባዋል:: ይህ አብዮት በመሠረቱ የገጠር አብዮት በመሆኑ አርሶ አደሩን በተረጋገጠ መንገድ የመሬቱ ባለቤት ያደርገዋል:: ስለሆነም አርሶ አደሩ የዚህ አብዮት ተሸካሚ በመሆኑ ለብሔራዊ ነፃነትና ለዲሞክራሲ በሚደረገው ትግል ውስጥ በማያጠራጥር ሁኔታ ይታገላል::

ለ- ወዝ አደር

ግንም እንኳ የኢት ህብረተሰብ እድገት ጉልምስ ወዝአደሩ በቁጥር፣በንቃትና በድርጅት የሚጠበቀው በትን ቦታ በመያዝ በዚህ ዲሞክራቲክ አብዮት የመሪነቱን ስልጣን በፓርቲው አማካይነት እስከ አሁን ሊቀዳጅ ባይችልም በአሁኑ አብዮት በሙሉ ሃይሉ የሚካፈልና ይህንንም አብዮት ከብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት ወደ ሶሻሊስት አብዮት በቀጥታ ሊያሸጋግር የሚችል ይሄው መደብ በመሆኑ የመደብ ንጽህናው ተጠብቆ በማርክሲዝም በሌኒኒዝም ታንጾ አሁን ያለበትን ድክመት አስወግዶ ያመራሩን ብትር ሊጨብጥ የሚችለው በረጂም ትግልና መስዋእትነት ነው:: ይህ መደብ በበለጠ እንዲነቃ፣ እንዲደራጅና እንዲታጠቅ ከገበሬውም ጋር ያለው ህብረትና አንድነት እንዲመሠረትና እንዲጠናከር ሃቀኛ ማርክሲስቶችን በሙሉ ታሪክ የጣለባቸውን ሃላፊነት ለሟሟላት መጣር ይኖርባቸዋል::

ሐ- ንዑስ ከበርቴ

ይህ ክፍል ማርክስ እንዳለው "ተሸጋጋሪ መደብና የሁለትም መደቦች ፍላጎት በጋራና በአንድነት የሰፈነበት" ወላዋይና የሀይል ሚዛን ወደአጋደለበት የሚዞር፣ በመሆኑ በኢት አብዮት ውስጥ የሚጫወተውን ሚና ከጊዜ፣ ከመደብ ቅደም ተከተል አሰላለፍ፣ ከለውም ኃይል ሚዛን ጋር አያይዞ መመልከት ያስፈልጋል:: በዚህ መደብ ውስጥ ያለውንም የግራና የቀኝ ክፍል ጠንቅቆ ማጤን ያሻል:: በኢት ተጨባጭ የእድገት ደረጃ የዚህ መደብ አብዛኛውን ክፍል በዲሞክራቲክ አብዮት ውስጥ ጥቅም አለው:: ስለሆነም የአብዮቱ ወዳጅ ሊሆን ይችላል:: በዚህ መደብ ውስጥ ገበሬ፣ ተማሪ፣ ወታደር ነጋዴ በአጠቃላይም ትናንሽ የማምረቻ መሣሪያ ያላቸውን ያጠቃልላል::

ሠ- ኢ ወ አ ደርግ

ኢ ወ አ ደርግ ብዙ አብዮታዊ ሚና የተጫወተ ቢሆንም ቅሉ ከመደብ ጠባዩ የተነሳ ብዙ ስህተቶችን ፈጽሟል:: ...የፈጸመም ነው:: የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም በሥራ





ላይ እንዳይውል ያገደው ከገበሬ፣ በብሔሮች ላይ ያለው የትምክህተኝነት አቋም፣ በቢሮክራሲው ላይ የወደቀው የመቀራረብ እርምጃ፣ ህዝቡን በተስታጠቀ በኩል ያሰየው የመነመነ ፍላጎት፣ ለጠርነቱ አብዮታዊ አመራር ላለማስጠት የወሰደው ገንዘብ እርምጃ በቂ ማረጋገጫዎች ናቸው::

ኢ ወ አ ደርግ ፕሮግራሚነው ራሱ የተቀበለውን የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም በመከዳ (በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ላይ ገጽ 16. ገጽ 12. ወዘተ የሰፈረውን በመከዳ) ፀረ-ዲሞክራቲክ የሆነ አቋም ይዟል:: በብሔር ትምክህተኝነት የተነሳ ከቢሮክራሲው ጋር በመተባበር ለዲሞክራሲ የሚታገሉትን የጭቁን ብሔረሰቦችን እንቅስቃሴ በማፈን ላይ ነው:: በሰፊው ህዝብ ከመተማመን ይልቅ በቢሮክራሲውና በውጭ እርዳታ ላይ በመተማመን፣ የኢት ጭቁን ህዝቦች በበለጠ ለመንቃት፣ ለመደራጀትና ለመታጠቅ እንዳይችሉ የጭቁኖችን የዲሞክራሲ መብቶች አፍኖ ይዟል:: የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮቱ እንዲራመድ የዲሞክራሲን ጥያቄ አንግበው ዲሞክራሲ ለጭቁኖች አሁኑኑ ብለው በሚታገሉ ሃቀኛ ተራማጆች፣ ወዝአደሮች፣ ገበሬዎች፣ ወጣቶችና ጭቁን ሴቶች ላይ ጭፍጨፋ በመፈጸም ላይ ነው:: በመሆኑም ይህ ጉባኤ ይህን አይነት ፀረ-ህዝብ አቋም እያወገዘ በደርጉ ውስጥ ያሉ ግራ ክንፎች ይህን ሴራ በመታገል ትግላቸውን ከሰፊው ህዝብ ጋር እንዲያስተባብሩ ይህ ጉባኤ ጥሪ ያቀርባል::

ቢሮክራሲና አብዮት

ሌኒን "የመሠረታዊው የአብዮት ጥያቄ የመንግሥት ስልጣን ነው:: ስልጣኑን የያዘው የትኛው መደብ መሆኑ ሁሉን ነገር ይወስናል" እንዳለው ሁሉ ቢሮክራሲውን ሙሉ ለሙሉ ሊለውጥ የሚችለው የትኛው መደብ መንግሥት ስልጣን ላይ እንዳለና ይህም መደብና የተዋቀረው የመንግሥት መኪና ያላቸው የጋራ ጥቅምና ቅራኔ እስከ ምን ድረስ የከረረና የላላ እስከሆነ ድረስ ብቻ ነው:: ደርግ ዛሬ በሚካሄደው ፀረ-ቢሮክራቲክ ካፒታሊስት ትግል ውስጥ ከቢሮክራሲው ጋር ማበሩ በመደብ ጥቅሙ ከቢሮክራሲው ጋራ ያለው ቅራኔ ከላይ እንደተመለከተውም ያህል የላላ እንደሆነ ያሳያል:: የገማሽ ከበርቴና ፊውዳል የመንግሥት መኪና በሙሉ ሊሰበር የሚችለው በህዝባዊ አምባገነን መንግሥት ብቻ ሲሆን ወደዚህ ጉዳና የሚያመሩ ሃይሎች በሙሉ እንቅፋታቸው ስለሆነ መዎታት እንዳለባቸው የታወቀ ነው:: ከአድሃሪው ቢሮክራሲው ጋራ የማይታረቅ ቅራኔ ያለውና ለህዝቦች ሙሉ ነፃነት፣ ጠላት የሆኑትን ድርጅቶች በህዝባዊ ድርጅቶች ሙሉ በሙሉ ለመተካት አቅሙና ጥበብ ያለው ህዝባዊ አምባገነን መንግሥት ነው:: ሆኖም ይህንን ለመቀዳጀት በአብዮቱ ሂደት ውስጥ ስልጣንን የሚወስዱ ህዝባዊ ድርጅቶች ካሁኑ በመፍጠርና በማጠናከር አስተዳደሩንና ኢኮኖሚውን ለመቆጣጠር ቀጥተኛ ተካፋይነት እንዲኖራቸው ማድረግ ይገባል:: ይህንንም ተግባር ለማካሄድ፣

ሀ) ከአሮጌው መኪና ውስጥ አስጊና አስቸኳይ የሆኑትን ቦታዎች ከአድሃሪው ቢሮክራሲ ነጥቆ በህዝባዊ ድርጅቶች ቁጥጥር ስር ማዋል፣

ለ) ከዶሮዎችን ጫዝት በማበልጠን፣

ሐ) በወዝ አደሮች፣ በአርሶ አደሮች ቀጥተኛ መቆጣጠር ስር የአርሶውን መኪና አቀቲያች ግቀልና በአዲስና በህዝብ ወዳጅ ኃይሎች መተካት ነው::

በመሆኑም በኢት ውስጥ ቢሮክራሲው የሚሊተሪም ሆነ የሲቪል ቢሮክራሲው ከአብዮቱ ጋር በቀጥታ የተያያዙ ድርጅቶች በዲሞክራቲክ አብዮቱ ላይ ከፍተኛ አሻጥር እየሰሩ በመሆናቸው የዲሞክራቲክ አብዮቱ ወዳጆችና በዚህም ቀቅም ያላቸው በዚህ ቦታ እንዲተኩና ህዝቡም እስከአሁን የቋቋማቸው ህዝባዊ ድርጅቶች በቀጥታ ስር እንዲውሉና እንዲተኩ፣ ተራማጅ ኃይሎች ህዝቡን እንዲቀሰቅሱ ህዝባዊ ድርጅቶች እንዲጠናከሩ፣ ሰፊው ህዝብ በንቃት እንዲታገል ሰፊ ቅስቀሳ መደረግ አለበት:: ለህዝቡም ቢሮክራቲክ (ቀደም-ተከተሳዊ)መግለጫና የአስተዳደር ትምህርቶችም በሰፊው እንዲሰጠው፣ በአስተዳደሮችም ሁሉ እንዲካፈል፣ ሰፊ መንገድ ለመጥረግም የሚደረገው ትግልም ረጅምና መራራ በመሆኑ ህዝቡን ለረጅም ጊዜ ትግል ማዘጋጀት አለብን::

<u>የዲሞክራሲ ጥያቄ</u>

ዲሞክራሲ የመንግሥት አንዱ ገጽታ በመሆኑ ያሉና የሚኖሩት ዲሞክራሲያች ሁሉ የገዢውን መደብ ጥቅም የሚያስጠብቁ ናቸው:: ዛሬም በአገራችን ኢት ያለው የነውስ ከበርቴ መንግሥት ግንም እንኳን በአብዮቱ ጥቅም ሲኖረው የሚችል ቢሆንምና ለአብዮቱም ሂደት የሚጠቅሙ እንደ መሬት አዋጅ ያሉ የዲሞክራሲ መብቶች በአዋጅ ደረጃ ቢሰጥም ቅሉ ለሰፊው ህዝብ በብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት ውስጥ የሚበቀሉትን የዲሞክራሲ መብቶች አፍና በመያዙ አብዮቱን ወደፊት በፍጥነት ለማራመድ እንዳይቻል እንቅፋቶችን ፈጥሯል::

<u>ስለሆነም የዲሞክራቲክ አብዮት ግቡን በአስቸኳይ እንዲመታ ሰፊው ህዝብ ከአብዮቱ ሊያገኛቸው የሚገባ የዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ አሁኑኑ መለቀቅ የአብዮቱ አስቸኳይ ጥሪ ነው ብሎ ጉባኤው ያምናል:: ይህንንም አርማ ይዘው ለሚታገሉ ሃይሎች በሙሉ ያለተቆጠበ ድጋፍን ይሰጣል::</u>

<u>ስለ ብሔረሰብ</u>

ብሔረሰቦች መብታቸውን ለማስከበር ማለት ወይም ለመገንጠል ወይም ሪጅናል አውቶኖሚ ለመመስረት ወይም በፌደሬሽን ለመተዳደር በሚያደርጉት ትግል ላይ መብቱን የማወቅ ጉዳይ ያላንዳች ገደብ እስከ መገንጠል ድረስ ያላቸው መብት መታወቅ ይኖርበታል:: ነገር ግን ይህን ፕሪንሲፕል ወደ ተግባር ለመመንዘር ወሳኙ የንቅናቄዎች ይዘት ለማን ጥቅም የሚሰለፉ እንቅስቃሴዎች መሆናቸው ነው:: ፀረ-ኢምፔሪያሊስትና ፀረ-ፊውዳል ያልሆኑ እንቅስቃሴዎች ከእነዚህም





አድሃሪያች ጋር በጥቅም የተሳሰሩትን ኃይሎችን ሁሉ ማውገዝ አስፈላጊና የኢትም የአብዮት አድገት ደረጃ የሚጠይቀው ነው:: በኤርትራ ህዝብ ስም ለአረብ አድሃሪ ሃይሎችና ለኢምፔሪያሊዝም ጥቅም የቆሙትን የግንባሩን መሪዎች ጉባኤው ያወግዛል ::
በኤርትራም ሆነ ከኤርትራ ውጭ ያሉ የኤርትራ አገር ወዳጆችና ተራማጆች እንዲደራጁና ችግሩ በሰላም መፍትሄ አግኝቶ ለሁለቱ ጭቁን ህዝቦች በሚጠቅም መንገድ እንዲያልቅ ያልተቋረጠ ጥረት እንዲያደርጉ ጉባኤው ጥሪውን ያቀርባል:: በኡጋዴንም የምዕራብ ሶማሌ ነፃ አውጪ ግንባር በተሰኘ ስም ተሸፍኖ የገባውን የሰይድ ባሬ ጦር እያጋለጠ ይቃወማል:: ጭቁን ብሔረሰቦችም በሰሜን፣በደቡብ፣ በደቡብ ምሥራቅ ለእኩልነት፣ለነፃነት፣ ለዲሞክራሲና ለሶሻሊዝም ለሚያደርጉት አብዮታዊ ትግል ሙሉ ድጋፉን ይሰጣል::

በአኢትማ በኢት ያለውን የብሔረሰብ ቅራኔ አንስቶ ትክክለኛ አቋም ከወሰደና ይህ ቅራኔ የሚፈታበትን መንገድ መጠቆም ከጀመረ ጊዜው ረጅም ነው:: የብሔረሰቦችን እስከ መገንጠል ያላቸውን መብት ያለማወላወል የመቀበል አቋም በመፈቃቀር ላይ የተመሰረተ አንድነት እንዲፈጠርና የኢት ጭቁኖች በጋራ የመደብ ጠላቶቻቸው ላይ በአንድ ሃይል እንዲነሱ የሚረዳ አቋም ነው:: ይህን የብሔረሰቦችን ቅራኔ በመጠቀም አድሃሪያች አብዮታችን እንዳይቀለብሱ ተገቢ መፍትሄ እየተሰጠው መረመድ አስፈላጊ ነው:: ከዚህም በተረፈ ከጨቋኝ ብሔረሰብ የወጡ ተራማጆች ትምክህተኝነትን መቋቋምና ለጭቁን ብሔረሰቦች እስከመገንጠል ድረስ የአላቸው መብት ላይ ቅስቀሳ ማድረግ ሲኖርባቸው ከጭቁን ብሔረሰቦች የወጡ ደግሞ ጠባብ ብሔርተኞችን እየተቋቋሙ በእኩልነት ላይ ለተመሠረተ አንድነት ቅስቀሳ ማድረግ ግዴታቸው ነው:: ለብሔረሰቦች መቀራረብ አስፈላጊና የብሔረሰቦችንም ችግር ለመፍታት ከመሠረታዊ ተግባሮች አንዱ ነው ብሎ ጉባኤው ያምናል ::

<u>ህዝባዊ ሠራዊት</u>

ህዝባዊ ሠራዊት ከገበሬው፣ ከወዝአደሩ የተውጣጣ የወደፊቱ የህዝባዊ አብዮታዊ ጦር ጥንስስ ነው:: ይህም ህዝባዊ ሠራዊት በአሁኑ የኢት አብዮት ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ ነው:: <u>ሆኖም እውነተኛ ህዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት ሊሆን የሚችለው የወዝአደሩን አመራር ሲያገኝና አሁን ባለው ደረጃ ከቢሮክራሲው ነፃ ሆኖ አብዮታዊ አመራር ሲያገኝ ብቻ ነው::</u> ያለእነዚህ ሁኔታዎችና በህዝባዊ ጦር ውስጥ የገቡትን የሰለሉና የሚሊተሪ አድሃሪ ቢሮክራቶች ሳይመነጠሩ እውነተኛ አብዮታዊ ተልኮውን ሊያሳካት ስለማይችል አብዮታዊ አመራር እንዲያገኝ መታገልና በበለጠ እንዲነቃ፣ እንዲታጠቅ በሰፊው መቀስቀስ የሃቀኛ ተራማጆች ተግባር ነው:: የህዝባዊ ሠራዊት አካል የሆኑትና ለሚፈጠረው አብዮታዊ ሠራዊት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉትን ህዝባዊ ሚሊሺያዎችና የአካባቢ ሠራዊቶች መፈጠር በበለጠ መጠናከርና መንቃት፣ መደራጀትና መታጠቅ ለህዝባዊ አመጽ አስተማማኝ ደጀን ናቸው:: ስለዚህ ያለ ቢሮክራሲውና

ደርግ ተስኖ የነዚህ ሃይሎች እንዲጠናከሩ ከፍተኛ ቅስቀሳ መደረግ አለበት ብሎ ጉባኤው ያምናል::

## ህዝባዊ ድርጅቶች

በአብዮቱ ሂደት ብዙ ህዝባዊ ድርጅቶች ተፈጥረዋል:: እነዚህም ህዝባዊ ድርጅቶች የወደፊቱ የመንግሥት ሥልጣን መሠረቶች ናቸው:: እነዚህ ህዝባዊ ድርጅቶች ማለትም መኢሰአማ፣ የገበሬ፣ የቀበሌ፣ የሴቶች ማህበራት ወዘተ አብዮታዊ ሚናቸውን ሊጫወቱ የሚችሉት ቢነቁ፣ ቢደራጁና ቢታጠቁ ከቢሮክራሲውና ከደርግ ነፃ በመሆን በአድሃሪያን ላይ ነፃ እርምጃ መውሰድ ሲችሉ በመሆኑ ለዚህም ነፃ በሆነ መንገድ በይፋ መነቃቃት፣ በይፋ መደራጀትና በይፋ መታጠቅ ያስፈልጋቸዋል:: ስለሆነም እነኝህ የአብዮቱ ወሳኝ ሁኔታዎች እንዲሟሉ ዲሞክራሲ ለጭቁኖች ያለ ገደብ አሁኑኑ መለቀቅ አለበት:: እነዚህም ህዝባዊ ድርጅቶች ለማፍረስ አድሃሪያንና ቢሮክራሲው ትልቅ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል:: ስለሆነም የዲሞክራሲ አስቸኳይነት ከድርጅቶች መጠናከርና ከአድሃሪያኖች መዳከም ተለይቶ ሊታይ አይችልም::

## ተጀምሮ ስለነበረው ህብረት

በኢት ውስጥ በሚካሄደው አብዮት ጥልፍልፍነትና የጊዜው ሁኔታ መቀያየር የተነሳ ሃቀኛ ድርጅቶች የትግል ዘዴአቸውን እየቀያየሩ መታገል ትክክለኛ የሳይንስ ህግ ነው:: በድርጅቶች ማሃል የተፈጠረውን አለመግባባት ቤቶ በሚገባ ከተነጋገሩበት በኋላ በአኢተማ የ17ኛው ጠቅላላ ጉባኤ በህብረቱ መፈጠር ምክንያት ለህብረቱ ሰጥቶት የነበረውን ድጋፍ (የ17ኛው ጠቅላላው ጉባኤ የፖለቲካ ውሳኔ ገጽ 29—30 ተመልከት) በመመርመር ማለት:—

ሀ— እነዚህ ህብረቱን ለመፍጠር የተነሱ የተራማጅ ድርጅቶች ህብረቱ እንዲጠናከር፣ ከሰርጎ ገቦች እንዲጠነቀቁ . . . ጠባብ ቡድን ስሜት. . . ከመሰሰሉና ፀበኛ ያልሆኑ የመስመር ጥያቄን ከሚሸፍኑ የትግል ዘዴዎች ተቆጥበው ህብረታቸውን ለማጠናከር በዲሞክራሲያዊ መንገድ የሁለት መስመር ትግል እንዲያደርጉ ብሎ ያሳለፈውን ውሳኔ በማስታወስ፣

ለ— በህብረቱ ውስጥ ያሉ ማሌዎች ከወዝአደሩና ከድሃው አርሶ አደር ጋር በይፋ እንዲዋሀዱ፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ ማሌዎችን እንዲሰበስቡ የተደረገውን ጥሪ በማሰብ፣

ሐ— ሰፊውን ህዝብ ለማነቃቃት፣ ለማደራጀትም ሆነ በተራማጅ ድርጅቶች መሃል ሃቀኛ ፖለቲካዊና ርእዮተ አለም ትግል አካሂዶ የወዝአደሩን ፓርቲ በፍጥነት ለመመስረት ሂደቱን ሊያፋጥን የሚችለው መሣሪያ የዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ መለቀቅ ነው ብሎ ያመነበትን በማጤን_ ጉባኤው በህብረቱ ምክንያት ለወዝ አደር ሊግ፣ ለማሌሪድና ለሰደድ ሰጥቶት የነበረውን ድጋፍ እንደገና ለመመርመርና ትክክለኛ አቋም





ለመውሰድ ተስማምቷል:: በትግሉ ሜዳ በሰማእታትነት የወደቁትን የመኢሶን ጓዶችና የሌሎችም አብዮታዊያን የትግል አርማ ይዞ ለመጓዝ ቃሉ ኪዳኑን እያደሰ ለመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን) ያለውን ሙሉ ድጋፍ እንደገና ያረጋግጣል::

## ስለ አድርባይ ድርጅቶች/ወዝ፣ማሌሪድ፣ሰደድ/

አድርባዮች እንደ ደርግ የንዑስ ከበርቴ ክፍሎች በመሆናቸው ድንጉጥነት ያጠቃቸዋል:: ጠንካራ የሆነው የወዝ አደር ርእዮተ አለም በሳሉ ተቀሃዳቸው በቀላሉ በደርግ ፖለቲካ ሥር እየሟሙ ናቸው:: በዙውን ጊዜ በሰፊው ህዝብ ውስጥ አብዮታዊያን መስሎ የመታየት ፍላጎት አላቸው፡ ዋና አላማቸው ግን የሰፊው ህዝብ ትግል በትክክለኛ መስመር ተራምዶ ግቡን እንዲመታ ሳይሆን የሰፊውን ህዝብ ትግል ከንዑስ ከበርቴ ''አብዮታዊነት'' ጋራ በማስታረቅ በአድርባይነት መመረዝ ሆኗል:: ለዚህም እስከዛሬ ድረስ የቆሙለትን የዲሞክራሲ ጥያቄ በመካድ እንዲያውም ይህ ጥያቄ እንዳይለቀቅ በተቋዋሚነት ደረጃ የሚያቀርቧቸው መፈክሮች በቂ ማረጋገጫዎች ናቸው:: ለዚህ መንሸራተታቸው ዋና ምክንያቱ አድርባይነታቸው ቢሆንም ይህ አድርባይነታቸው በይፋ እንዳይጋለጥ፣ ማንነታቸው በግልጽ እንዳይታወቅ የዲሞክራሲን ጥያቄ ያለርህራሄ ይታገሉታል:: እንዲያውም ለዚህ ጥያቄ በአስቸኳይ መለቀቅ የቆሙትን ሃቀኛ ተራማጆች እየጠቆሙ ያስበራሉ፣ ያስገድላሉ:: ዲሞክራሲ ቢለቀቅ የሰፊው ህዝብ ነፃ ተሳትፎ ስለሚጨምር ዘረ ሸረሩ የሚሉት አድሃሪ ቢሮክራሲ በይፋ ስለሚጋለጥና ስለሚመታ የዲሞክራሲ ጥያቄ አሁኑኑ መፈታት የአድርባዮችን መሠረት ሊያናጋ እንደሚችል ይህ ጉባኤ በጥብቅ ያምናል::

## እ ር ዳ ታ

የኢት ጭቁን ህዝቦች አብዮታዊ እንቅስቃሴ እንደተጀመረ ይህንን እንቅስቃሴ ለማፈን ዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝምና አድሃሪያን የጋራ ግንባር በመፍጠር ሊያነካኩቱት ሞክረዋል:: ገን አብዮቱ የዓለም የሶሻሊዝምና የዲሞክራሲ አካል በመሆኑ እርዳታ ከሶሻሊስት አገሮችና ከሌሎች ተራማጅና በላም ወዳድ አገሮች በማግኘት ላይ ነው:: ሆኖም ይህ እርዳታ ሰፊው ህዝብ ለሚያደርገው ወሳኝ ትግል ድርሻውን እንዲያበረክት ከቢሮክራሲው አገልግሎት ነፃ ሆኖ ለሰፊው ህዝብ ጥቅም ቢውልና የአብዮቱም በሪ ሰፊው ህዝብ መሆኑ ታምኖ በራስ መተማመን የሚለውን መርህ መከተል ቢቻልና ሥራ ላይ ቢውል ብቻ ነው:: ስለሆነም በዓለም አቀፋዊነት መንፈስ ከሶሻሊስት አገሮችና ከሌሎችም አብዮታዊ ኃይሎች ጋር የሚደረገውን መቀራረብና ግንኙነት ጉባኤው ይደግፋል:: የሚሰጠውም እርዳታ ለህዝቦች ትግል አጋዥ እንጂ ወሳኝ እንዳልሆነ ያለማወላወል ያምናል::

## በእስር ላይ ስለሚገኙ ሀቀኛ ተራማጆች

አገራችን ውስጥ በሚካሄደው አብዮት ውስጥ እያሉ አብዮታውያን በየጊዜው ይወድቃሉ::

የሚወድቀው ኢትዮጵያን የትግል አርማ በማንሳት ማህበራችን እንደሚታገል ደግሞ ደጋግሞ ገልጿል:: ከዚህም ጋር ተያይዞ ዛሬ ደርግና በርካሪቢ በሳቸው ሥልጣን በመጠቀም በጎዳና ነዪ መሰማሪታቸውን እየተቃወምን የታሠሩት ሃቀኛ ተራማጆች፣ ወዝ አደሮች፣ አርሶ አደሮች፣ ...ቀን ቤቶች፣ ወጣቶችና መለዮለባሾች በስቸኳይ እንዲፈቱ ይህ ጉባኤ ይጠይቃል:: ለዚህም ...ታገላል::

ዲሞክራሲ ለጭቁኖች ያለገደብ አሁኑኑ !!
አብዮታዊ እናት አገር ወይም ሞት !!
የታሰሩት የህዝብ ወገኖች በአስቸኳይ ይፈቱ !!
የነቃ፣ የተደራጀና የታጠቀ የህዝብ ኃይል ያሸንፋል !!

<u>ይህን ውሳኔ ያስለፉት</u>

1- በቼኮዝላቫኪያ የኢት ተማሪዎች ማህበር

2- በዩጎዝላቪያ የኢት ተማሪዎች ማህበር

3- በሃንጋሪ የኢት ተማሪዎች ማህበር

4- በቡልጋሪያ የኢት ተማሪዎች ማህበር

5- በሶቪየት የኢት ተማሪዎች



# የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር
# በም·ጀርመን

ሐይደልበርግ 30/3/78

<u>ከ24-3-78 እስከ 27-3-78 በዲልስበርግ የምዕራብ ጀርመን</u>
<u>18ኛ ጠቅላላ ጉባኤ የፖለቲካ ውሳኔዎች::</u>

መ ግ ቢ ያ :-

በዲልስበርግ በተደረገው በ18ኛ ም/የጀርመን ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤ ከሉት 10 ውስጣዊ ማህበራትና የጥናት ክበባት ሰባቱ ማለት የበርሊን፣ ቦሁም፣ የካስል፣ የማይንዝ፣ የሐይደልበርግ፣ የሙንሸንና የሁገን ሲገኙ የሸቱትጋርት፣ የፍራንክፈርትና የሉቤክ ውስጣዊ ማህበራት አልተገኙም::

በጉባዔችን ላይ ለመሣተፍ የተገኙት እህት ቅርንጫፍ ማህበራት የፈረንሳይ፣ ስዊዝ፣ ቤልጂየም፣ ስዊድን፣ የሶቪየት ህብረት፣ የአውሮፓ የመጽሔት ቦርድ፣ የቢቶች ዲሞክራቲክ ማህበርና የአውሮፓ ማህበር ልዩ ጽህፈት ቤት ናቸው:: እነዚህ የእህት ቅ ማህበራትና የዩጎዝላቪያ፣ የአውሮፓ ስራ አስከያጅና ከውጭ ድርጅቶች ከ K S V (Kommunistische studenten veban )ና ከ KHG (Kommunistische Hochschul Gruppe) የአንድነት መግለጫ መልእክት አሰምተዋል::

ጠቅላላው ጉባኤ የተነጋገረባቸው የጥናት አርእስቶች:-

1) ስለ ጊዜያዊ የኢት ሁኔታ
   ሀ) በሰሜን ክፍለ ሃገር
   ለ) በመሐል ክፍለ ሃገር
   ሐ) በደቡብ ምስራቅ ክፍለ ሃገር

2) ስለ ዲሞክራሲ
   ሀ) ስለህጋዊና ህገወጥ ትግሎች

3) ስለ ደርግ
   ሀ) ቢሮክራሲ
   ለ) ህዝባዊ ድርጅቶች
   ሐ) ተራማጅ ድርጅቶች

4) ስለ ብሔር ጥያቄ
5) ስለ ጦርነቱና የሚሊሺያ ሚና
6) ጠቅላላ የማህበረት ዓመታዊ ሪፖርትና የማህበር ችግር

ይህ 18ኛው የም/ጀርመን ጠቅላላ ጉባኤ አብዮታዊ መንፈስ በተሞላበት ሁኔታ ተካሂዷል:: ከ24—27/03/78 የተካሄደው ጉባኤ የኢትን ተጨባጭ ሁኔታ ከመረመረ በኋላ ከዚህ የሚከተለውን የፖለቲካ ውሳኔ አሣልፏል::

ለዚህም የስራ ዓመት በስራ አስከያጅነት የወሰደው የሃይደልበርግ ውስጣዊ መህበር ነው::

ETHIOPIAN STUDENTS UNION
* EXECUTIVE COMITTEE *
IN FEDERAL REPUBLIC OF GERMANY





የኢት ጭቁን ህዝቦች አብዮታቸውን ካፈነዱበት ከየካቲት 66 ዓ.ም ጀምሮ ከፍተኛ መስዋእትነት የተሞላበት መራራ ትግል እንዳካሄዱና እንደሚያካሄዱ ለማንም ግልጽ ነው:: በዚህም መራራ ትግላቸው ብዙ ፈተናዎችንና ችግሮችን በማለፍ ደማቸውን አፍስሰው በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት በሚያደርጉት ረጅምና ጠመዝማዛ ጉዞና ጥርጊያ የሚሆኑ አያሌ ታሪካዊና አብዮታዊ ድሎችን ተጎናጽፈዋል:: ካካሄዱትም ውስብስብና ውጣ ውረድ የበዛበት የትግል ጉዞና ብዙ ጠቃሚ ትምህርቶችን ቀስመዋል::

የኢት ጭቁን ህዝቦች አብዮት በዚች አራት ዓመት እድሜ ውስጥ ከጠላቶቹ በየጊዜው ብዙ ጥቃቶች ደርሰውበታል፣ ብዙ የመደብ መንሸራተቶች ታይተውበታል፣ አጥቂነትና ተከላካይነት ተፈራርቀውበታል:: ሆኖም ግን እነኚህ በየጊዜው የተነሱበት የውስጥና የውጭ ፀረ—አብዮት ሃይሎች ብዙ ጥቃቶችና ፈተናዎች ቢያደርሱበትም ቆራጡ ጭቁን ህዝብ እነዚህን ጥቃቶች በየጊዜው እየተቋቋመ አብዮቱን ወደፊት ለማራመድ የሚያደርገውን መራራ ትግል አላቋረጠም::

የኢት ጭቁን ህዝቦች አብዮት በየጊዜው ብዙ ውጥረቶችን ያሣለፈ፣ ብዙ የመደብ መንሸራተቶች የታዩበት፣ በየጊዜው የተለያዩ ጠላቶች የተነሱበት፣ አጥቂነትና ተከላካይነት የተፈራረቁበት ቢሆንም ቆሉ ከአጥቂነት ወደ ተከላካይነት ከተሸጋገረበት ከመጋቢት 69 ዓ/ም ጀምሮ አዲስ የትግልና የፈተና ምእራፍ ውስጥ ይገኛል:: በዚህ የትግል ምእራፍ ውስጥ አዲስ የመደብ መንሸራተቶች እየታዩ ከመምጣታቸውም ሌላ አብዮቱ የሚገኝበት የቀልበሳ አደጋ ከጊዜ ወደ ጊዜ በፈጣን እርምጃ በመሄድ ላይ ይገኛል:: ትላንት ከጭቁን ህዝብ ጎን ተሰልፈው ለነፃ፣ ለተደራጀ፣ ለታጠቀ ህዝባዊ አመጽ እንታገላለን፣ የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ከስራ ላይ ይዋል፣ ዲሞክራሲ ለጭቁኖች በአስቸኳይ፣ የሀቀኛ ተራማጆች ህብረት ይጠንክር፣ ሀቀኛ ወዝ አደር ፓርቲ ይፈጠር ወዘተ እያሉ የሐቀኛ ተራማጆችና የሠፊውን ህዝብ መፈክሮች ሲያስተጋቡ የነበሩት ደርግ፣ ሰደድ፣ ወዝና ማሌሪድ ዛሬ ከዚህ አቋማቸው አፈንግጠዋል:: ደርግና እነዚህ አድርባይ ድርጅቶች ባደረጉት የቀኝ አድርባይ የመስመር ምርጫ የተነሳ ዛሬ አብዮቱ ያለበት ውጥረት ከመቸውም የበለጠ እየጨመረ ሄዷል:: ፀረ—አብዮት ሃይሎች ተጠናክረዋል፣ የአብዮቱ ሀይሎች ከመቸውም ይበልጥ በተጠቂነት ደረጃ ላይ ይገኛሉ::

ደርግና እነዚህ አድርባዮች የሚከተሉት መስመር አብዮቱንና የሀገሪቱን ብሔራዊ ነፃነት በከፍተኛ አደጋ ላይ ጥለውታል:: ከዚህ አደገኛ መስመር ምርጫ የተነሳ ደርግ ከሠፊው ጭቁን ህዝብ ይልቅ እምነቱን በአድሃሪው ቢሮክራሲ ላይ በመጣል የኢት ጭቁን ህዝቦች አብይ ጠላት የሆነውን የቀድሞውን ቢሮክራሲ በመጠገንና ከውጭ የሚገኘውን እርዳታ በመጠቀም የአብዮቱን ችግሮች ከአብዮት ሰሪው ከሠፊው ህዝብ ተሳትፎ ውጭ ለመፍታት በመጣር ላይ ይገኛል:: ባሁኑ ወቅት ደርግ ያገሪቱን ችግሮች ከአብዮቱ ነጥሎ በመመልከት በነፃ፣ በተደራጀና በታጠቀ ህዝባዊ አመጽ የሚለውን አብዮታዊ መፍትሄ ትቶ በአጭር ጊዜ ውስጥ ጠላቶችን

ደምስስ በተደላደለ ሁኔታ ወደፊት ለመራመድ በመመኘት ቢፈጠር ጃሞር ባለቀቀው በሽታ በሰፊው ህዝብ ላይ አምነት በማጣት፣ በሚሊዮን ከሚቆጠረው አብዮት ሰሪ ጭቁኑ ህዝብ ይልቅ በውጭ አርዳታ ላይ በተቀዳሚ አምነት በመጣሉ ዛሬ የኢትን አብዮት በታላቅ አዘቅት ውስጥ ጥሎታል::

ደርግና አድርባይ ድርጅቶች በሚከተሉት መስመር ከጊዜ ወደጊዜ ከሰፊው ህዝብና ከተራማጆች ጋር እየተቆረረጡ በሄዱ ቁጥር ከአብዮቱ ጠላቶች በተለይም ከአድሃሪው ቢሮክራሲው ጋር እየተቀራረቡና አንድነትን እየፈጠሩ በመሄድ ላይ ይገኛሉ:: በዚህ መሰረት ዛሬ ደርግና አድርባዮች በደረጉት የመስመር ምርጫ ሰፊው ህዝብ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቱን በመገፈፍ በየቦታው ይጨፈጨፋል፣ ሰፊው ህዝብ የዲሞክራሲ መብቶችን በመገፈፉና በመታፈኑ በገዛ አብዮቱ ውስጥ ሙሉ ተሳትፎውን እንዳያደርግ ተገዷል:: በየቦታው በተለይም በሰሜንና በደቡብ ህዝባዊ ድርጅቶች በመፈራረስ ላይ ይገኛሉ፣ አብዮቱ በነፃ፣ በተደራጀና በታጠቀ ትግል ወደፊት እንዲራመድ የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም በስራ ላይ እንዲተረጐም አብዮቱ ከሚገኝበት ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት እንዲሸጋገር የሚታገሉ መኢሶንና እንዲሁም ሌሎች ሀቀኛ ተራማጆች፣ ታጋይ ወዝአደሮች፣ ጭቁን ቤቶች፣ ገበሬዎች፣ መለዮ ለባሾች፣ ወጣቶች፣ ወዘተ እየታደኑ ይታሠራሉ፣ ይገደላሉ፣ ይሰቃያሉ፣ በነፃ አድሃሪያች ከእስር ቤት ይለቀቃሉ:: በዚሁ ዛቢያ በተለይም በፀረ ህዝብነታቸው የታወቁ የቀደሞ የኢሕአፖ አባላት ምህረት እየተደረገላቸው ነው:: ደርግ አድርባይ ድርጅቶችና ቢሮክራሲው የህዝብ ድርጅቶችን በቁጥጥራቸው ስር ለማድረግ በሚያደርጉት ጥረት ሰፊው ህዝብ በአብዮቱ ውስጥ በሙሉ ነፃነት ለመሣተፍ መንገዱ እየታጠረበት ሄዷል:: ዛሬ ደርግ ከሰፊው ህዝብ ይልቅ እምነቱን በፀረ-ህዝብ ቢሮክራሲ ላይ በመጣል ቁልፍ ቦታዎችን ያስያዛቸው የወጣላቸው አድሃሪ ቢሮክራቶች አብዮቱን በፍጥነት ለመደፈት የሚያደርጉት የኢኮኖሚና የፖለቲካ አሻጥሮች ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ ተፋፍሞ ይገኛል:: በሌላ ወገን ደርግ ለዚሁ አድሃሪ ቢሮክራሲ የዘመቻውን አመራር በመስጠት በዘመቻው ላይ ከፍተኛ ጉዳትን ከማድረሱም ሌላ በሺህ የሚቆጠሩ የመደበኛ ጦሩና የሚሊሽያው ህይወት በቀላሉ እንዲጠፋ አድርጓል:: ቢሮክራሲው ባደረገው የተቀነባበረ አሻጥር የተነሣ በሰሜን አድሃሪ የኤርትራ ተገንጣይ ቡድኖች 90 በመቶ የሚሆነውን ቦታ በቀላሉ ለመያዝ ችለዋል::

ደርግ የያዘው መስመር ከስከተለበት የፖለቲካ ክስረት የተነሣ በቁጥጥሩ ስር የሚገኘውን የዜና ማሰራጫ በመጠቀም በማን አለብኝነት የህዝብ ድርጅቶች ያሣለፉትን ውሣኔዎች እንዳላሣለፉ ያሳለፉትን እንዳለፉ እያደረገ ለማቅረብ ይጥራል:: ከሰፊው ህዝብና ከሀቀኛ ተራማጆች ይልቅ በድሃሪው ቢሮክራሲ በመተማመንና የውጭ እርዳታን አንደወሳኝ አድርጎ በመውሰድ ጭቁኑ ህዝብ ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ''አብዮታዊት ኢትዮጵያ ወይም ሞት''በማለት አብዮቱንና የአገሩን ዳር ድንበር ሳለማስደፈር በተነሳበት ወቅት ሶማሌን ለሥታህል ወራሪ ጠላት የውጭ ወታደሮችን እርዳታ መጠየቅ ተገዷል:: ደርግ በጭቁኑ ህዝብና በተራማጆች ላይ እምነት ቢኖረውና ዘመቻው አብዮታዊ አመራር ቢኖረው ኖሮ ይህን ጊዜያዊና አስቸኳይ ድል በሶማሌ ላይ ለመቀናጀት ይህን ያህል





ወታደሮች ከውጭ ኢትዮጵያ ድረስ ለመምጣት በላስፈለገ ነበር::

የምዕራብ ጀርመን ጠቅላላ ጉባኤ የኢትን ተጨባጭ ሁኔታ በመመርመር ዛሬ አብዮቱ የሚገኝበትን አሣሣቢ ሁኔታ ከጨነ በኋላ አብዮቱን ከቀልበሳ አደጋ ለማዳንና ትግሉን ወደፊት ለማራመድ ከዚህ የሚከተሉትን የፖለቲካ ውሣኔዎች አሣልፏል::

## የጊዜያዊ ወታደራዊ ደርግ

የጊዜያዊ ወታደራዊ ደርግ የነውስ ከበርቴ መንግስት እንደመሆኑ ሁሉ በመደብ ይዘቱ አንደየጊዜውና ሁኔታው ይወላውላል፣ ውስጡም ገራና ቀኝ ክፍሎች ያዘለ በመሆኑ ማህበራችን ''አብዮታዊ ሂስ''የሚለውን የማርክሲስት ሌኒንስት መርሆ በመከተል አብዮታዊ እርምጃዎችን በወሰደ ቁጥር ድጋፍ አንደሰጠና ፀረ-ህዝብና ፀረ-አብዮት ድርጊቶችን ሲያካሄድ ደግሞ ከሰፊው ህዝብና ከሃቀኛ አብዮታውያን ጎን በመሰለፍ አውግዞታል:: ዛሬ ሃቀኛ አብዮታውያን ይኸን ሣይንሣዊ አቋም በመከተል ደርግ ወደ ሰፊው ህዝብ እንዲጠጋ በመታገል ላይ ናቸው::

የደርግ በአብዮቱ ውስጥ ያለው ሚና የሚወሰነው ከሚወስዳቸው እርምጃዎች አንፃር በመነሳት ነው:: አብዮቱን ወደፊት ለማራመድና እንዲሁም ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን የሚያዳክም እርምጃዎች በወሰደ ቁጥር ተራማጆች ያልተቆጠበ ድጋፍ ሰጥተውታል:: ባሁኑ ወቅት በተለይም ከመጋቢት ወር 69 ዓ.ም አብዮቱ ከአጥቂነት ወደ ተከላካይነት ከተሸጋገረበት ጊዜ አንስቶ ደርግ ከሰፊው ህዝብና ከአብዮታውያን ይልቅ በድሃሪው የሲቪልና የሚሊተሪ ቢሮክራሲ ላይ በመተማመን ሳብዮቱ አደገኛ ሁኔታ በመፍጠር ላይ ነው:: ከቢሮክራሲው ጋር በተግባር በመቀሃዱ ለብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት ፕሮግራም በተግባር ለመመንዘር የሚታገሉትን ሃቀኛ አብዮታውያን፣ ወዝአደሮች፣ ጭቁን ቤቶችን፣ የገበሬ ማህበራት መሪዎችን፣ መለዮ ለባሽና ወጣቶችን ያሣድዳል፣ ያስረል ይገድላል:: በስነት አብዮታውያን መስዋእትነት የተቋቋሙትን ህዝባዊ ድርጅቶች ማለት መኢሰአማን፣ የቀበሌ ማህበራትን፣ የገበሬና የሴቶች ድርጅቶችን አብዮታዊ ፈረቸው ለማሣትና ለማፈራረስ በሚደረገው ፀረ-አብዮት ሴራ ከቢሮክራሲው ጋር በተግባር ይሰለፋል:: የነዚህ ድርጅቶች ወኪሎች የሚያሣለፉትን አብዮታዊ ውሣኔዎች በመሻር በነፃ በይዘታቸው የማይመሣሰሉትን በማን አለብኝነት በቁጥጥሩ ስር ባደረጋቸው ጋዜጣዎች ላይ ያወጣል::

ከሀቀኛ አብዮታውያንና ከሠፊው ህዝብ ይልቅ በይበልጥ በውጭ እርዳታ ላይ ይተማመናል:: አብዮታዊ ከሆነ የፖለቲካ መፍትሄ ይልቅ በጭር ጊዜ ድልን ለመቀዳጀትና የራሱን ስልጣን ለማደላደል በሚሊተሪ ሃይል ብቻ በማተኮር በትምክህተኝነት ጭቁን ብሔረሰቦችን ይጨፈጭፋል:: ያስጨፈጭፋል::

ጉባኤያችን እነዚህን ፀረ—ህዝብና አፀያፊ ተግባሮችን በማጤን ያብዮቱን አቅጣጫ ለመ ዘውም ቢሆን የሚቀጠው መሆኑን በመገንዘብ በደርጉ ውስጥ ለሚገኙ ተራማጆችና አገር ወዳዶች ዛሬ ደርግ የሚከተለውን ፀረ—ህዝብና ፀረ—አብዮት ስራ ከስራው ህዝብና ከአብዮታውያን ጋር ተሰልፈው እንዲታገሉ አብዮታዊ ጥሪውን ያቀርባል:: ስለሆነም:—

— በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ሳይ የሰፈሩት በተግባር እንዲተረጎሙ ለሚደረገው ትግል፤

— ካንዱ አመት ተኩል በፊት በህዝብ ድርጅት ጽ/ቤት ረቂቆ አነ ዓለማየሁ ሃይሌ ከፃፉ ነውት ነበር የተባለው የዲሞክራሲን መብት በስራ ሳይ ለማዋል ይታወቃል የተባለው ፕሮግራም አሁኑኑ በስራ ሳይ እንዲውል፤

— ሀቀኛ አብዮታውያን በተለይም መኢሶን ያገሬቱን ቁጠባጭ ሁኔታ በመገንዘብና አብዮቱን ወደፊት ለማራመድ በህጋዊ ትግል ያስጣሬቸውን አንዳንድ የታወቀ አበሳቸውን ትግል ስለቱን ሰውጭ ህቡእ በማስገባቱ ይኸም እንደ ወንጀል ተቆጥሮ በዚህ ሃቀኛ ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅት አበሳትና ደጋፊዎች ናቸው ተብሉ በሚጠረጠሩ ሳይ የሚደረገው የማሣደድ፤የግድያ፤የሥራትና የማሰቃየት ተግባር አሁኑኑ እንዲቆም፤

— ያለ ስራው ህዝብ ተሣትፎ በቀይ ሽብር ስም የሚካሄደው አሰሣ ከአድሃሪያች ጋራ አያዳበለ ተራማጆችን በመምታት ሳይ ነው:: ይኸ ቀይ ሽብር ትክክለኛ ትርጉም እንዲኖረው ተራማጆችና ስራው ህዝብ እንዲሣተፉበትና አድሃሪያችን በመመንጠር ሳይ እንዲያተኩር ጓህበሬችን ይጠይቃል::

— በቢሮክራሲና በውጭ እርዳታ ሳይ ከመተማመን ይልቅ አብዮት ሰሪው ሰራው ህዝብ በመሆኑና ያለሰራው ህዝብ ተሳትፎ አብዮቱ ግቡን ስለማይመታ ሰራውን ህዝብ በይበልጥ ለማንቃት፤ ለማደራጀትና ለማስታጠቅ በሚደረገው ትግል እንዲያገዝና ሰራው ህዝብም ከሌሎችም ተጽእኖ ነፃ አርምጃዎችን እንዲወስድ ጉባኤያችን አጥብቆ ይጠይቃል:: ለዚህም ይታገሳል::

<u>ስ ለ ቢ ሮ ክ ራ ሲ</u>

ቢሮክራሲው በመደብ ይዘቱ የፀረ—አብዮት አካል ነው:: የኢምፔሪያሊስቶችና የፊውዳሊዝም ጥቅም የሚያስከብር በመሆኑ ለዚህም ተግባር ቢበል ኢምፔሪያሊስቶች ከትኩተው ያሣደጉት ስለሆነ በይዘቱ የነበሩን በህልና ፖለቲካ ዘይቢ ያንፀባርቃል ፤ አብዮታዊ ሂደቶችን ለማኮላሸትና ማንኛውንም የፀረ—አብዮት ሤራዎችን ያቀነባበረል::





ሀቀኛ አብዮታውያን ይህን በመገንዘብ ያለርህራሄ ታግለውታል፤ ይታገሉታልም:: በመሆኑም ከብዙሃኑ ሳይ ይኸ የፀረ—አብዮት ሃይል እንደሚመታ ሰፍሯል:: ነገር ግን ይኸን ሃቀ በመሣት ወይም በድርበይነት በመታወር ደርግ በስተዳደር ውስጥ ቁልፍ ቦታዎችን ለወጣሳቸው ቢዚልና ሚሊተሪ አድሃሪ ቢሮክራቶች በመስጠት ከአብዮቱ ወገናች ይልቅ ፀረ—አብዮት ሃይሎችን ይረዳል:: አብዮቱ የፈጠራቸው ህዝባዊ ድርጅቶች የዚህ ቢሮክራሲ ተቀጢሳ እንዲሆኑ ደርግ በይፋ ያገዛል:: በሰሜንና በደቡብ ምስራቅ የዘመተውን ሰራዊት ይኸው አድሃሪ የሚሊተሪና የሲቪል ቢሮክራሲ አዝማች በመሆኑ ባገሬቱና ባብዮቱ ሳይ ትልቅ ጉዳትን አድርሧል:: ስለሆነም:—

— ህዝባዊ ድርጅቶች ከቢሮክራሲው ተጽእኖ እንዲላቀቁና ነፃ አርምጃዎችን እንዲያፋፍሙ::

— በደቡብ ምስራቅና በሰሜን ኢት ለደረሰው አደገኛ ሁኔታና ለሃገሪቱ ዱንበር እስከ መደፈር ለመድረሱ ተጠያቂው ይኸው አድሃሪ ቢሮክራሲ በመሆኑ፤

— ቁልፍ ቦታዎች በሃቀኛ ተራማጆችና ባገር ወዳድ እንዲተኩና በነፃነም ቢሮክራሲው ያለርህራሄ እንዲመታ ጉባኤያችን አጥብቆ ይጠይቃል፤ ለዚህም ይታገሳል::

<u>ስ ለ ዲ ሞ ክ ራ ሲ</u>

ጭቆን የኢት ህዝቦች ከፋሽስታዊ የኃይለስላሴ የፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በለማቋረጥ መስዋእትነት ከሚታገሉሳቸው ጥያቄዎች አንዱ የዲሞክራሲ ጥያቄ ነው:: ይህ ጥያቄ ዛሬ የኢት አብዮት የደረሰበት ቦታና እንዲሁም የአገሬቱን አጠቃላይ ሁናቴ ሲታይ አሁኑኑ መፈታት ያለበት ነው::

የዲሞክራሲ ጥያቄ የብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት መሠረታዊ ጥያቄ እንደመሆኑ መጠን የካቲት 66 አብዮቱ ኢት ውስጥ ከፈነዳበት ጊዜ ጀምሮ ሰራው ህዝብና ተራማጆች ያለምንም ማቋረጥ ታግለውለታል:: የጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥትም በፕሮግራሙ ሳይ ለሰራው ጭቁን ህዝብ ዲሞክራሲ ያለገደብ እንደሚለቀቅ አስፍሮታል:: ከዚህም ሌላ በሥራ እንደሚተረጎመው ደጋግሞ ቃል መግባቱ ይታወቃል::

ይህ ሆኖ ሳለ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ይህንን እስከ:አሁን ጊዜ ድረስ የዲሞክራሲን ጥያቄ አንቆ በመያዙ አብዮታችን በተከሳካይነት ሳይ ይገኛል:: ሰሬው ህዝብ የዲሞክራሲ መብቱ ታውቆለት፤ :ከአልነቃ፤ ከአልተደራጀና ከአልታጠቀ አብዮቱ ምንም ጊዜ ወደፊት ሊራመድ አይችልም:: የሰራው ህዝብ ዲሞክራሲ መብቶች አለማገኘት የሚጠቀመው ፀረ—አብዮተኞች በሰራው ህዝብ ሳይ አፈጥር ለመስረት ኃይሳቸውን ለማጠናከርና ለማስተባበር እንዲችሉ ብቻ ነው ::



...HIOPIAN STUDENTS UNI...

ከዚህም በመነሳት በጭቆና ህዝብ ላይ ይህ ነው የማይባል ጉዳት ያደርሳሉ:: ስለዚህም፡—

— ሰፊው ህዝብ ነቅቶ፣ ተደራጅቶና ታጥቆ አብዮቱን ወደፊት ለማራመድና ከአሁን በፊት የተቀዳጃቸውን ድሎች ለማስከበር፣

— ሌት ተቀን በጭቆኑ ላይ የአለ የሌለውን ተንኮል የሚሸርቡበትን የፊውዶ ቡርዧ ቢሮክራሲ ለመስበር፣

— የወዝአደሩ ፓርቲ ህዝባዊ አብዮታዊ ገንበርና ህዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት ለመፍጠር የሚደረገውን ትግል እንዲያፋፍም፣

— በብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት ፕሮግራም የሰፈረውንና በዚህ ፕሮግራም የገባውን ቃል ኪዳን የህዝባዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ በወረቀት ላይ ብቻ ሳይሆን በተግባር መግለጽ ስለሚያስፈልገው፣

★ EXECUTIVE COMMITTEE ★ IN FEDERAL REPUBLIC OF GERMANY

— ሰፊው ህዝብ ከዳር እስከ ዳር እንደ አንድ ሰው ሆኖ በመንቀሳቀስ የውስጥና የውጭ አድሃሪ ሃይሎችን በመደምሰስ ብሔራዊ ነፃነቱን እንዲያስከብር ወሳኝ የሆነው የዲሞክራሲ ጥያቄ ያለገደብ አሁኑኑ እንዲለቀቅ:: በአሁኑ ወቅት የጭቁን ህዝብ የዲሞክራሲ መብቶች እንዳይለቀቁና በተለያዩ ስንኩል ምክንያቶችን በመስጠት የሚታገሉ አድርባይ ድርጅቶችን ማለት (ኃዝ፣ ግሌሬድ፣ ሰደድ) በዚህ ፀረ—ህዝብና የቆሙ አድርባይ አቋማቸው ከአድሃሪያን ጋራ በቀጥታ እንደሚሰለፉና የፀረ—አብዮት ትግል በማጠናከራቸው አያወገዝ፣ የዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኑ ህዝብ ያለገደብ አሁኑኑ እንዲለቀቅ ጉባኤአችን አጥብቆ ይጠይቃል:: ለዚህ አንገብጋቢ ጥያቄ ከሚታገሉ ሐቀኛ ተራማጆችና አብዮታውያን ጎን ተሰልፎ ይታገላል::

## ስለ የውጭ ዐርዳታ

ማንኛውም አብዮት ግቡን እንዲመታ ከተፈለገ ዓለም አቀፋዊ ዐርዳታና ድጋፍ ከተራማጅ ኃይሎች ማግኘት ይኖርበታል:: የኢት ጭቁን ህዝቦች አብዮት ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ተራማጆች አብዮቱ የዓለም አቀፋዊ የተራማጆችን ድጋፍና ዐርዳታ እንዲያገኝ ያልተቋረጠ ትግል አድርገዋል:: ሆኖም እነኚን አብዮቱን ለማካሄድ ዓለም አቀፋዊ ዐርዳታና ድጋፍ ቢያስፈልገውም ቅሉ በማንኛውም አገር አብዮት ሠሪውና ታሪክ ሠሪው ሰፊው ህዝቡ እንደመሆኑ መጠን ተራማጆች በተቀዳሚ ደረጃ መውሰድ የሚኖርባቸው ''ራስ በራስ መተማመን'' የሚለውን አብዮታዊ መርህ መሆን አለበት:: ይኸውም ተራማጆች በተቀዳሚ በአብዮት ሰሪ ሰፊው ህዝብ የመፍጠርና የመታገል ችሎታ ላይ እምነታቸውን መጣል ይኖርባቸዋል:: በዚህም መሠረት ተራማጆች የሚጠይቁት





ዐርዳታ ወይንም ድጋፍ አብዮት ሰሪው ሰፊ ህዝብ በሚያደርገው ትግል የተጓደለ ማሟያ፣ ለትግሉ አጋዥ እንጂ ወሳኝ መሆን የለበትም:: ራስ በራስ መተማመን በተቀዳሚነት ማጠቀሙ የማንኛውንም ዓይነት ተጽእኖ ሙከራ የሚያከሽፍ ከመሆኑም በላይ ለብሔራዊ ነፃነትና ክብር ለአለማስደፈር ዋስትና ይሰጣል:: ማህበረችን ኢት ደሃ አገር እንደመሆኑዋ መጠን ሰፊው ህዝብ ለሚያካሂደው አብዮት የውጭ ዐርዳታ እንደሚያስፈልገ ምንም አይጠረጠርም:: ሆኖም ከውጭ የሚገኘው ዐርዳታ በእኩልነት፣ በወንድማማችነትና በሐቀኛ የወዝአደር ዓለም አቀፋዊነት ላይ መመሥረት ይኖርበታል::

በዚህ መሠረት ከውጭ የሚገኘው ዐርዳታ በምንም አይነት ሁኔታ የኢኮኖሚ ሆነ የፖለቲካ ተጽእኖ በአገሪቱና በአብዮቱ ላይ የሚያስከትል መሆን የለበትም:: በአሁኑ ጊዜ ደርግ የውጭ ዐርዳታን በሚመለከተው ረገድ የሚከተለው መስመር ዐርዳታን እንደ ወሳኝ የሰፊውን ህዝብ የመታገልና የመፍጠር ችሎታ እንደ አጋዥ አድርጎ የመውሰድ አዝማሚያ ይታይበታል:: ይህ ፀረ—ህዝብ ፀረ—አብዮት መስመር ብሔራዊ ነፃነትን የሚያስደፍር፣ አብዮትን የሚያኮላሽ፣ አገሪቱን ጥገኝነት ውስጥ የሚከት አደጋ ለመፍጠር ስለሚችል ይህን አደገኛ መስመር ተራማጆች ከሰፊው ህዝብ ጎን በመቆም ማጋለጥና መታገል ይኖርባቸዋል:: የኢት አብዮት ሰሪ ሰፊው ጭቁን ህዝብ እንደመሆኑ መጠን በውጭ ዐርዳታ ላይ ሙሉ ለሙሉ ተመርኩዞ ዘላቂ ድል ለመጎናጸፍም ሆነ ሐቀኛ አብዮት ለማድረግ አይቻልም:: ስለሆነም:—

— ደርግ አሁን የያዘውን ዐርዳታን እንደ ወሳኝ አድርጎ መውሰዱን በማቆም አብዮቱን ወደፊት ለማራመድ የሰፊውን ህዝብ የመፍጠርና የመታገል ችሎታ በተቀዳሚ መውሰድ ይኖርበታል:: ይህንንም በተግባር ለመተርጎም ሰፊው ህዝብ በአብዮቱ በይበልጥ እንዲሳተፍ የሚያስፈልጉትን ዲሞክራሲያዊ መብቶች መለቀቅ ይኖርበታል:: ለጭቁኑ ህዝብ አብዮታዊ ተሳትፎ እንቅፋት ከሆነው ፀረ—ህዝብ ቢሮክራሲ ጋር የሚያደርገውን እርቅና እምነት በማቆም ይህን ፀረ—ህዝብ ቢሮክራሲ ለመደምሰስ በሚደረገው ትግል ከሰፊው ህዝብና ከሐቀኛ ተራማጆች ጎን እንዲሰለፍ አብዮታዊ ጥሪ እናቀርባለን::

## ስለ ዘመቻ

የኢት ጭቁን ህዝቦች አብዮታቸውን፣ ድንበራቸውን፣ ብሔራዊ ክብራቸውን ለማስከበር የውጭና የውስጥ ጠላቶችን ለመቋቋም ከጭቁን መለዮ ለባሾችና ህዝባዊ ሰራዊት የተውጣጣ ፀር በሰሜን አድሃሪ የኤርትራ ተገንጣይ ቡድኖችን፣ በደቡብ የሱማሌ መንግሥት በኢምፔሪያሊስቶችና በአንዳንድ የአረብ መንግሥታት ድጋፍ የሚያካሂደውን ወረራ ለመቋቋም እንደዘመተ ይታወቃል:: ተራማጆች ይህን ዘመቻ አስፈላጊነት ሲቀበሉና ሲደገፉ ዘመቻው የተሳካ ውጤትን እንዲሰጥ አብዮታዊ አመራር እንዲኖረው፣ አንቂ ካድሬዎች በብዛት በዘመቻው ላይ እንዲሳተፉ የአደረጉትን

አብዮታዊ ጥሪ ትቶ ደርግ የዚህን ዘመቻ አመራር ለአድሃሪ ቢሮክራሲ በመስጠት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ጭቁን ወለዮ ለባሾችና የህዝባዊ ሰራዊት አባሎች በተቀነባበሩ የአድሃሪው ቢሮክራሲ አሻጥሮች ህይወታቸውን አጥተዋል:: በተጠማሪ በዚህ ቦታ የሚገኙ ጭቁን ብሔረሰቦች በአድሃሪው ሚሊተሪ፣ ቢሮክራሲና ነፍጠኞች በጭፍን በብሔረሰብ ትምክህተኝነት ተጨፍጭፈዋል:: ደርግ በጭቁን ህዝብ እምነት በማጣቱና አብዮታውያን የአደረጉትን ጥሪ በአለመቀበሉ ይህ ዘመቻ በበሜንም ሆነ በደቡብ ምሥራቅ ብዙ ጉዳትን አስከትሎአል:: ደርጉ ዘመቻውን ለቢሮክራሲ አሳልፎ በመስጠትና በሚከተለውም የተሳሳተ የፖለቲካ መስመር ከስረት ለሱማሊ ወራሪዎች ከሚበቃ በላይ የዘመተው መደበኛ ጦርና ህዝባዊ ሠራዊት አልበቃ ብሎት በሺህ የሚቆጠሩ የውጭ ወታደሮች በዚህ ዘመቻ ላይ እንዲሳተፉ ተደርጓል:: እርግጥ ዛሬ ደርግ በውጭ እርዳታ የሱማሌን ወራሪ ጦር ለማባረር ቢቻልም ይህ አስቸኳይ የጦር መፍትሄ በበኩላችን ዘላቂ መፍትሄ ነው ብለን አናምንም። በዚህ ቦታ ዘላቂ መፍትሄ ሊገኝ የሚችለው የአካባቢው ጭቁን ህዝብ ነቅቶ፣ ተደራጅቶና ታጥቆ በአብዮቱ ውስጥ ሙሉ ለሙሉ ለመሰተፍ ሲችል ብቻ ነው:: ደርግ አሁን በሱማሊ ላይ የአገኘውን ሁኔታዎችና የጦር ድል እንደ መፍትሄ በመቁጠር የኤርትራንም ችግር በጭፍን ወታደራዊ ስሜት በመሠረት በጭቦባበይ መንገድ ለመፍታት በመጣር ላይ ይገኛል:: ይህን ዓይነት የጦር መፍትሄ በተለይ በዚህ ቦታ ከተገንጣይ ቡድኖች ይልቅ በጭቁን የኤርትራ ህዝቦች ላይ ጭፍጨፋን ስለሚያስከትል እንዲሁም ይህ ዓይነቱ ጭፍጨፋ ከተካሄደ ህዝቡ ለአድሃሪ ተገንጣይ ቡድኖች ያለውን ድጋፍ መጠመር ብቻ ሳይሆን በኤርትራና በኢት ጭቁን ህዝቦች መሐከል የአለውን የትግል አንድነት ያፋልሳል::

— ደርግ በጭፍን ወታደራዊ ስሜት በመሠረት የሚያደርገውን የጦር መፍትሄ በተቀዳሚነት መውሰዱን ትቶ አብዮታዊ የፖለቲካ መፍትሄዎችን እንዲፈልግ፣

— በኤርትራ ህዝብና በኢት ህዝብ መሐከል የሚካሄደው ከንቱ የደም መፋሰስ እንዲቆም ከተገንጣይ ቡድኖች ጋር የሰላም ውይይት እንዲከፈት፣

— በዚህም ቦታ የሚገኙት ብሔረሰቦች መብት ማወቅና በተግባር መመንዘር ይኖርበታል፣

— ዛሬ በሰሜን ሆነ በደቡብ ምሥራቅ በተደረጉት ዘመቻ ላይ ለደረሱት ዱከሞቶች መሠረታዊ ምክንያቶቹ የሰው ሃይል ማነስ ሳይሆን ዘመቻው አብዮታዊ አመራር በማጣቱና ደርግ በጭቁን ህዝብና በሃቀኛ ተራማጆች ላይ እምነት በማጣቱ ነው:: ስለሆነም ደርግ የውጭ እርዳታን ወበኝ አድርጉ በመውሰድ ፋንታ በተቀዳሚ በሰፊው ህዝብ የመታገልና የመፍጠር ችሎታ ላይ መተማመን ይኖርበታል:: የኢትን ብሔራዊ ነፃነት ለማስከበርም ሆነ አብዮቱን ከግቡ ለማድረስ ከጭቁኑ ህዝብ በስተቀር ሌላ ሃይል ሊኖር አይችልም:: ስለሆነም ዛሬ ደርግ ከሰፊው ህዝብ አብዮታዊ ተሳትፎ ውጭ የአገሪቱንና የአብዮቱን ችግሮች በውጭ ወታደሮችና ሃይሎች እርዳታ ለመፍታት





የሚያደርገውን ፀረ—ህዝብና ፀረ—አብዮት ድርጊት በአስቸኳይ በማቆም ህዝቡ በአብዮቱ ውስጥ ሙሉ ተሳትፎ በማድረግ በውስጥና በውጭ የተነሱበትን ጠላቶች ሊደመስስ የሚያስችሉትን የዲሞክራሲ መብቶች በአስቸኳይ መልቀቅ አለበት::

## ስለ ተራማጅ ድርጅቶችና ተጀምሮ ስለነበረው ህብረት

በአገራችን ውስጥ በሚካሄደው አብዮት የተራማጅ ድርጅቶች በበዛት መፍለቅና የነዚህም ድርጅቶች አንድ ላይ መሰብሰብ ለአብዮቱ መገፋት፣ የወዝ አደሩን ፓርቲና ህዝባዊ አብዮታዊ ግንባሩን ለመፍጠር ለሚደረገው ትግል አስፈላጊ መሆኑ ይታወቃል:: በዚህ መሰረት ማህበራችን በኢት ውስጥ የሚገኙ ተራማጅ ድርጅቶች በአንድነት እንዲሰበሰቡና ትግላቸውን እንዲያስተባብሩ ያልተቋረጠ ጥሪ ማቅረቡ አይዘነጋም::

ከየካቲት 69 ዓ/ም አምስት ማሌ ህቡእ ድርጅቶች ማለትም መኢሶን፣ ኢጭአት፣ ወዝአደር ሊግ፣ ሰደድና ማሌሪድ ህብረት በመመስረት የጋራ መግለጫና የድርጊት ፕሮግራም ባወጡበት ወቅት ማህበራችን ይኸን አብዮታዊ እርምጃ የወዝአደሩን ፓርቲና ህዝባዊ አብዮታዊ ግንባሩን ለመመስረት የሚደረገውን ትግል እንደሚያፋጥን በመተማመን ድጋፋችንን ሰጥተናል:: ማህበራችን ይኸን ድጋፍ ለህብረቱ በሰጠበት ጊዜ ድጋፉን የመሰረተው:—

— ድርጅቶች በወዝ አደር ፓርቲ አፈጣጠር ላይ ያላቸውን አንድ አይነት አቋም በመመልከት፣

— በአብዮቱ ዋና ቅራኔዎች ላይ ያላቸውን አቋም በማጤንና በአብዮቱ እንገብጋቢ ጥያቄዎች በተለይም በቢሮክራሲው፣ በዲሞክራሲ ጥያቄ ላይ የነበራቸውን አቋም እንዲሁም በብሄአኘ ሳይ የነበራቸውን አቋምና አያንዳንዳቸውን ድርጅቶች ፕሮግራም በማጤን ነበር:: ሆኖም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መኢሶንና ኢጭአት በቀድሞ አብዮታዊ አቋማቸው ላይ ፀንተው ሲቆዩ የተቀሩት ማለትም ሰደድ፣ ወዝና ማሌሪድ የጋራ አቋማቸውን ከድተዋል:: እነዚህ ሶስት ድርጅቶች በተጠቀሱት ጥያቄዎች ላይ የነበራቸውን አብዮታዊ አቋም ከመቀየራቸውም በላይ በፍጹም አድርባይነት አብዮቱ ወደፊት እንዳይራመድ እንቅፋት በመሆን ከደርግ የቀኝ ክንፍና ከአድሃሪ ቢሮክራሲ ጋር በመተባበር በመኢሶንና በሃቀኛ ተራማጆች ላይ በሚደረገው ዘመቻ ሙሉ በሙሉ በመሳተፍ የሐቀኛ የተራማጆች ህብረት እንዳይፈጠር በመታገል ላይ ይገኛሉ:: ዛሬ እነዚህ አድርባይ ድርጅቶች የደርግና የቢሮክራሲ ተቀጥያ በመሆንና በአብዮቱ እንገብጋቢ ጥያቄዎች ላይ ባላቸው አቋም በፍጹም የተራማጅነት ጠባይ ስለማይታይባቸው ይኸ 18ኛው የምእራብ ጀርመን ጠቅላላ ጉባኤ በህብረቱ ሳቢያ ለነዚህ

3ት ድርጅቶች የሰጠውን ድጋፍ በሙሉ ያነሳል:: ይህ ጉባኤ የሃቀኛ ተራማጆች ህብረት እንዲፈጠር ከሃቀኛ ተራማጆች ጉን ቆሞ ይታገላል::

## መ ኢ ሶ ን

ማህበራችን ለዚህ ሐቀኛ የማሌ ድርጅት በኢት አብዮት ውስጥ ያለውን ህልውናና ፕሮግራሙን በመመርመር ያልተቆጠበ ድጋፉን እንደሰጠ ይታወሳል:: ይህ የማሌ ድርጅት የኢት አብዮት ትክክለኛውን ፈር እንዲይዝ ከኢት ጭቁን ህዝቦች ጉን በመሰለፍ ግራ አክራሪነትና ቀኝ አድርባይነትን እየታገለ ለህዝባዊ ድርጅቶች መፈጠር፣ለማሌ ድርጅቶች ማበብ ትግል ያደረገና የሚያደርግ ድርጅት ነው:: የኢት አብዮት አሁን ካለበት ደረጃ እንዲደርስ በግንባር ቀደምትነት የታገለ አንጋፋ ድርጅት ነው::

ከጥቂት ጊዜ ወዲህ ያብዮቱን አዝማሚያና ሂደት የኢት ተጨባጭ ሁኔታን በመመርመርና አብዮቱን ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ለማሸጋገር ለሚደረገው ትግልና ለመጨረሻው ፍልሚያ በር ለመክፈት በሕጋዊ መስክ ያሰማራቸውን የታወቁትን አባላቱን ህቡዕ ማስገባቱን ይህ የውነተኛ የማሌ የትግል ስልት ስለሆነ ጉባኤያችን ያልተቆጠበ ድጋፉን ይሰጠዋል:: ከጉኑም ቆሞ ይታገላል:: ይህንን ሣይንሳዊ ሃቅ በመዘንጋት ደርግ ወዝ፣ ማሌሪድና ሰደድ ከአድሃሪው ቢሮክራሲ ጋር በተግባር በመሰለፍ በዚህ አብዮታዊ ድርጅት ላይ የሚያካሂዱትን የመግደል፣ የማሰርና የማሣደድ ድርጊት ሌላ የለየላቸው አድሃሪ ድርጅቶች ጋር አንድ አድርጉ ለማቀረብ መሞከርና ድርጅቱን ለመከፋፈል ''ፈርጣጭ'' የሚል ስም መስጠታቸውን ጉባኤው አጥብቆ ይቃወማል:: በተጨማሪም ዛሬ በመኢሶን ላይ ደርገና አድርባይ ድርጅቶች ከድሃሪው ቢሮክራሲ ጋር በመተባበር የሚያካሂዱት ጭቆናና ጭፍጨፋ በኢት አብዮት ላይ ከሚደረገው የማንኛውም የፀረ—አብዮት ሴራ ነጥለን አንመለከተውም:: ''ፈርጣጭ'' የሚለው አፀያፊ ቃል ለዚህ አብዮታዊ ድርጅት የሚሰጥ መጠሪያ ሳይሆን የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራምና የተራማጆችን ሰፈር ለከፋ የቀኝ አድርባዮች ማለት ሰደድ፣ ወዝ፣ ማሌሪድ የሚሰጥ መጠሪያ ነው:: ስለሆነም ጉባኤያችን ለዚህ የማሌ ድርጅት ቃለ ተሃድሶውን እንደገና በማክበር:—

— የዚህ ድርጅት አባላት ወይም ደጋፊዎች ናቸው ተብለው በሚጠረጠሩት ወዝአደሮች፣ አርሶ አደሮች፣ ተራማጅ ሴቶች፣ መለዮ ለባሾችና ወጣቶች ላይ የሚወሰደው ማንኛውም አሰቃቂ እርምጃ አሁኑኑ እንዲቆም፣

— በስር ቤት የሚሰቃዩት የዚህ ድርጅት አባላትና ደጋፊዎች በስቸኳይ አሁኑኑ እንዲለቀቁ፣





— መኢሶን ያቀረባቸው አብዮታዊ ጥያቄዎች በሙሉ በተግባር እንዲተረጎሙ፣

— የድርጅቱ አባላትና ደጋፊዎች መገደል ተጠያቂ የሆኑትን ካለምንም ርህራሄ ለፍርድ በስቸኳይ እንዲቀርቡ ጉባኤያችን አጥብቆ ይጠይቃል ለዚህም ይታገላል::

## ሰ ሰ ኢ ቤ አ ን

ሴቶች የህብረተሰቡ አንድ አካል ቢሆኑም በፊውዳል ስርዓተ ማህበር ውስጥ ድርብ ጭቆና እንደደረሰባቸውና አሁንም እንዳልተላቀቁ ግልጽ ነው:: ከዚህም የተነሣ ሳብዮቱ ያደረጉት አስተዋጽኦ ዝቅተኛ ነው:: ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ከግቡ ለማድረስ የሴቶች ሙሉ ተሳትፎ አስፈላጊ መሆኑን እሙን ነው:: ይህንን ሃቅ በመረዳትና በስራ ለመተርጐም በሚያዝያ 1969 ዓ ም የወጣውን የኢሴአን የኢትዮጵያ ሴቶች አብዮታዊ ንቅናቄ ፕሮግራም ተራማጅነትና በልሣኑ ታጋይ ኢትዮጵያዊት አማካኝነት በጊዜያዊው አንገብጋቢ ጥያቄ የምትሰጣቸውን ትንተናዎች ትክክለኛነትን በመገንዘብ ማህበራችን ለዚሁ ንቅናቄ ያልተቆጠበ ድጋፉን ይሰጣል:: አሁን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በንቅናቄው መሪነት የሚጠረጠሩና በሌሎች ታጋይ ሴቶች ወጣቶች ላይ የሚደረገው ዘመቻና ኢሰብአዊ ማሰቃየት ጉባኤያችን ያወግዛል:: ስለሆነም:—

— የድርጅቱ መሪዎችና አባላት በስቸኳይ እንዲፈቱና ድርጅቱ በጠየቀው መሰረት በማደራጀት በነበሩበት ቦታ ላይ እንዲመለሱና የማሰደድ ድርጊት በስቸኳይ እንዲቆም ጉባኤያችን አጥብቆ ይጠይቃል፣

— ዛሬ ደርግ በተራማጅ ሴቶች ላይ የሚያደርገውን እስራት፣ ግድያና ኢሰብአዊ ማሰቃየት በፍጥነት እንዲቆም፣ ለሚደረገው ትግል ሃቀኛ ተራማጆችና የሰፊው ህዝብ ወገኖች የሆኑ ሁሉ ትግላቸውን እንዲያፋፍሙ ጉባኤያችን አብዮታዊ ጥሪ ያደርጋል::

## ሰ ሰ ኢ አ ወ ን

ኢ አ ወ ን የኢት አብዮታዊ ወጣቶች ንቅናቄ ዛሬ ወጣቱን ኃይል በአብዮት ሠፈር እንዲሰማራ ለማድረግ የጣረና የሚጥር ግንባር ቀደም ድርጅት ነው:: ይህ ድርጅት የኢት አብዮት አቅጣጫውን ሳይስት በተያዘው የነፃነት ጎዳና ላይ ተጉዞ የመጨረሻ ድሉን እንዲቀዳጅ ልሳኑን ''የአብዮት ፋና'' መውጣት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ የታገለ የሚታገል ድርጅት ነው::

እንዲሁም ትሳንትና በአገራችን ወጣት ሁሉ በጅምላ እንደ አብዮታዊ የሚቆጠርበትን የተሳሳተ እምነት ሰብሮ በወጣቶም መሐከል የመደብ ትግል እንደአለና ወጣት በአጠቃላይ ተራማጅ

እንዳልሆነ በገሃድ አሳይቷል:: ይህ የወጣት ንቅናቄ ትናንት በኢህአፖ ቁጥጥር ሥር የነበ
ረውንም ወጣት ዛሬ ወደ አብዮታዊ ሠፈር ለመቀላቀል የቻለው በከፍተኛ የርእዮተ ዓለም ትግል
እንደሆነ ማህበራችን ያምናል:: ከኢ አ ወ ን ፕሮግራም እንደምንረዳው ኢ አ ወ ን የመከበ
ወጣት ድርጅት ነው:: መ ኢ ሶ ን በኢት አብዮት ውስጥ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት አንጋፋ ማር
ክሳዊ ሌኒናዊ ድርጅት በመሆኑና ወጣት ንቅናቄውም ከርሱ ነጥሎ ስለማናየውና የ መ ኢ ሶ
ን የፖለቲካ አቋም በመያዝ በተለየ መስክ የሚታገል ድርጅት ስለሆነ ጉባኤያችን ሙሉ ድጋፉን
ይሰጠዋል:: ከ ኢ አ ወ ን ጎን ቆሞ ይታገላል::

## ስለ ብሔረሰብ ጥያቄ

ማህበራችን ከዚህ በፊት ደጋግሞ እንደገለጸው በኢት ውስጥ የሚገኙትን ጭቁን ብሄረሰቦ
በሙሉ የራሳቸው እድል በራሳቸው የመወሰን እስከ መገንጠል ድረስ ያላቸውን መብት ያውቃል::
በዚህ መሠረት ይህ መብት እንዲታወቅና በብሔረሰቦች መሃከል በእኩልነትና በወንድማማችነት የተ
መሠረተ አንድነት እንዲፈጠር ከሚታገሉ ሃቀኛ ማርክሲስት ሌኒኒስቶችና ተራማጅ የብሄረሰብ ንቅ
ናቄዎች ጎን በመሰለፍ ይታገላል:: በሌላ ወገን ዛሬ በኢት ውስጥ የሚገኘው የብሔረሰብ ጥያ
ቄ ዲሞክራሲያዊና ሰላማዊ መፍትሄ እንዲያገኝ ይታገላል:: በአንጻሩ በአሁኑ ጊዜ ደርግና
አድርባዮች ከአድሃሪው ቢሮክራሲ ጋር በግብር በመተባበር በተለይም በደቡብ በሚገኙ ጭቁን ብሄ
ረሰቦች ላይ በብሄር ግንኩህሉኝነት የሚያካሄዱትን ጭፍጨፋ ይህ ጉባኤ አጥብቆ ያወግዛል::
ዛሬ ደርግ በሚከተለው የቀኝ አድርባይነት መስመር የተነሳ በሰሜንና በደቡብ የሚገኙ ጭቁን
ብሄረሰቦች አብዮታዊ ተሳትፎ ከምን ጊዜውም የበለጠ እየቀነሰ በመሄድ ላይ ይገኛል:: ነፍጠ
ኞች እንደገና በማንሰራራት በጭቁን አርሶ አደሮች ላይ ይህ ነው የማይባል ጭፍጨፋ ያካሄዳሉ፣
የህዝብ ድርጅቶች በመፈረረስ ላይ ናቸው:: ካድሬዎች ይታሰራሉ፣ ይጨፈጨፋሉ:: ይህ ሁኔታ
በዚህ ከቀጠለ በገብር የቅልበሳ ሃይሎችን ስለሚረዳና ስለሚያጠናክር ባሁኑ ጊዜ በነዚህ አካባ
ቢዎች የሚካሄደው በብሄር ትምክህተኝነት ላይ የተመሠረተ ጭፍጨፋ በአስቸኳይ ቆሞ በዚህ ሥፍራ
የሚገኙ ጭቁን ብሄረሰቦች እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ መብታቸው ታውቆና ተከብሮ በአብዮቱ ውስጥ
ሙሉ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ለዚህ የሚያበቋቸው የዲሞክራሲ መብቶች በአስቸኳይ መለቀቅ አለባቸው፣
ህዝቡን ለማንቃት፣ ለማደራጀትና ለማስታጠቅ የሚደረገው ትግል መፋፋም አለበት:: ከጭቁን
ብሄረሰብ በመጡ ካድሬዎች ላይና በሃቀኛ ተራማጆች ላይ የሚካሄደው ክትትል፣ እስራትና ግድያ
አሁኑኑ መቆም አለበት:: አብዮቱን ለመቀልበስ ሌት ተቀን በሚታገለው አድሃሪ ቢሮክራሲ እን
ዲደመሰስ የሚደረገው ትግል መፋፋም ይኖርበታል::

## ለሠራዊቱ ጥሪ

— አድርባይ ድርጅቶች ከአድሃሪው ቢሮክራሲ ጋር በመተባበር የሚያካሄዱትን ጭፍጨፋና
እሥራት ማሰቃየት በአስቸኳይ እንዲቆም::





— ጭቁኑ ህዝብ በአብዮቱ ውስጥ ሙሉ ተሳትፎ እንዲያደርግ የወዝአደር ፓርቲውን
ህዝባዊ አብዮታዊ ግንባሩንና፣ አብዮታዊ ሠራዊትን ለማቋቋም የሚደረገውን ትግል
በይበልጥ ለማፋጠን ለጭቁን ህዝብ የዲሞክራሲ መብቶች ያለገደብ አሁኑኑ እንዲለ
ቀቁ::

— የውጭ እርዳታ ለትግሉ አጋዥ እንጂ ወሳኝ ባለመሆኑ የውጭ እርዳታን በተቀዳሚ
በመውሰድ የብሔራዊ ነፃነታችንን ሊያስደፍር የሚችል መሆኑን በመገንዘብ ዛሬ ከአ
ብዮቱ ሰፊ ጭቁን ህዝብ ይልቅ በውጭ እርዳታ በተቀዳሚ ለመውሰድ የሚደረገውን ማን
ኛውንም ዓይነት ጥረት እንዲቆም::

— ዛሬ በኤርትራ ያለውን ችግር በሰላማዊ ይልቅ በጦር ለመፍታት የሚደረገው ጥረት
በኤርትሬ ጭቁኖችና በኢት ጭቁኖች መሐከል ከንቱ የደም መፋሰስ ስለሚያስከትል
በዚህ የጦር መፍትሔ በተቀዳሚ የፖለቲካ መፍትሔ እንዲገኝለት ጥረት እንዲደረግ::

— ጭቁኑ መለዮ ለባሽና ህዝባዊ ሠራዊት አሁን በዘመተበት በሰሜንና በደቡብ ምሥራቅ
የደረሰው ከንቱ የደም መፍሰስ ያስከተለው የአድሃሪው ቢሮክራሲ አመራርና አሸጥ
ሮች በመሆኑ ዘመቻው የተፈለገውን ውጤት እንዲሰጥ አብዮታዊ አመራር እንዲኖረው፣
መደበኛ ጦሩና ህዝባዊ ሠራዊቱ አብዮቱንና አገሩን ዳር ድንበር ለመጠበቅ ለጭቁኑ
ህዝብ የብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮትን ፕሮግራም በሥራ ላይ በማዋል በገባው ቃል
ኪዳን መሠረት ከዚህ በላይ የጠቀስናቸው ጥያቄዎች በሥራ ላይ እንዲውሉ የሚደረ
ገውን ትግል እንዲያፋፍሙ ጉባኤያችን አብዮታዊ ጥሪውን ያቀርባል::

## ስለ ሱማሌ

አድሃሪው የሱማሌ መንግሥት ‘‘የታላቋን ሱማሌ’’ እቅድ በሥራ ላይ ለማዋልና ኢምፔሪያ
ሊስቶች አብዮታችንን ለመቀልበስ በአደረጉት ከበባ ተባባሪ በመሆን ኢት ከመቸውም ጊዜ በውስ
ጥና በውጭ ጠላቶች ተወጥራ የምትገኝበትን አመች ጊዜ በመምረጥ ከኢት ግዛት አንድ አራተኛውን
በራሱ ግዛት ለማጠቃለል በአፍሪካ አንድነት ድርጅት የጸደቀትን ስምምነቶችና በተባበሩት መንግ
ሥታት የሰፈሩትን ውሎች በመጣስ የኢት ወሰንና ህልውና በመድፈር በደቡብ ምሥራቅ ኢት ወረራ
ማካሄዱ ይታወቃል:: በዚህ ወረራ ሳቢያ በካባቢው ጭቁን ብሔረሰቦች ላይ ከፍተኛ የደም መፋ
ሰስ እንደደረሰ፣ የህዝብ ድርጅቶች እንደፈረሱ ይታወቃል:: በሌላ ወገን ይህን አድሃሪ ወረ
ራ ለመቋቋም ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት በቢሮክራሲው አመራር ስር የተጠቀመበት ወታደራዊ መፍ
ትሄ ያስከተለው ትምክህተኝነት በዚህ አካባቢ የሚገኙትን ነፍጠኞች በማጠናከርና የካባቢውን
ጭቁን ብሔረሰቦች አብዮታዊ ተሳትፎ በማዳከም በአብዮቱ ላይ ይህ ነው የማይባል ጉዳቶች ሊደ
ርሱ ችለዋል:: ስለሆነም ማህበራችን:—

— የሱማሌ መንግሥት ወረራና የመስፋፋት ፖሊሲ አጥብቆ አያወገዝ፣ ለሱማሌ ህዝቦች ይህንን አድሃሪ ወረራ አውግዘው ከኢት ጋር የመልካም ጉርብትና እንዲመሠረት ጥረታችንን እንድናስተባብር ጥሪ ያደርግላቸዋል። በሌላ ወገን በዚህ አካባቢ የሚገኙትን ጭቁን ብሄረሰቦች በአብዮቱ ውስጥ ሙሉ ተሳትፎ እንዲያደርጉና የውስጥ ጠላቶቻቸውንና ወራሪዎችን እንዲቋቋሙ የብሄረሰብ መብታቸው መታወቅ አለበት። እንደማንኛውም የአብዮቱ ሃይሎች ለማንቃት፣ ለማደራጀትና ለማስታጠቅ የሚደረገው ትግል ማፋፋም ይኖርበታል።

ETHIOPIAN STUDENTS UNION
* EXECUTIVE COMITTEE *
IN FEDERAL REPUBLIC OF GERMANY



15/05/78

**ከኤፕሪል 29/04/78 እስከ ሜይ 1/05/78 በቤልግሬድ ከተማ በዩጎዝላቪያ ቀ/ማህበር አዘጋጅነት የሩማንያ፣ የሐንጋሪና የዩጎዝላቪያ ቀ/ማህበራት በደረጉት ሲሚናር ላይ ያስተላለፉት የፖለቲካ ው ሳ ኔ።**

**መ ግ ቢ ያ፦**

ህብረተሰብ በመደቦች መከፋፈል ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በጨቋኝና በተጨቋኝ መደቦች መካከል ከባድ መራራና የከረረ ትግል ይካሄድ እንደነበር፣ አሁንም በመካሄድ ላይ እንደሆነ ይኸም ትግል ወደሬት መደብ አልባ ህብረተሰብ እስኪመሠረት ድረስ እንደሚቀጥል የተረጋገጠ ሳይንሳዊ ሐቅ ነው። የዓለም ህዝቦች ለፍትህ፣ ለነፃነትና ለእኩልነት ከጨቋኝ መደቦች ጋር የሚያካሂዱት አብዮታዊ ትግል በአሁኑ ሰዓት ከምን ጊዜውም የበለጠ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል። ጭቁን ህዝቦች ከቀንደኛ ጠላታቸው ከአለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም በተለይም ከአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ጋር በሚያደርጉት ትግል በየጊዜውና በየቦታው አዳዲስ ድሎችን እየተቀዳጁ ናቸው።

የሦስተኛ ዓለም ጭቁን ህዝቦች ከቀጥተኛ ቅኝ አገዛዝ ከእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ፣ ከብዝበዛ ነፃ ለመውጣት የሚያደርጉት ትግል ድልን እየተቀዳጀ መምጣቱ አለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝምን ሳያርበተብተው እንዳልቀረ አይካድም። የቻይና፣ የቬየትናም፣ የካምቦዲያ፣ የኮሪያ፣ የአንጎላ ህዝቦች ታሪካዊ ድሎች ለዚሁ ምሥክር ናቸው።

የጊዜውንና የአካባቢውን ሁኔታ በማብሰልሰል ጭቁን ህዝቦችን አፍና በበሰበሰ ሥርአት ውስጥ አንጋሎ ለመበዝበዝ ኢምፔሪያሊዝም ረቂቅ ዘዴዎችን መጠቀም ቢጀምርም በያሰበት አየተጋሰጠና በጽኑ እየተመታ ሄደ እንጂ የጭቆናችን ትግል አልገታውም። ጽኑ የህብረተሰብ መመሪያቸውን በወዝ አደሩ አብዮታዊ መድረክ ላይ ያሰፈሩ የተራማጅ መንግሥታት ቁጥር በየጊዜው መጨመር ለዚሁ በቂ ማስረጃ ነው፣ ቢሆንም የዓለም ጭቁን ህዝቦች በጊዜያዊ ድል በይሞኙ ነቀምነው ካልጠበቁ የሐገር ውስጥ ፀረ—አብዮት ሐይሎችን አስተባባሪ የሆነው ኢምፔሪያሊዝም ፀረ ህዝብ ጥቃቱን እንደማያዳክም የተረጋገጠ ነው፣ አስትንፋስ ህይወቱ የጭቁን ህዝቦች ደም ነውና

ሐገራችን ኢት ከፊል ፊውዳል ከፊል ከበርቴ ሥርአት የሰፈነበት አገር እንደመሆኗ ህዝቦቿን ከዚህ አስቃቂ ሥርአት ሊያላቅቅ የሚችለው ሰውየ ዋና ጠላቶቿን ማለትም ፊውዳሊ

ዝምን፣ ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን ሊደመስስ የሚችል መሠረታዊ ለውጥ ብቻ
ነው፡፡ ስለሆነም በኢትዮጵያችን ውስጥ ሥርጉውን ሥርአት ደምስሶ በአዲስና በታዳጊ ሥርአ
ለመተካት የሚያስችለው ብቸኛ ጉዳይ የሰፊውን ህዝብ ዋና ጠላቶች በማያዳግም ሁኔታ ሊደመስ
የሚችለው <u>የአዲሱ ዲሞክራቲክ አብዮት</u> መባከት ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም ሰፊውን የኢት ህዝብ
ወዝአደሩን፣ አርሶአደሩን፣አብዮታዊ ወጣቶችን፣ ጭቁን ሴቶችን፣ መለዮ ለባሹን፣ ምሁሩን በን
ቃል ሐቀኛ ተራማጆችን የሚያቅፈው ፀረ-ፊውዳል፣ ፀረ-ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊስት፣ ፀረ-ኢምፔሪ
ሊስት አብዮት ግቡን ሲመታ ብቻ ነው፡፡

## <u>ስ ለ ጊ ወ አ ደ ር ን</u>

ደርግ በመደብ ይዘቱ የንዑስ ከበርቴውን የመደብ ጠባይ የሚያንፀባርቅ ነው፡፡ አ
ዱም ከሰፊው ህዝብ በሌላው ወቅት ደግሞ ከፀረ-ህዝብ ሀይሎች ጉን በመሰለፍ የንዑስ ከበር
ውን መደበኛ ጠባይ ማለትም ወላዋይነትን ሥልጣን ላይ ከወጣ ጀምሮ በገቢር አያሣየ ነው፡፡
በአብዮቱ ውስጥ የተጫወተው ሚና ከፍተኛ ቢሆንም በፀረ-ዲሞክራቲክነቱ በአሁኑ ጊዜ ከምን
ጊዜውም በበለጠ የአብዮቱ እንቅፋት ሆኗል፡፡

በማንኛውም የአብዮት ትግል ወቅት የአብዮቱ መገፋትና የመደቦች ትግል መፋፋም እስ
ተወሰነ ደረጃ ድረስ ተራማጅ ሚና የተጫወቱ ድርጅቶችም ሆኑ ግለሰቦች እንዲጠነክሩ ወይ
ብዮት ወይ በፀረ-አብዮት ሠፈር እንዲቆሙ ያስገድዳቸዋል፡፡

ደርግም በቢሮክራሲ ጥያቄ፣ በዲሞክራሲ ጥያቄ፣ በብሔረሰቦች ጥያቄ፣ በውጭ እርዳታ
በትጥቅ ጥያቄና ህዝባዊ ሠራዊቱ ላይ በወሰደው ወላዋይ አቋም ምክንያት ወደ ፀረ-አብዮት
ካምፕ እየተሸቀለቀለ ነው፡፡ የወዛደሩ መለስተኛ ፕሮግራም የሆነውን የአዲሱ ዲሞክራሲ
አብዮት ፕሮግራም ''ፕሮግራሜ'' ነው ብሎ ከተቀበለ በኋላ በቃል እንጂ በገቢር ከዶታል፡
በአዲስ ፕሮግራም በማያሻማ ሁኔታ በጊዜያዊ አጣዳፊ ተግባሮች ሥር የሰፈረውን የዲሞክራሲያ
መብቶችን መለቀቅ ጥያቄ ፍፁም ከዶታል፡፡ በብሔር ትምክህተኝነት በመቀጥ፣ የዲሞክራሲ መ
ቶችን በማፈን ከጠነበው ቢሮክራሲ ጋር አጅና ጓንቴ በመሆን ብሔረሰቦች ለዲሞክራሲ የሚያደ
ጉትን ትግል በኃይል ለማዳፈን የተቻለውን ሁሉ በማድረግ ላይ ነው፡፡ የውጭ እርዳታን በ
መለከተው በኩል በሰፊው ህዝብ ከመተማመን ይልቅ በቢሮክራሲውና በውጭ እርዳታ በመተማመኑና
እርዳታን እንደ <u>ወሰኝ</u> አድርጉ በመቆጠር በአብዮቱና በኢት ብሔራዊ ነፃነት ላይ ከፍተኛ አ
ጋ በማድረግ ላይ ነው፡፡

አዲስ ፕሮግራምን በተግባር ለመቲጉም የሞትና የሽረት ትግል በሚያደርጉ አብዮታው
ያን፣ የቀበሌ ማህበራት፣ የገበሬ ማህበራት፣ የሴቶች ማህበራት፣ የወዛደሩ ማህበርና የወጣ





ቶች ማህበራት፣ መሪዎችና አባሎች እንዲሁም ሀገር ወዳጆችን በመረሸን፣ በማሠርና የፀረ-
ህዝብ ዘመቻውን ከምንጊዜውም በበለጠ በማፋፋም ላይ ይገኛል፡፡

በነዚህ አብዮቱ በወለዳቸው ሐቀኛ ተራማጆችና የህዝባዊ ድርጅቶች መሪዎች መገደልና መ
መታጠር ተጠያቂው ሥልጣኑን የያዘው አድሐሪው የደርግ ቀኝ ክንፍ ነው እንላለን፣ ይህንን ፀረ
ህዝብ ድርጊት ሲሜናፉ አያወግዝ በደርግ ውስጥ ያሉ ተራማጆች በዚህ አድሐሪ ክንፍ ላይ ቆራጥ
የሆነ አብዮታዊ እርምጃ እንዲወስዱ ይጠይቃል፣ አብሮአቸውም ይታገላል፡፡

በወህኒ ቤት የታጐሩት ሐቀኛ ተራማጆች፣ የገበሬ፣ የሠራተኛ፣ የቀበሌ፣የሴቶችና የወ
ጣቶች ማህበራት መሪዎችና አባላት እንዲሁም ጭቁን ወታደሮች፣ተራማጅ መኰንኖች ሀገር ወዳጆችና
ዲሞክራቶች <u>አሁኑኑ</u> እንዲፈቱ እየጠየቀ ለዚህም እስከመጨረሻው በቆራጥነት እንደሚታገል ያረጋ
ግጣል፡፡

## <u>ስ ለ ቢ ሮ ክ ራ ሲ ው</u>

ከፊውዳ ቡርዣው ሥርአት የተወረሰውና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር በሺህ ድሮች የተሣሠረው
አድሐሪ ቢሮክራሲ እስከአሁን ድረስ የሰፊው ህዝብ አብዮታዊ ብትር አላረፈበትም፣ እንዲያውም
የሰፊውን ህዝብ አብዮታዊ እንቅስቃሴ አፍኖ የያዘ መቆቅር መሆኑ የማይታበል ሐቅ ነው፡፡
ይህ ቢሮክራሲ ፍፁም አድሐሪ ከመሆኑም የተነሳ ለማንኛውም ፀረ-አብዮታዊ ሴራና ለመፈንቀለ
መንግሥት ሙከራ አመቺ መሣሪያ ነው፡፡ የፀረ-አብዮት ሤራዎችም ከተሰኩለት ኢት ውስጥ
ሊመሠረት ለሚችለው ፋሺስታዊ ሥርዓት ተሸካሚ እንደሚሆን ባይታለም የተፈታ ነው፡፡

ይህ አድሐሪ ቢሮክራሲ ቀንደኛ የህዝብ ጠላት ከመሆኑ የተነሳ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ
ለፀረ-አብዮት ኃይሎች ተገን በመሆን በአብዮታችን ላይ ከፍተኛ አሻጥሮችን እየፈፀመ ነው፡፡
በቅርብ ጊዜ አድሐሪ የደርግ አባሎች በቢሮክራሲው ውስጥ የተሰገሰጉ ወጣት ነፍጠኞች እንዲ
ሁም ለሥልጣን የቋመጡ አድርባይ ድርጅቶች ''ቢሮክራሲው የጥገና ለውጥ ይደረግለት፣ ለአብ
ዮቱ ጠቅሟል፣ ''<u>ቢሮክራሲ ይውደም አሁኑኑ</u>'' የሚሉ ገራ ቀደዎች ናቸው''ወዘተ የሚል
ፍፁም ኢሳይንሳዊ የሆነ የፀረ-አብዮት ፕሮፖጋንዳ መንዛት እንደጀመሩ የታወቀ ነው፡፡

የኢት ሐቀኛ ተራማጆች ይህን ፀረ-አብዮታዊ ፕሮፖጋንዳ በማጋለጥ ቢሮክራሲው እንዲ
መታና የሰፊው ህዝብ እንዲጠናከር፣ ትግሉ እንዲፋፋም ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አለባቸው፡፡

ቢሮክራሲው እንዲሞታና እንዲወድም የሚደረገው ትግል ለዲሞክራሲ መብቶች መለቀቅ ከሚደረገው ትግል ተነጥሎ ስለማይታይ ተራማጅ ነን የሚሉ ድርጅቶችም ሆነ ግለሰቦች በዚሁ አንፃር የሚኖራቸው አቋም ተራማጅነታቸውን ይወስነዋል እንላለን::

## የ ዲ ሞ ክ ራ ሲ መ ብ ቶ ች ጥ ያ ቄ

የኢት አብዮት ወደፊት እንዲገፋና ለመጨረሻውም ፍጻሜያ በማያጠራጥር ሁኔታ እንዲ ጋጅ ከተፈለገ የሰፊው ህዝብ የንቃት፣ የድርጅትና የትጥቅ ደረጃ በተፋጠነ ሁኔታ ማደግ አለ ርበታል:: አብዮቱ በሚያስተማምን ሁኔታ ድሉን እንዲቀዳጅ ከተፈለገ ሰፊው ህዝብ እንደ አንድ ሰው ሆኖ በጠላቶች ሳይ መነሳት ይኖርበታል:: የዚህም ወሳኝ ትግል ቁልፍ ጥያቄ የዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ አሁኑኑ የመለቀቅ ጥያቄ ነው::

ሁላችንም እንደምናውቀው የዚህን ጥያቄ አስፈላጊነት ኢ ወ መ የአዲሱን ፕሮግራም ሲቀበል ተቀብሎት ነበር፣ ከዚያም የአለማየሁ፣ ተፈሪ መፈንቅለ መንግሥት ሲከሽፍ ደርጉ በአሁኑ ሊቀመንበር አማካይነት በአብዮት አደባባይ ይህ ጥያቄ በአስቸኳይ መፈታት እንዳለበ በይፋ ለሰፊው ህዝብ አረጋግጦ ነበር:: አምስቱ ማሌ ድርጅቶችም ህብረት ቢመሠርቱ በወ ት የጋራ መግለጫ ሳይ ቁልጭ ባለ ሁኔታ አስቀምጠውት ነበር፣ ነገር ግን የኢት አብዮት ት እየገፋ መጥቶ ከፍተኛ ደረጃ ሳይ በመድረሱ የመደብ መሸጋሸግ ሆነና ደርግም በዚህ ጥ ሳይ ፍፁም ፀረ—ዲሞክራቲክ አቋሙን አሳየ:: ከአምስቱ ማሌ ድርጅቶችም ሦስቱ (ወዝ፣ ሰ ና ማሌሪድ) በዚህ ጥያቄ ሳይ የነበራቸውን አቋም በመሳብ በአድርባይነት ውስጥ ተዘፍቀው ለቆመለት መደብ የሚያገለግል ከሳሽና በራዥ አቋማቸውን እያስተጋቡ ናቸው:: በዚህ ብ ተወስነው አልቀሩም በዚህ ጥያቄ ሳይ በአቋማቸው በፀኑት ጠቀኛ ተራማጆችና ድርጅቶች ማለ እንደ መኢሶንና ኢጭአት ባሉት ሳይ በደርግ ግንባር ቀደምትነት በአድሐሪው ቢሮክራሲና የፊ ውዓል ርዝራዦች ተባባሪነት፣ በከሐዲያች ጠቋሚነት ከፍተኛና ኢሰብአዊ የሆነ ጭቆናና ጭፍ እያደረጉ ነው:: በነዚህ ድርጅቶች በተለይም በመኢሶን አባልነትና ደጋፊነት የሚጠረጠ ግለሰቦች በየጊዜው፣ በየቦታው እየተረሸኑ፣ በወህኒ ቤት እየታጎሩ፣ እየታደኑና እየተሰደ ናቸው:: ወንጀላቸው ያው አላይ እንደገለጽነው የገበያውን ሁኔታ አይተው አቋማቸውን አለ ለወጣቸው ብቻ ነው::

የዚህ ቁልፍ ጥያቄ በአስቸኳይ አለመመለስ አድሐሪ ኃይሎች ከምን ጊዜውም በበለ እንዲጠናከሩና ሀይላቸውን አስተባብረው አብዮታችንን እንዲፈታተኑ አድርጓቸዋል፣ ሴሚናሩ ይህን ሁኔታ በሚገባ ከመረመረ በኋላ:—



ሀ) ተባብሮ አብዮታችንን የሚፈታተነውን ምድሬ አድሐሪ ለመደቆስ ሰፊው ህዝብ በበለጠ ንቅናቄና ተደራጅቶ የአመጽ ትግልን ማፋፋም እንዳለበትና በዚህም አብዮታዊ ድርጊት በአሸናፊነት ለመውጣት የዲሞክራሲ መብቶች ጥያቄ በአስቸኳይ መፈታት እንዳለበት በመገንዘብ፣

ለ) ይህንንም አብዮታዊ አመጽ የሚመራ ጠቀኛ የወዝ አደር ፓርቲ (ፓርቲ እንፈጥራለን ብለው አሁን ሸር ጉድ የሚሉትን የነውስ ከበርቴ ጥርቅም የሆነ ፓርቲ ሳይሆን) መመሥረት እንዳለበት በመመልከት::

ሐ) አድሐሪውን ቢሮክራሲ በህዝባዊ አስተዳደር ለመተካት ለሚደረገው ትግል ህዝቡን ለማዘጋጀትና ነፃ እርምጃውንም አብዮታዊ ጥራት ለመስጠትና እንዲሁም የህዝቡን ነፃ እርምጃ (ቀይ ሽብር) በበለጠ ለማፋፋም፣

መ) የኢትን አብዮት ወጥረው ከያዙት አንዱ የብሔረሰብ ጥያቄ በትክክለኛው መንገድ ለመፍታት የዲሞክራሲ መብቶች እጅግ በጣም አስፈላጊ መሆናቸውን በማመን፣

''የዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ አሁኑኑ'' ብለው ከሚታገሉ ድርጅቶች፣ ተራማጅ የብሔረሰብ እንቅስቃሴዎችና ተራማጅ ግለሰቦች ጎን በመሰለፍ እስከ መጨረሻው የሚታገል መሆኑን አረጋገጠ፣ በዚህ አቋማቸው ምክንያት ጭቆናና ግፍ የሚያደርሱባቸውን ማንኛውንም ኃይሎች/በጥብቅ ያወግዛል፣ ያለርህራሄም ይታገላቸዋል፣ ያጋልጣቸዋል!! የዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ አሁኑኑ ለሚለው አብዮታዊ መፈክር በቆራጥነት በመታገላቸው በወህኒ ቤት የተጣሉት ጠቀኛ ተራማጆች፣ ጭቁን ቢሮች፣ ወጣቶች፣ ጭቁን ወታደሮች፣ አርሶ አደሮች፣ ወዝ አደሮች፣ የቀበሌ ማህበራት መሪዎች፣ ሐገር ወዳጆችና ዲሞክራቶች በአስቸኳይ እንዲለቀቁ አጥብቆ ይጠይቃል፣ ለዚህም እስከመጨረሻው ይታገላል::

## የ ብ ሔ ረ ሰ ብ ጥ ያ ቄ

ኢት የብዙ ብሔረ ሰቦች ሐገር እንደመሆኗ መጠን በነበረው ሥርአት አንዱ ጨቋኝ ሌሎቹ ተጨቋኝ በመሆን የብሔረ ሰቦች እሥር ቤት እንደነበረች ለማንም ግልጽ ነው:: ስለ ዚሁም የመደብ ትግላችንን ለማፋፋም የዚህ ጥያቄ መፈታት ለአብዮታችን ከፍተኛ ቀልቱና ነው እንላለን::

ደርግ ከነበረው ጭፍን የሸበኒነት አ[illegible] በጠቀኛ ተራማጆች ትግል አንዱ እርምጃ ረቀ ብሎ የጭቁን ብሔረሰቦችን የራስን እድል በራስ የመወሰን እስከ አተናሚ ቢያንስ

በወረቀት ደረጃ ቢያውቅም እንኳን በውስጡ በተሰገሰጉት ወጣት ነፍጠኞች፣ በቢሮክራሲውና በአድርባዮች አስተባባሪነት የብሔር ትምክህተኝነትን በይበልጥ አፋፍሟል፡፡ የጭቆን ብሔረ ሰቦችንም እንቅስቃሴ በወታደራዊ ኃይል ለማፈን ከፍተኛ ጥረት እያደረገ ነው፡፡ ሲሚናሩ ይህን በመመርመር ጭቆን ብሔረ ሰቦች ለሰላም፣ ለዲሞክራሲ፣ ለእኩልነትና ለነፃነት ያደረጉትንና የሚያደርጉትን ከፍተኛ ተጋድሎ ሙሉ በሙሉ እየደገፈ በማርክሲዝም ሌኒንዝም መርህ መሠ ረት የራሳቸውን እድል በራሳቸው የመወሰን እስከ መገንጠል ድረስ ያለውን መብታቸውን እንዲገ ናፀፉ አቋብቶ እየታገለ:—

ሀ) የኤርትራ ጭቆን ህዝቦች ችግር በሰላም በፖለቲካ ከመፍታት ይልቅ በወታደራዊ የበላይነት ብቻ ለመጨረስ የሚያደርገውን የደርግን አዝማሚያ እያጋለጠ፣ በአን ጻሩም የኤርትራን ጭቆን ህዝቦች ትግል ከቀሩት የኢት ጭቆን ህዝቦች ትግል ጋር እንዳይጣመድ የሚታገሉትን የኢምፔሪያሊስትና የአድሐሪ አረብ መንግሥታት አፈ ቀላጤ የሆኑትን አድሐሪ ተገንጣይ ቡድኖች በጥብቅ ያወግዛል፡፡ ችግሩ በሰላ እንዲፈታ የኤርትራ ተራማጆችና የቀሩት የኢት ተራማጆች ትግሳቸውን እንዲያስተ ብሩ አብዮታዊ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

ለ) በአዲሱ ዲሞክራቲክ አብዮት መሠረት የብሔር እንቅስቃሴው ከመደብ ትግሉ ጋር እንዲፋፋም ብሔረ ሰቦቻቸውን ለመደብ ትግል ለማዘጋጀትና በዲሞክራቲክ አብዮት ውስጥ ለመሰተፍ የሚታገሉትን የአፋር ብሔራዊ ነፃ አወጪ ንቅናቄ(አብነግ)፣ የኦሮሞ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ(ኦብዲን)፣ የአዲያ ብሔረ ሰብ ዲሞክራሲያ ንቅናቄ(ኦብሰዲን)...ወዘተ ሲሚናሩ ሙሉ ድጋፉን እየሰጠ ከጐናቸው ቆሞ እንደሚ ታገል በድጋሚ ያረጋግጣል፡፡

ሐ) የብሔረ ሰብ ጥያቄ ከዲሞክራሲ ጥያቄ ተነጥሎ የሚታይ ባለመሆኑ የጭቆን ብሔረ ሰቦች ጥያቄ በዲሞክራሲ መንገድ እንዲፈታ ለጭቆን ህዝቦች ዲሞክራሲ መብት እንዲሁም በጭቆን ብሔረ ሰቦች ሳይ ገደብ ሳያበጁ እስከ መገንጠል መብት የሚ ታገሉትን ሐቀኛ ተራማጆች (መኢሶንና ኢጭአት)አሁንም በበለጠ ገፋበት እያሰ ከጐናቸው መቆሙን በድጋሚ ያረጋግጣል፡፡

መ) አድርባይ ድርጅቶች (ሰደድ፣ ወዝ፣ ማሌሪድ) በሶቭል ሾቪኒስትነት በመወጠር ''ከሰአኛ ኩሚኒስት የሉም፣ የጭቆን ብሔረሰቦች ተራማጆች የሉም''በማለት የብሔረ ሰብ ጥያቄ መፍትሔው ሪጂናል ኦቶኖሚ ብቻ ነው''እያሉ ለማወናበድ የሚጥሩትን እያጋለጠ እነኝህን የብሔር ትምክህተኞች የነውስ ከበርቴ ጥር ቆሞ ቡድኖች ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ይታገላቸዋል፡፡



## ስ ለ አ ድ ር ባ ይ ድ ር ጅ ቶ ች

የአለም ጭቆን ህዝቦች አብዮታዊ ትግል እንደሚያስተምረን አንድ አብዮት በሚካሄድበት ወቅት አዳዲስ የእድገት ደረጃዎች ላይ በደረሰ ቁጥር በየጊዜው የኃይሎች መሸጋሸግ ይኖራል፡፡ አብዮቱ ሲጀምር አብረው የተነሱ ኃይሎች እስከመጨረሻው ገብ ድረስ አብረው እንደማይሄዱ ግልጽ ነው፡፡ የኢት አብዮትም በዚህ በአጭር እድሜው የመደብ መንሸራተት፣ መሸጋሸግን ደጋግሞ ታይቶበታል፣ በተለይም በአሁኑ ሰአት አድርባይነት በኢት አብዮት ውስጥ በጉልህ እየተንፀባረቀ ነው፡፡

አድርባዮች የወዛደሩን ንቅናቄ ለቡርዧው መደብ ጥቅም በማዋል የወዛደሩን ትግል ያጨናግፋሉ፡፡ አድርባዮች ፕሮግራማቸውን፣ ድርጅታቸውንና የትግል ዘዴአቸውን ለዚህ አሳማቸው እንዲያገዝ አድርገው ነው የሚነሱት፡፡ ስለዚህ ጉዳይ ሌኒን እንዲህ ይላል፡፡

''በፕሮግራም አድርባይነት ከታክቲክ አድርባይነትና ከድርጅት አድርባይነት ጋር በተፈጥሮ የተያያዘ ነው፡፡''

ሌኒን፣ አንድ እርምጃ ወደፊት፣ ሁለት እርምጃ ወደኋላ
ገጽ 293 ተራማጅ አታሚያች ሞስኮ 1970

ይህም በመሆኑ የተዘበረረቀ ፕሮግራም አውጥተው ቀንደኛ ቢሮክራቶችን፣ ትከቢተኛ ወጣት ነፍጠኞችንና ትናንት የደገፊው ንውስ ከበርቴ ቡድን (ኢህአፖ)አባላት የነበሩትን ፀረ—አብዮተኞች አገበስብሰው በየድርጅቶቻቸው አጉረው ከቁጠባ ሁኔታ ተነስቶ ለአብዮቱ የሚያስፈልገውን አብዮታዊ የትግል ዘዴ መቀየስ ሲገባቸው ሳያደርጉ፣ እንዲያውም በዚህ የትግል ዘዴ ላይ ትክክለኛና አብዮታዊ እርምጃ የሚወስዱትን ተራማጅ ድርጅቶች ለምሳሌ እንደ መኢሶን ያሉትን ''ፈርጣጭ''፣ ''ቀኝ መንገደኛ'' እያሉ፣የአብዮን ወደ እምቅ ልከከ እንደተባለው ለራሳቸው መሆን የሚገባውን ሥም በመስጠት ሐቀኛ ተራማጆችን ለማስመታት ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ ናቸው፡፡

እነዚህም ቀንደኛ አድርባዮች ማለት ወዝሊግ፣ ሰደድና ማሌሪድ ፀረ—አብዮታዊነታቸውን (በቢሮክራሲ፣ በዲሞክራሲ፣ በጭቁ አርዳታ፣ በብሔር ጥያቄ፣ በጦርነቱና በህብረቱ ሳይ ባሳቸው አቋም) በገቢር እያሳዩ በመሆናቸው ይህ ሲሚናር በጥብቅ ያወግዛቸዋል፡፡ በሐቀኛ ተራማጆች ላይ የሚያደርጉትን ጭፍና፣ ተጽእኖና ጠቀሳሳ ፀረ—አብዮት ሴራቸው በጥብቅ ይቃወማል፣ እስከ መጨረሻው ይታገላቸዋል፡፡ ስራው የኢት ህዝብም ቀበጥባጣውን የንውስ ከበርቴ ቡድን ኢህአፖን አንቅሮ እንደተፋው ሁሉ እነኝህንም አንባጓሮች ዱምጥማጣቸውን እንደሚያጠፋ ለአንዲት ደቂቃ እንኳን አንጠራጠርም፡፡

በእነዚህ ድርጅቶች ውስጥ ሳሉ ተራማጆች እነዚህን ድርጅቶች አብዮታዊ መስመር ለማስያዝ የሚያደርጉትን ትግል ከምንጊዜም በበለጠ እንዲያፋፍሙ አብዮታዊ ጥሪ ያደርግላቸዋል፡፡ ለዚህም ትግላቸው ከጎናቸው መቆሙን ያረጋግጥላቸዋል፡፡

## ስለ ሐቀኛ ተራማጆችና ስለ ኢማሌድህ

በአገራችን በመካሄድ ላይ ያለው የአዲሱ ዴሞክራቲክ አብዮት ቀንደኛ ጠላቶች ፊውዳሊዝም፣ ኢምፔሪያሊዝምና ቢሮክራቲክ ካፒታሊዝም ሲሆኑ አብዮቱ ግቡን ሊመታ የሚችለው ፀረ—ሶስቱ የሆኑ ኃይሎች በሙሉ በየፈርጃቸውና በየደረጃው ተደራጅተው በነቃ፣ በተደራጀና በታጠቀ የህዝብ አመጽ እነኝህን ጣምራ ጠላቶቻቸውን ሲደመስሱ ብቻ ነው፡፡

ባለፈው አመት አምስት ግሬ ድርጅቶች ህብረት ፈጥረው የአብዮቱን ይዘት ለማጣራትና ሂደቱን ለማፋጠንና መስመር ለማስያዝ ተነስተናል ባሉበት ጊዜ በአንድ ድምፅ ለዚሁ ተፈጥሮ ለነበረው ህብረት ሙሉ ድጋፍ ሰጥተን ነበር፡፡ እዚህ ላይ ''ትግላችን'' ቁጥር ሁለት 1969 በሰፊው እንጠቅስ:—

> ''አሁን የትግል ደረጃ የወዛደሩን ፓርቲ ለመፍጠር ከፍተኛ ጥረት የምናደርግበት በመሆኑም እነዚህ አምስት ድርጅቶች ለዚሁ ዓላማ በመተባበር የትግል አንድነታቸውን የሚያበስር መርሃ ግብር አውጥተዋል፡፡
>
> በኛ ግምት የአምስቱ ድርጅቶች መተባበር የወዛደሩን ፓርቲ ለመፍጠር በሚደረገው ትግል አንድ ከፍተኛ እርምጃ ነው፡፡ በኢት ህዝቦች የትግል ታሪክ ውስጥም ከፍተኛ ቦታ እንደሚይዝ አንጠራጠርም፡፡ ገጽ ሁለት

ህብረቱን የደገፍነው ከዚህ አብዮታዊ አቋማችን አንፃር ተመልክተነው ነበር፣ ነገር ግን ህብረት መስርተው ከነበሩት ድርጅቶች ሶስቱ [ወዝሊግ ሰደድና ማሌሪድ] በአጠቃላይ የተስማሙባቸውን አብዮታዊ ጥያቄዎች በመካድ መርሐ ግብሩን በድፍረት ለውጠው ህብረቱን በቢሮክራሲው ቁጥጥር ስር የሆነ የቀኝ አድርባዮች ጉረኖ አድርገውታል፡፡

ታዲያ እነሱ በፀረ—አብዮቱ ነፋስ ተውሽልሽለው ወደ ቀኝ ያጉበደቁ እንደሆነ እኛ ከአቋማችን ጋር በአብዮታዊ መሥመር ሆነን ወዝ፣ ሰደድና ማሌሪድ ''ኢማሌድህ'' ይጠንክር ''የወዛደሩ ፓርቲ በቶሎ ይመሥረት'' እያሉ ሽር ጉድ የሚሉበትን የአድርባዮች ''ህብረት'' ልንደግፍ አንችልም፣ እኛ የደገፍነው ህብረትና የአድርባዮች ህብረት ልዩነታቸው በሰማይና መሬት ነውና፡፡

ሴሚናሩ ይህን የአድርባዮች ''ህብረት'' እያወገዘ ሐቀኛ ተራማጆች ትክክለኛውን ኢማሌድህ ለመመሥረት የሚያደርጉትን ትግል እንዲያፋፍሙ አብዮታዊ ጥሪውን ያቀርባል፣





ለዚህም ትግላቸው ከጎናቸው የቆመ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

የአዲሱ ዴሞክራቲክ አብዮት ፕሮግራምን በተግባር ለማዋል ከሰፊው ህዝብ ጎን በመቆም ከአድሐሪያንና ከአድርባዮች ጋር የሞትና የሽረት ትግል ለሚያካሂዱት ለመኢሶን፣ ለኢጭአት፣ ለኢሲአን፣ ለኢአወን፣ ለአብዊን፣ ለአብነን፣ ለሀከሰዊን ለሌሎችም ሐቀኛ ተራማጆች ሙሉ ድጋፉን እየሰጠ አድርባዮችን ያለርህራሄ ይታገላቸዋል፣ ያጋልጣቸዋል

## ስለ ውጪ እርዳታ

በመሠረቱ የኢት አብዮት የአለም አቀፍ የጭቁን ህዝቦች አብዮት አካል ነውና የተራማጅ ኃይሎች የሞራልና የማቴሪያል እርዳታ ያስፈልገዋል፣ ነገር ግን ይህ እርዳታ ለአብዮታችን አጋዥ እንጂ ወሳኝ እንዳልሆነ የአብዮቱ ወሳኝ ኃይል ሰፊው ህዝብ እንደሆነ ሐቀኛ ተራማጆችም ሆኑ ማህበራችን ደጋግመው አስገንዝበዋል፡፡ ለአብዮታችን ድል መቀዳጀትና ለብሔራዊ ነፃነታችን ፍፁምነት ሙሉ ዋስትናው ሰፊው የኢት ህዝብ ብቻ ነው፣ ከዚህ የተለየ ሌላ መንገድ የሚታያቸው የውጪ እርዳታን በአብዮታችን ውስጥ የሚጫወተውን ሚና በአንጋፋነት ደረጃ በላይ አድርገው የሚገምቱ ፀረ—ዴሞክራቲክ ደርግንና የወጣላቸውን የቀኝ አድርባዮች [ወዝ፣ ሰደድ፣ ማሌሪድ] እንዲሁም እርዳታ በጭራሽ አያስፈልገም በማለት አብዮታችን ነጥለው ለማስመታት የሚታገሉትን የግራ አድርባዮች [የሲአይኤ ቅጥረኞች ኢህአፓና አረጥራጦች] ሴሚናሩ አጥብቆ ያወግዛል፣ በዚህ ጥያቄ ላይ ትክክለኛውን አቋም ይዘው ማለት ''ራስን በራስ መቻል''፣ ''እርዳታ አጋዥ እንጂ ወሳኝ አይደለም'' የሚለውን ሳይንሳዊ መፈክር አንግበው ከሚታገሉት ሀቀኛ ተራማጆች ጎን ይሰለፋል፡፡ በዚህም አቋማቸው የሚደረገባቸውን ማናቸውንም ትንኮሳ ያወግዛል፡፡

## ስለ ውጪ ወረራ

አንድ አብዮት በሚካሄድበት ወቅት የውስጥ ፀረ—አብዮት ሀይሎች አብዮቱን ከውስጥ ሆነው በመቦርቦር ብቻ አይወሰኑም፡፡ በውጪ ካሉት የፀረ—አብዮት ኃይሎች በተለይም ከቀንደኛው ከአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ጋር በሚሊዮን ገመዶች የተሳሰሩ ስለሆኑ ከውጪ ለሚመጡ ጥቃቶች አመቺ መሣሪያዎች ይሆናሉ፡፡ በኢት ላይ የታወጀው ፀረ—አብዮት ጦርነት የተጋጋለውን አብዮታችንን ለማዳፈን በአለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም አቀናጅነት፣ በአካባቢው ሊያመጣ የሚችለውን አብዮታዊ እንቅስቃሴ በተገነዘቡት በአካባቢው አድሐሪ የገዥ መደቦችና በአገር ውስጥ ባሉ ፀረ—አብዮት ኃይሎች ተባባሪነት የተወጠነ ሴራ ነው፡፡

ስለዚህም ጦርነት መነሻ:—

1 — ሱማሌ በባንዲራዋ ላይ ያስቀመጠችው አምስት ኮከቦችን አንድ የማድረግ ፍላጎ ትዋንና "ታላቋዋ ሱማሌ" የሚለውን ቅዠቷን እውን ለማድረግ ያደረገችው ጥረት፣

2 — በአካባቢው ያሉት ጭቁን ብሔረ ሰቦች ለነፃነታቸው የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ በትክክለኛው መንገድ አለመረዳታቸው ናቸው::

ማህበራችንና ሐቀኛ ተራማጆች የአብዮተኛውን የዚያድ ባሬ ጦር በአገራችን ላ የሚያካሂደውን ወረራ ለመመከት የሚቻለው:—

ሀ) በአካባቢው ያለው የብሔረ ሰቦች ችግር በማርክሳዊ ሌኒናዊ መርህ መሠ ረት ሲፈታ፣

ለ) የአካባቢው ህዝብ ነቅቶና ተደራጅቶ የራሱን ህዝባዊ ሠራዊት ቢያቋቁም ስለሆነ ሱማሌ ሰርጎ ገቦቿን በምትልክበት ወቅት "ህዝቡ ይታጠቅ" "ነፃኛ ንጥቁን ይፍታ" በማለት እንዲሁም የዘመተውን ህዝባዊ ሠራ ከአድሐሪ ቢሮክራሲው ቁጥጥር ነፃ ሆኖ አብዮታዊ አመራር ይኑረው እያሉ ጠቁመው ነበር፣ ነገር ግን ደርግ ለዚህ ጥቆማ "የዝሆን ጆሮ" ይስጠ በማለት ሰራዊቱን በታወቀ ቀንደኛ የሚሊቴሪ ቢሮክራቶች ስር በማድረግ በአካባቢው ህዝብ ላይ እምነት ባለመጣል ጦርነቱን ጀመረና ማጠፊያው በ ጥርበት የወታደርና የማቴሪያል እርዳታ ከአንዳንድ ሶሻሊስት አገሮች አ መጥቶ ጊዜያዊ ድል አገኘ:: ይህም ያሳየው አድሐሪ ቢሮክራሲው እን ሰፊው ህዝብ ይቅርና እምነት ሳያድርበት ለወሳኞ ደርግ እንኳ ታማ እንዳልሆነ ነው:: የሆነ ሆኖ ይህ ጊዜያዊ ድል ዘላቂ መፍትሄ ነው ባንልም እንኳን የውጭ ወራሪ ኃይል ከዚያ አካባቢ መባረር ለሚካሄደው የመደብ ትግል አመቺ ሁኔታ ፈጥሯል እንላለን::

ፀረ—ዲሞክራቲኩ ደርግ የበሰበሰው ቢሮክራሲና አድርባዮች እንደሚሉት በኢቱ ውስጥ ያሉትን [በዚያ አካባቢ] የሱማሌ ብሔረ ሰብና የኦሮሞ ብሔረ ሰብ የሚያደርጉትን ትግ እንቅስቃሴ የሱማሌ ገዥ መደብ ከሚያደርገው የመስፋፋት ምኞት ጋር ጠፍልቆ ማየት ፍፁም ስህተተኛና የብሔር ትምክህተኝነት ነው፣ ለሁለቱም አንድ ዓይነት መፍትሄ መፈለግ ፍፁም ፀረ—ህዝብ እርምጃ ነው::



ሲጠናሩ ይህንን ሁኔታ በሚገባ ከመረመረ በኋላ:—

ሀ) የዚያድ ባሬ አድሐሪ መንግሥት በአገራችንና በወገናችን ላይ የፈፀመውን ፋሽስታዊ ወንጀል ለዚህም ገብሩ የተባበሩትን ኃይሎች ሁሉ በጥብቅ እያወገዘ፣ ያለርህራሄ ይታገላቸዋል::

ለ) ጦርነቱን ከአብዮቱ ነጥሎ እንደ ዓብ እባ በመወሰድ ለውስጥ አድሐሪ ኃይሎች በተለይም ለቢሮክራሲው ፋታ በመስጠት የብዙ ጭቁን ኢትዮጵያውያን ደም በከንቱ እንዲፈስ ያደረጉትን ደርግና አድርባዮች በጥብቅ ያወግዛል::

ሐ) በጦርነቱ ምክንያት በወጣት ነፃጠኞችና በአድርባዮች አማካይነት መሪነው የታጠቁት ነፍጠኞች በአስቸኳይ ትጥቃቸውን እንዲፈቱ ይጠይቃል::

መ) በዚህ አካባቢ የሚገኙት ብሔረሰቦች መብታቸው ታውቆላቸውና ታምነው ጊዜያዊ ድሉ አስተማማኝ እንዲሆን መንቃት፣ መደራጀትና መታጠቅ አለባቸው:: ለዚህና በጠቅላላው በአብዮታችን ላይ ለሚደረገው የውጪ ወረራ የማያዳግምና ዘላቂ ድል ለማግኘት የሚቻለው የኢት ጭቁን ህዝቦች ነቅተው፣ ተደራጅተውና ታጥቀው እንደ አንድ ሰው ሆነው በጋራ ጠላቶቻቸው ላይ ሲነሱ ብቻ ነው:: ለዚህም ህዝባዊ አመጽ እስከ አሁን ያልተሟሉ ነገሮች ሁሉ በአስቸኳይ መሟላት ይኖርባቸዋል:: የዲሞክራሲ መብቶች መለቀቅ፣ የብሔረሰቦች መብት እስከ መገንጠል መታወቅ፣ አድሐሪው ቢሮክራሲ በአፋጣኝ መመታትና ህዝባዊ ሠራዊቱ አብዮታዊ አመራር ማግኘት ናቸው ብሎ ያምናል:: በእነኝህ ነጥቦች ላይ ሰፊው የኢት ህዝብ ትግሉን አጥፍ ድርብ እንዲያደርግ አብዮታዊ ጥሪውን እያቀረበ አብሮትም እስከ መጨረሻው ድረስ እንደሚታገል በጽንሚ ያረጋግጣል::

## ስ ለ ህ ዝ ባ ዊ ድ ር ጅ ቶ ች

በአብዮቱ ሂደት ብዙ ህዝባዊ ድርጅቶች ተፈጥረዋል:: እነዚህም ህዝባዊ ድርጅቶች የመንግሥት ሥልጣን [የህዝባዊ መንግሥት] መሠረቶች ናቸው:: ስለሆነም ህዝባዊ ድርጅቶች ማለት መኢሰማ፣ የገበሬ፣ የቀበሌ፣ የሴቶች ማህበራት ወዘተ አብዮታዊ ሚናቸውን ሊጫወቱ የሚችሉት ሲነቁ፣ ሲደራጁና ሲታጠቁ እንዲሁም ከአድሐሪው ቢሮክራሲና ከደርግ ቁጥጥር ነፃ በመሆን በፀረ—አብዮት ኃይሎች ላይ እርምጃ ለመውሰድ ሲችሉ ብቻ በመሆኑ ነፃ በሆነ መንገድ በይበልጥ መንቃት መደራጀትና በይበልጥ መታጠቅ ያስፈልጋቸዋል:: ስለሆነም ለእነኝህ ድርጅ ቶች መጠናከር ወሳኙ ጥያቄ የዲሞክራሲ መብቶች በአስቸኳይ መለቀቅ ነው:: ባሁኑ ጊዜ በአ ድር ባዮችና በቢሮክራሲው አማካይነት አ[illegible] አብዮቱ የወለዳቸውን ድርጅቶች ለመከፋፈልና

ለማፈራረስ ትልቅ አሸቀዳዳም ይታያል:: ቢሚናሩ በእነኚህ ድርጅቶች ላይ የሚደረገውን ተጽእኖና የመከፋፈል ሁኔታ እያወገዘ፣እነኚህን ድርጅቶች ከቢሮክራሲውም ሆነ ከደርግ ተጽእ ውጭ በበለጠ እንዲነቁና እንዲታጠቁ ለሚታገሉ አብዮታውያን በሙሉ ድጋፉን ይገልጻል፣ የአዲሱ ዲሞክራቲክ አብዮት ፕሮግራም በገቢር እንዲመነዘር ሲታገሉ በደርግና በአድሐሪው ቢሮክራሲ ሥር ቤት የተወረወሩትን ወዝአደሮች፣ የገበሬ፣ የቀበሌ፣ የሴቶች ማህበራትና አባሎችን፣ ተራማጆችና ወጣቶች በአስቸኳይ እንዲፈቱ ይጠይቃል!! ለቆሙለት ዓላማም እስከ መጨረሻው አብ ይቆማል:: ይታገሳል

## የ ሴ ቶ ች ጥ ያ ቄ

በኢት ዉስጥ በመካሄድ ያለው የአዲሱ ዲሞክራቲክ አብዮት ግቡን ሊመታ የሚችለው ጭ ሴቶች ነቅተው፣ ተደራጅተውና ታጥቀው በአብዮቱ ውስጥ ሙሉ ተሳትፎ ሲኖራቸው ብቻ ነው:: ጭቁን ሴቶች በአንድ በኩል ከመደብ ጠላቶቻቸው በሌላ በኩል ከወንድ ትምክህተኝነት ጋር የሚ ያካሂዱትን መራራና የከረረ ትግል ለማፋፋምና ለማጠናከር በበለጠ መደራጀት ይገባቸዋል:: ቢሚናሩ ይህንን ባይነባዊ ሃቅ በመገንዘብ:—

ሀ) ጭቁን ሴቶችን ለማደራጀትና ጠምራ ትግላቸውን አብዮታዊ መስመር ለማስያዝ በግን ባር ቀደምትነት ለሚታገለው ለኢትዮጵያ ሴቶች አብዮታዊ ንቅናቄ [ኢሴአን] የሰጠ ሙሉ ድጋፍ እያደሰ በዚህ ድርጅት ላይ አድርባዮች፣ አድሐሪያንና ደርግ የሚያ ደርጉትን ማናቸውንም ተጽእኖ ያወግዛል፣ ያጋልጣል፣ ይታገላልም::

ለ) በዚህ ድርጅት አባልነትና ደጋፊነት የተጠረጠሩ ግለሰቦችን የመረሸን፣ በወህኒ ቤት የማጉር፣ የማሰደድን እርምጃ በጥብቅ ያወግዛል፣ ግድያና ማስቃየቱ በአስ ቸኳይ እንዲቆምና በወህኒ ቤት የታጎሩት ተራማጅ ሴቶች በአስቸኳይ እንዲፈቱ ይጠይቃል::

ሐ) ጭቁን ሴቶች በሀገር አቀፍ ደረጃ እንዲደራጁ አብዮታውያን የሚያደርጉትን ትግ እንዲያፋፍሙ አብዮታዊ ጥሪውን ያቀርባል፣ ለዚህም ትግል ከአብዮታውያን ጎን የቆመ መሆኑን ያረጋግጣል::

## የ ወ ጣ ት ጥ ያ ቄ

በአብዮት ውስጥ አዲሱ ትውልድ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወት የታወቀ ቢሆንም ወጣቱ በጅምላ አብዮተኛ፣ ሊባል እንደማይችል ታሪክ ያረጋገጠልን ሐቅ ነው:: ይህም ስለሆነ የአ



ወጣቶች በአብዮትና በፀረ—አብዮት ካምፕ ተከፋፍለው ለየቆሙለት መደብ እየታገሉ ናቸው::

ሀ) የአናርኪስት ቡድን ኢህአፖ አብዛኛውን ወጣት በሚያምር ቃላትና በስሜታዊነት ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን በቁጥጥሩ ሥር እንዳደረገ የማይታበል ሐቅ ነው፣ ሆኖም በሃቀኛ ተራማጅ ወጣቶች ትግል የወጣቱ ንቃተ ህሊና እየጠመረ ሲሄድ ኢህአፖን እየተፋው መጥቷል:: ነገር ግን ባሁኑ ጊዜ ወደ አብዮቱ ሠፈር ተመልሰዋል እየተባለ ታክቲካቸውን የለወጡ የኢህአፖ ወጣቶች [''መኢሶን ከደርግ ጋር ተጣልቷልና ከአድርባዮች ጋር ሆነን እንምታው''በማለት ደመኛ ጠላታቸው እሱ ስለሆነ] በጅምላ አብዮተኞች እየተባሉ በአድር ባይ ድርጅቶች እየተመለመሉ በካድሬነት ሥራ ላይ ውለዋል፣ እንዲሁም ይበክ ተብሉ ትጥቅም ታጥቀዋል:: ቢሚናሩ ይህን ዓይነት የአብዮት ቀልበሳ ሴራ እያጋለጠ የሲአይኤው ቡችላ የኢህአፖ ወጣቶች ትጥቃቸውን በአስቸኳይ እንዲፈቱና ከካድሬነት ሥራቸው እን ዲገለሉ ይጠይቃል፣ ይታገላል::

ለ) የአብዮታውያን ወጣቶች መደራጀት ለአብዮታችን ከፍተኛ ዋስትና ነው:: ይህም በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ የአብዮቱን ሠፈር ለማጠናከር ከፍተኛ ትግል የሚያደርገውን የኢትዮጵያ አብዮታዊ ወጣቶች ንቅናቄ [ኢአወን] መመሥረት ይህ ቢሚናር በታላቅ ደስታ ተቀብሎታል:: በተለይም ይህ የወጣቶች ንቅናቄ የመኢሶን የወጣት ክንፍ በመሆኑ ደስታው እጥፍ ድርብ ነው:: ቢሚናሩ ለዚህ የወጣት ንቅናቄ ሙሉ ድጋፉን እየገለጸ በአድሐሪና በአድርባይ ሀይሎች እንዲሁም በደርግ የሚደረጉበትን ማናቸውንም ጭቆና በጥብቅ ያወግዛል::

ሐ) የኢትዮጵያ ወጣቶች በአገር አቀፍ ደረጃ ለመደራጀትና ''መላው የኢት ወጣቶች ማህበር''ለማቋቋም የሚያደርጉትን ትግል በበለጠ እንዲያፋፍሙ አብዮታዊ ጥሪውን እያቀረበ፣ ለዚሁም ትግላቸው ከጎናቸው የቆመ መሆኑን ይገልጻል::

## በኖርዲክ [ኖርዌይ፣ፊንላንድ፣ ዴንማርክና ስዊድን] የመጀመሪያው የኢት ተማሪዎች የአካባቢ ሰሚናር የፖለቲካ ውሳኔ

የኢትዮጵያ ሰፊ ህዝቦች በቀጥታ ጠላቶቻቸው ላይ በአንድነት አብዮታዊ ትግላቸውን ካነሱበት ከየካቲት 66 ዓ.ም ጀምሮ የተጧጧፈበት አብዮታዊ የትግል ጉዞና ብዙ ውጣ ውረዶችና መሰናክሎች የበዙበት መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው፡፡ ሰፊው ህዝብ በዚህ በአጭር ጊዜ ውስጥ በከፈለው መራራ ትግል ለጋብ ትግሉ የሚያዘጋች ብዙ መስዋዕትነትን የጠየቀ አኩሪያ ታሪካዊ ድሎችን ተጎናጽፏል፡፡ በዚሁ መጠን ሰፊው ህዝብ እስከ አሁን ድረስ በከፈለው ያልተቋረጠ የመደብ ትግል ብዙ ትምህርቶችን ቀስሟል፡፡ በነቃት በድርጅትና በትክክል በመጠኑም ቢሆን ኃይሉን ተረድቷል፡፡ ሆኖም ግንም እንጂ ሰፊው ህዝብ ከሰነዘረው በከፈለው ትግል የሬውቶሊዝምን፣ የኢምፔሪያሊዝምና የቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምን መሠረታዊ ይዘቶች የሚያናጉ የመጠን ለውጦችን ቢያገኝም ቅሉ ቀረኛ ጠላቶችን በማያዳግም ሁኔታ ደምስሶ የፖለቲካ ሥልጣንን በእጁ ሥር ለማስገባት አልቻለም፡፡ ዛሬም ለዚህ ለሰፊው ያሉ የሚያበቁትን የህሊናዊ ዝግጅቶች አሟልቶ ካለመገኘቱም በላይ እስከ አሁን ድረስ የተጎናጸፈውን ድሎች ጠብቆ ትግሉን ኃይሬት ለማራመድ የሚያበቃው አንድነትን ቀስቅሞ የለውም፡፡

እርግጥ የኢት አብዮት በዚች በአጭር እድሜው ውስጥ ብዙ የመደብ መንሸራተቶች ቢታዩበትም እጥፈትንና ተከሳካይነት ቢፈራረቁበትም የጠላትና የወዳጅ ጠላቶች በየጊዜው ቢፈታተኑትና ጉዳቶች ቢያደርሱበትም ቅሉ ሰፊው ህዝብ ለይበገር በደረገው ቆራጥ ተጋድሎ በየጊዜው የደረሱበትን ጉዳቶችና የተነሱበትን ጠላቶች እየተቋቋመ አብዮቱን በያስቀሰብስ እስከ ዛሬ ለማቆየት ችሏል፡፡ ሆኖም ታሪክ ሰፊው ህዝብ ማሸነፉ ብቻ በይሆን ጊዜያዊ መሸነፍም፣ አብዮት ከግቡ መድረስ ብቻ ሳይሆን መቀልበስም ሲደርስበት እንደሚችል ያስተምረናል፡፡ በዚህ መሠረት የኢት ሰፊ ህዝቦች ለብዙ የሚያስፈልጉትን የህሊናዊ ቅድመ ሁኔታዎች ሙሉ ለሙሉ ባያሟሉ እስከ አሁን ከጠላቶቻቸው የተጎናጸፉትን ቀደምት ድሎች በመቋቋም አብዮታቸውን በያስቀሰብስ ቆይቷል፣ይህ ማለት ደግሞ አብዮቱ ሊቀለበስ አይችልም ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ነው፡፡

የኢት ሰፊ ህዝቦች አብዮት ከእጥፈት ወደ ተከሳካይነት በተሸጋገረበት በመጋቢት 69 ዓ/ም ጀምሮ ከዚህ በፊት በይዘቱም ሆነ በጥልቀቱ ተወዳዳሪ በማይገኝለት ከፍተኛ የውጥረትና የትርምስ አደጋ ውስጥ ይገኛል፡፡ በዚህ በአሁኑ የትግል ምእራፍ ውስጥ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ የመደቦች አሰላለፍ እየተለዋወጠ መጥቷል፡፡ የአብዮቱን አመራር የያዘው





ወሳኙና የንዑስ ከበርቴ መደብ ተራማጅ ክፍሉን አጧጦ ከአብዮቱ ጥርጥ ጠላቶች በተለይም ከቢሮክራሲው ጋር ስልጣን በማጋመር ላይ ይገኛል፡፡ ትላንት ከህዝቡ ጎን የተሰለፈ በመስራ ሰፊ የሰራውን ህዝብና ግሃቀኛ ተራማጆችን መፈክሮች በአብዮት አደባባይ ላይ ሲያስተጋቡ የነበሩት ወዘ፣ ሰደድና ማሌሪድ በአብዮቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ከፍተኛ የመደብ መንሸራተት በማሳየት ላይ ይገኛሉ፡፡ ደርግና እነዚህ የቀኝ አድርባይ ድርጅቶች ትላንት የተቀበሉትን የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ ፕሮግራም ዛሬ በመክዳት ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚህ ታሪካዊ ወቅት ሰደድ፣ ወዝና ማሌሪድ በወጣለት አድርባይነት የገዛ ፕሮግራማቸውን፣በኢማሌድህ ውስጥ ያዐደቋቸውን መርሃ ግብርና የድርጊት ፕሮግራም በገሃዱ ከመክዳታቸውም በላይ ዛሬ በግብር ከአድሃሪ የደርግ አባላትና ከአብዮቱ ቀንደኛ ጠላት ከሆነው ከቢሮክራሲው ጋር በመመሳጠርና የእሱ ተቀጥላ በመሆን በሃቀኛ አብዮታውያን፣በታጋይ ኃይሎች፣ ወዝአደሮች፣ መለዮ ለባሾች፣ ወጣቶች ይህ ነው የማይባል ዐረ–አብዮት ሴራ በማካሄድ ላይ ይገኛሉ፡፡

ዛሬ ደርግና አድርባዮች በሚከተሉት የቀኝ አድርባይ የፖለቲካ መስመር ሰበብ የአብዮቱ ሃይሎች እየተዳከሙ የአብዮቱ ጠላቶች ከመቸውም ይበልጥ ተጠናክረውና ተደላድለው የጥፋት ሴራቸውን በማካሄድ ላይ ይገኛሉ፡፡

ኢሕአፓ የነቃ፣ የተደራጀና የታጠቀ ህዝባዊ አመጽ የሚለውን አብዮታዊ መስመር በመከተል በአሁኑ ጊዜ አብዮቱ ያሉበትን ችግሮች ከአብዮቱ ሰራው ሰፊ ህዝብ ተነጥሎ ይልቅ ከውጭ የሚገኘውን እርዳታና ቢሮክራሲውን በመጠቀም የአጭር ጊዜ ወታደራዊ መፍትሄዎችን እየፈለገ በስልጣን ተደላድሎ ለመቀጠል ይሻል፡፡ ዛሬ አብዮታችን በሚገኝበት አዲስ የትግል ምእራፍ ውስጥ ኢሕአፓ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ በአመራር ሚናው አውነተኛ የንዑስ ከበርቴ መደብ ጠባዩን በማንፀባረቅ ላይ ይገኛል፡፡ በዚህ መሠረት ሰፊው ህዝብ ታሪካዊ ሚናውን እንዳይጫወት ከማድረጉ፣ ሀገሪቱና አንድነት ከማዳከት የተነሳ የሚያስከትሉ መብቶችን አፍኖ በመያዝና ህዝባዊ ድርጅቶችን በማንአስበኝነት በቀጥጥሩ ሥር ለማድረግ በመጣጣር ላይ ይገኛል፡፡ በዚህ ቸ"በቀውጢ ቀን" ከሃቀኛ ተራማጆችና ከአገር ወዳዶች ይልቅ በአስተዳደር ውስጥ ቁልፍ ቦታዎችን ለወጣላቸው አድሃሪ ቢሮክራቶች በመስጠት፣ ከአብዮት ሰራው ከሰፊው ህዝብ ይልቅ በተቀጣሪ በውጭ እርዳታ ላይ በመተማመን፣ ከሰፊው ህዝብና ከእውነተኛ ወገኖች ይልቅ በግልጽ የአብዮቱን አበይ ጠላት ቢሮክራሲውን በመያረቅና ከእሱም ጋር በተግባር በመስለፍ፣ ሰፊው ህዝብ ከባር እስከ ዳር "አብዮታዊት እናት አገር ወይም ሞት" ብሎ በተነሳበት ወቅት የዘመቻውን አመራር ለወጣላቸው የህዝብ ጠላት ሚሊተሪ ቢሮክራቶች በመስጠት፣ አብዮቱ ከሚገኝበት ከቀሰበበ አደጋ ለመውጣት ሰፊው ህዝብ በይበልጥ እንዲነቃ፣ እንዲደራጅና እንዲታጠቅ አድሃሪው ቢሮክራሲ እንዲመታ፣ ህዝባዊ ድርጅቶች እንዲጠናከሩ፣ የሃቀኛ ተራማጆች አንድነት እንዲጠናከር፣ የወዝአደሩን ፓርቲ፣ ህዝባዊ አብዮታዊ ኅንባሩንና ስራዊቱን ለመመስረት የሚደረገው ትግል እንዲፋፋም በሁኑ ወቅት ወሳኝ የሆነውን የዲሞክራሲ ጥያቄ አፍኖ በመያዝ

ከፍተኛ የመደብ መነሸራተት በማድረግ ወደደመ ጠላ በገበር ፀረ—አብዮትን በማጠናከር ላይ ይገኛል::

ዛሬ ጊወአደ በሚከተለው የፖለቲካ መስመር የአብዮቱ ሰፈር እየተዳከመ የፀረ—አብዮቱ ሰፈር እያየለ መጥቷል:: ሰፊው ህዝብ ሰበዊና ዲሞክራሲያዊ መብቱን በመገፈፍ በገዛ አብዮቱ ውስጥ ሎሌ ተበትኛ ለማድረግ ከለመቻሉም ሌላ በአንዳንድ በታዎች በሰሜን በደቡብና ደቡብ ምስራቅ በበዛ ትምክህተኝነት ጭቁን አርሶ አደሮች ይጨፈጨፋሉ:: በተለይም በደቡብና በደቡብ ምስራቅ ባንድ ወገን የሶማሊ ወራሪዎች በሌላ ወገን የደርግ ቀኝ ክንፍና አድርባዮች ከቢሮክራሲው ጋር በመተባበር ያጠናከሯቸው የቀደሞ ነፍጠኞች እንደገና በማንሰራራት በነዚህ ቦታዎች ይህ ነው የማይባል ፋሽስታዊ ጭፍጨፋ በጭቁኑ ገበሬ ላይ ያካሂዳሉ:: ከዚህ በተጨማሪ በብዙ ስፍራዎች በተለይም በሰሜንና ደቡብ ህዝባዊ ድርጅቶች በመፈራረስ ላይ ናቸው:: በነዚህ ቦታዎች የሚገኙ ካድሬዎች እንደ ህዝብ ጠላት እየታደኑ፣እየተረሸኑ እየታሰሩ በምትካቸው የአድርባይ መስመር በሚከተሉ ካድሬዎች ይቀየራሉ:: ዛሬ የብዙሃ በሥራ እንዲተረጎም አብዮቱ ከሚገኝበት ተከላካይነት ወደ አጥቂነት እንዲሸጋገር የሚታገሉ መኢሶን ሃቀኛ ተራማጆች፣ ታጋይ ወዝ አደሮች፣ አርሶ አደሮች መለዮ ለባሾች ወጣቶች የጭቁን ብሄረሰብ ታጋዮች እየታደኑ ይረሸናሉ፣ ይታሰራሉ ቶርቸር ይደረጋሉ:: በአንፃሩ የወጣሳቸው አድሃሪዎች ከእስር ቤት ይለቀቃሉ:: በሰሜንና በደቡብ ምስራቅ የተደረገውን ዘመቻ አመራርን የሰጡት የጋጣሳቸው አድሃሪ ቢሮክራቶች በደረጉት የተቀነባበረ አሻጥር በብዙ ሺ የሚቆጠሩ የመደበኛው ጦርና የህዝባዊ ሠራዊቱ አባላት ደም በከንቱ ሊፈስ ችሏል:: በተለይም የሶማሊ ወራሪዎች ሀረርና ድሬዳዋን ገፍተው ለመያዝ ያደረጉት ያልተሳካ ሙከራና በሰሜን የኤርትራ አድሃሪ ተገንጣይ ቡድኖች/90% የኤርትራ ክፍለ ሃገር በቁጥጥራቸው ስር ለማድረግ የቻሉት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በቢሮክራሲው ትብብር መሆኑ ያደበባይ ሚስጥር ነው:: በደቡብ ምስራቅ በሶማሊ ወራሪዎች ላይ የተገኘውን ጊዜያዊ ወታደራዊ ድልና መጥቃት ቢሮክራሲው በሱ ብርታት የተገኘ ለማስመሰል የሚያደርገው ሙከራ በፍጹም ከእውነት የራቀ ለመሆኑ በቢሮክራሲው አመራር ስር በዘመቻው ላይ በደረሱት ከፍተኛ ውድቀቶች ለመረዳት ይቻላል:: ደርግ በአሁኑ ጊዜ በሰሜን በኩል ያለውን ችግር የፖለቲካ መፍትሄን በተቀዳሚ ወስዶ ለመፍታት ከመሞከር ይልቅ በውጭ በሚያገኘው እርዳታ ላይና በፀረ—ህዝብ በሆነው ቢሮክራሲው አመራር በመተማመን እንደ ደቡብ ምስራቅ ተመሳሳይ የሆነ የጦር መፍትሄ ለማድረግ በመዘጋጀት ላይ ይገኛል:: ይህ በፀረ—ህዝብ ቢሮክራሲ አመራር ስርና በውጭ እርዳታ ላይ በተቀዳሚ ተማምኖ የሚገኝ አስቸኳይ የወታደራዊ መፍትሄ በዚህ ቦታ የሚገኘውን ችግር ከማባባሱም በላይ ብዙ እልቂትን የሚያስከትልና በአብዮቱና በአገሪቱ ላይ ተጨማሪ ውድቀትን ሊያስከትል ስለሚችል ከዚህ ዓይነቱ ስህተት አስቀድሞ መጠንቀቅ ብልህነት ነው እንላለን::





በተጨማሪ ከፍ ብለን በጭሩ ከጠቀስናቸው የፖለቲካ ችግሮች በላይ በሁኑ ጊዜ አገሪቱ በገጠርና በከተማ የኑሮ መወደድ ህዝቡን አንገሽግሽታል፣ በብዙ ቦታዎች አርሃብ ገብቷል፣ ስለሆነም አገሪቱ በከፍተኛ የኢኮኖሚ ውድቀት ውስጥ ትገኛለች:: ይህ ችግር ከጊዜ ወደጊዜ እየተባባሰና አስከፊ መልክ እየያዘ እንዲመጣ፣ ሰፊው ህዝብ በአብዮቱ ተስፋ እንዲቆርጥና በገዛ አብዮቱ ላይ እንዲነሳ ቢሮክራሲው የሚያደርገውን አሻጥር ከመቸውም ይበልጥ በማፋፋም ላይ ይገኛል::

ባጠቃላይ ዛሬ ደርግና አድርባዮች በሚከተሉት የፀረ—አብዮት መስመር አብዮቱ በከፍተኛ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ቀውስ ውስጥ ይገኛል:: የአብዮቱ ጠላቶች ከምን ጊዜም የበለጠ ተጠናክረዋል:: የአብዮቱ ሃይሎችና የሰፊው ህዝብ ወገኖች ከመቸውም ይበልጥ ተረግጠዋል:: ይህ ሁኔታ በዚህ ከቀጠለ የአብዮቱ መቃብር ሩቅ አይሆንም:: በዚህም የተነሳ በኖርዲክ የሚገኙት የኖርዌይ ቅ|ማህበር፣ የፊንላንድ ቅ|ማህበር፣ የዴንማርክ የጥናት ቡድንና የስዊድን ቅ|ማህበር ከ13/5/78—14/5/78 ባካሄዱት ጉባኤ የኢት ጊዜያዊ ሁኔታን ከመረመረና አብዮቱን የገጠሙትን የቀልበስ አደጋዎች ካጤኑ በኋላ ከዚህ የሚከተለውን የፖለቲካ ውሳኔዎች አሳልፈዋል:

## ስ ለ ጊ ወ አ ደ ር ግ

ጊ ወ አ ደርግ የኢት ህዝቦች ትግል ከፈነዳበት በተለይ ደርግ በስልጣን ላይ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ብዙ የተለያዩና ፍጹም የማይጣጣሙ አቋሞችን ወስዷል:: በአንድ ወቅት አብዮቱን የሚረዳና አብዮታዊ ትግሉን የሚያጠናክር እርምጃ ሲወስድ በአንፃሩም ብዙ አብዮቱን የሚጎዱ ሚናዎችን ተጫውቷል:: የጊ ወ አ ደርግ በየአለቱ መወላወል ካለው የመደብ/ጠባይ አንጻር ሲታይ አዲስ ሊሆን አይችልም:: ሆኖም በተለይ ከመጋቢት 69 ወር ወዲህ የወሰዳቸው አድሃሪ እርምጃዎች በቀላሉ የሚታዩ አይደሉም:: የሰፊው ህዝብ ወገኖች የሚያዳክሙ፣ አድሃሪዎችን የሚያጠናክር፣ ትግል አካሂዷል:: ከእነዚህም ውስጥ የሰፊውን ህዝብ ወገኖችና አካሎች የሆኑትን ሃቀኛ ተራማጆች፣ ታጋይ ወዝአደሮች፣ አርሶ አደሮች፣ ጭቁን ሴቶች፣ አብዮታዊ ወጣቶችን አስሯል:: ከአዚያም አልፎ ጨፍጭፏል:: የኢት ህዝብ ለረጅም ጊዜ የታገላቸውና አሁንም በመታገል ላይ ያሉትን አድሃሪ ቢሮክራቶች እየሾመ አብዮቱን እንዲጎዱ ሁኔታ ፈጥሮላቸዋል:: ጭቁን ብሄረሰቦችን ፍጹም ትምክህተኛ በሆነ መንገድ ጨፍጭፏል፣ እየጨፈጨፈም ነው:: የረጅም መራራ ትግል ውጤት የሆኑትን የህዝብ ድርጅቶች እንደ ገበሬ፣ ሰራተኛ ማህበር፣ የቀበሌ፣ የሴቶችና የወጣት ድርጅቶች በማፈራረስ ላይና እነዚህ የህዝብ ድርጅቶችን በማንአለብኝነት ከቁጥጥሩ ስር ለማድረግ ከላይ ታች በማለት ላይ ነው:: ከዚህም አልፎ የሰፊውን ህዝብ ታሪካዊ ሚና ዝቅ አድርጎ በማየትና በመናቅ የውጭ እርዳታን በተቀዳሚ በመውሰድ ላይ ይገኛል:: እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸው ድርጊቶች በተጨባጭ አብዮቱን የሚጎዱ

በመሆናቸው ኢ ወ አ ደርግ ሰልፉን ከሰፊው ህዝብ ጋር ለማስተካከል የሚችለው:—

— ሰፊው ህዝብ አብዮትን አክሄዶ ድል ይጎናጸፍ ዘንድ የዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁ ያለገደብ አሁኑኑ ሲለቅ፤

— በየአብዮቱ አደባባይ አብዮት አብዮት እያለ እየወሸ በተግባር አብዮትን የሚጎ አርምጃዎችን መውሰድ አቅሞ፤ለአብዮቱ ጥንካሬ የሚረዱ ድርጊቶችን በተጨባጭ ሲወ ስዱ፤

— በመኢሶን አባሎችና ደጋፊዎች፤ ታጋይ ወዝአደሮች፤ አርሶ አደሮች፤ ጭቁን ቢሮ አብዮታዊ ወጣቶች፤ አብዮታዊ ሠለዋ ሰባሾች ላይ የሚያካሄደውን ጭፍጨፋ፤ እስ ራት፤ ክትትል አሁኑኑ አቅሞ በየእስር ቤቱ ያጎራቸውን የሰፊው ህዝብ ወገኖች ሲፈታ፤

— ሰፊው ህዝብ አብዮት እስከክሄደ ድረስ የፊውዳ ቡርዡው ቢሮክራሲ የአብዮቱ ጠላ ት እንጂ የአብዮቱ ወዳጅ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ ፍጹም የማይቻል መሆኑን ተቀ ብሎ ከዚህ ሃይል ጋር የጀመረውን መቀራረብና መወዳጀት አቅሞ አሁን የሰጣቸውን ና በመስጠት ላይ ያለውን ቁልፍ ቦታዎችን ነጥቆ በእነሱ ቦታ ተራማጆችና የሰፊ ው ህዝብ ወገኖች የሆኑትን አገር ወዳዶችን ሲተካ፤

— የአንድ አብዮት መሰረቱ ሰፊው ጭቁን ህዝብ ነው:: ያለሰፊው ህዝብ ሙሉ ተሳ ትፎ አብዮቱ ግቡን ይመታል የሚል አስተሳሰብ ያላቸው ሰፊውን ህዝብ የሚፈሩ የሰፊው ህዝብ ጠላቶች ናቸው:: እርዳታ ለአንድ አብዮት አጋዥ እንጂ ወሳኝ አይደለም:: ስለሆነም ደርግ ይህንን ተገንዝቦ ሰፊው ህዝብ በአብዮቱ ሙሉ በሙሉ እንዲሳተፍ፤ እንዲነቃ፤ እንዲደራጅና እንዲታጠቅ የሚደረገው ትግል ቢቀ ጥልና ለዚህም ተራማጆች ከሰፊው ህዝብ ጋራ መቀሳቀስ አስፈላጊ መሆኑን ተረድቶ እንዳይቀሳቀሱ የሚደረገውን ተጽእኖ በሙሉ እንዲቆም ሲያደርግ፤

— "የቀይ ሽብርን" መደበኛ ይዘት በማስት በቃሉ ብቻ በመጠቀም በቀይ ሽብር አሰበ ብ ተራማጆችንና የሰፊው ህዝብ ወገኖችን ለመጨፍጨፍ የሚደረገው ዘመቻ ቆሞ የቀይ ሽብር ትክክለኛና መደበኛ ይዘቱን በይስት ይህ ቀይ ሽብር በአድሃሪዎ ና በአብዮቱ ጠላቶች ላይ ብቻ የሚያተኩር መሆን ይገባዋል:: ይህም በደንብ ሊቀነባበርና ግቡን ሊመታ የሚችለው ሰፊው ህዝብ በህዝባዊ ድርጅቶች አማካኝነ ቱሉ በሙሉ ሲሳተፍበት ብቻ በመሆኑ፤ ደርግ በስም ብቻ መጠቀሙን አቅሞ ሰፊ ው ህዝብ ነፃ የሆነ አርምጃዎችን እንዲወስዱ ሲያደርግ፤





ቀ

— አገሪቷን ከውጭ ወረራ ለመከላከል በሚደረገው ዘመቻ ቢሮክራሲው አመራሩን ተነ ጥቆ በተራማጆችና በአገር ወዳዶች እንዲተካ ሲያደርግ፤

— ሰፊው ህዝብ የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራምን በስራ ለመተርጎም በሚያደ ርገው ትግል ውስጥ ደርግ በጎኑ የሚሰለፍ መሆኑን በወረቀትና በአፍ ብቻ ሳይሆን በተጨባጭ የሚያስመሰክረው በሚወስደው አርምጃና አብዮትን ለማራመድ በሚጫወተው ሚና መሆኑን በመገንዘብ ደርግ እነዚህ ከላይ የገለጽናቸውን አርምጃዎች በስቡብ በአስበቡ ሳያቆበሰብስ በአስቸኳይና በተጨባጭ በተግባር እንዲተረጉማቸው በደርግ ውስጥ ሳሉ ተራማጅ ሃይሎች ይህ ጉባኤ አብዮታዊ ጥሪውን ያደርጋል:: እነዚህ በተግባር ካሴኮነዘሩ ማህበራችን እስከ መጨረሻው ድረስ ከሰፊው ህዝብ ጎን በመ ቆም ለእነዚህ አርምጃዎች በስራ መተርጎም የሚጠይቀዋቸውን መስዋእቶች በሙሉ በመ ስጠት የሚታገል መሆኑን በድጋሚ ያረጋግጣል::

## ስለ ቢሮክራሲ

በኢት ውስጥ የሚገኘው ቢሮክራሲ ከፈላጭ ቆራጩ የሃይለስላሴ መንግሥት የተወረሰው ቢሮክራሲ የፊውዳሊዝምንና የኢምፔሪያሊዝምን ጥቅም ለመጠበቅ ኢምፔሪያሊስቶች ከትኩተው ያስ ደጉት እንደ መሆኑ መጠን በአጠቃላይ የመደብ ይዘቱም ሆነ በአብዮቱ ውስጥ ባለው የሃይል አሰላለፍ በቀጥታ ከሰፊው ህዝብ አበይ ጠላቶች ኢምፔሪያሊዝምና ፊውዳሊዝም ጋር የሚመደብ ነው:: ስለሆነም በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ላይ በማያሻማ ቃላት ቢሮክራ ሲው ከአብዮቱ ዋና ጠላቶች አንዱ መሆኑና መመታት ብሎም መደምሰስ እንዳለበት ሰፍሯል:: ይህ ፀረ—ህዝብ የሆነ ቢሮክራሲ አብዮቱ ከፈነዳበት ጊዜ ጀምሮ ያሳነዳች ማቋረጥ የውስጥና የውጭ ፀረ—አብዮት ሴራዎችን ለማቀነባበር ልዩ ልዩ ገልጽና ሰውር የኢኮኖሚ፤ የፖለቲካ፤ አሻጥሮችን በማድረግ ህዝቡ እንዳይነቃ፤ እንዳይደራጅና እንዳይታጠቅ እንቅፋቶችን በመፍጠር፤ ህዝባዊ ድርጅቶችን በማዳከም፤ በተራማጆች መሃከል አንድነት እንዳይፈጠር በአንዳንድ "ተራ ማጅ" መሰል ድርጅቶች ውስጥ ሰርጎ በመግባትና ውዥንብሮችን በማሰራጨት ሃቀኛ ተራማጆችንና አገር ወዳዶችን በማሰር፤ በመግደል፤ በማንገላታት አብዮትን በአፍ ጢሙን ለመድፋት ይህ ነው የማይባል ፀረ—ህዝብና ፀረ—አብዮት ሴራ እንዳካሄደና አሁንም በማካሄድ ላይ መሆኑን ገልጽ ነው:: በዚህም መሠረት የኢት ጭቁን ህዝቦች፤ ተራማጅ ድርጅቶችና አገር ወዳድ ግለሰቦች ያለማቋረጥ ይህን ፀረ—ህዝብና ፀረ—አብዮት ሃይል እንዲደመሰስ ታግለውታል፤ አሁ ንም እየታገሉት ናቸው::

ሃቁ ይህ ሆኖ ሳለ ኢ ወ አ ደርግ ከዚህ ፀረ—ህዝብና ፀረ—አብዮት ቢሮክራሲ ጋር በተግባር በመዋሃድ ከአብዮት ሰፊው ጭቁን ህዝብ ይልቅ በቢሮክራሲው ላይ እምነቱን

በመጣልና ለወጣሳቸው አድሃሪ ቢሮክራቶች በአስተዳደር ውስጥ ቁልፍ ቦታዎችን በመስጠቱ አብዮቱን ለመቀልበስ የሚያሴሩት አድሃሪ ቢሮክራቶች አዲስ በማግኘታቸው አብዮቱ ከፍተኛ የቀልበሳ አደጋ እየተፈታተነው ይገኛል:: በተለይ የጊ ወ አ ደርግ የዘመቻውን አመራ ር ከተራማጆች ይልቅ ለወጣሳቸው አድሃሪ የሚሊቴሪ ቢሮክራቶች በመስጠት በሰሜንና በደቡብ በዘመተው መደበኛና ''ህዝባዊ ጦር'' ላይ ከፍተኛ ጉዳቶች እንዲደርሱ ከመቻላቸውም በላይ ይኸው አድሃሪ ቢሮክራሲ በአመራር ባደረገው አሻጥር አብዮታዊ እናት አገራችን ከመደፈሯ አልፎ ለጠላት ጊዜያዊ ድል ሰጥቶ እንደነበር ይታወቃል:: ስለሆነም ይህ ጉባኤ:-

– በአድሃሪ ቢሮክራቶች በተያዙት ቁልፍ ቦታዎች ምትክ በተራማጆችና በአገር ወዳዶች እንዲተኩ፤

– የወደፊቱ የህዝብ ስልጣን አውታሮች የሆኑት ህዝባዊ ድርጅቶች እንዲጠናከሩና የሰፊው ህዝብ አብዮታዊ ተሳትፎ እንዲዳብር እነዚህ ህዝባዊ ድርጅቶች ከቢሮክራሲው ቁጥጥር ነፃ እንዲሆኑ፤

– በተራማጆች መካከል አንድነት እንዳይፈጠር ፀቸንበር በመንዛትና አገር ወዳ[ድ] የሆኑትን በማሰርና በማንገላታት፤ በመግደልና በማሰቃየት ቢሮክራሲው ከፍተኛ ፀረ-አብዮት ሴራ ስለሚያካሂዱ፤

– አገሪቱንም ላይ ደርሶ የነበረው ወረራ የሚሊቴሪውና የሲቪሉ ቢሮክራሲ አሻጥ[ር]ና ተንኮል ጭምር በመሆኑ ለወደፊትም ከዚህ አይነት አደጋ ለመውጣት እንዲያ[ስችል] ጉባኤችን ይህንን አድሃሪ ሃይል ያለ ርህራሄ እንዲመታ ይታገላል:: በተጨ[ማሪ]ም ዛሬ ሰፊው ህዝብ የሚያካሂደው ፀረ-ቢሮክራሲ ትግል በይበልጥ እንዲፋፋ[ም] የሰፊው ህዝብ ነፃ እርምጃዎች እንዲለቀቁ ይጠይቃል፤ ለዚህም ይታገላል::

ከበሰበሰው ስርአት የተወረሰው አድሃሪ ቢሮክራሲ እንዲመታና ከዚህ ፀረ-ህዝብ ሃ[ይል] ጋር ለመታረቅ የሚደረገውን አዝማሚያ ለማጋለጥ የሚካሄደውን ትግል እንዲያፋፍሙ ለሃቀኛ አብዮታውያን፤ በደርጉ ውስጥ ከደርጉ ውጪ ለሚገኙ ተራማጆችና አገር ወዳዶች በሙሉ አብዮ[ታ]ዊ ጥሪውን ያቀርባል::

## ስ ለ ዲ ሞ ክ ራ ሲ

በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ ሊኖር የሚችለው ዲሞክራሲ በመንግሥት ስልጣን ላይ የ[ተቀ]መጠው መደብ ጥቅም የሚያስከብርበትና መገልገያ መሣሪያው መሆኑን የህብረተሰብን እድገት መርምሮ የተረዳ የሚያውቀው ነገር ነው::





የኢት ጭቁን ህዝብ በፋሽስታዊው ሃይለስላሴ አገዛዝ ሥር በነበረበት ወቅት የነበሩት ህጎች በሙሉ ሰፊውን ህዝብ ረግጦ ለመግዛት የፊውዶ ቡርዧዋውን መንግሥት ሙሉ ጥቅም ለማስከበር የተደነገጉ ነበሩ:: በዚያን ጊዜም በኢት ሰፊው ህዝብ ላይ ይደርሱበት የነበረው ኢሰብአዊ ሁኔታዎችን ማስታወስ በቂ ማስረጃ ነው:: የኢት ጭቁን ህዝብም ነፃነቱን ለማስከበር በቆራጥነት አንስቶ ይታገልባቸው ከነበሩት ጥያቄዎችም አንዱ የዲሞክራሲ ጥያቄ ነበር:: የሃይለስላሴንም ፋሽስታዊ አገዛዝ በረጅም ጊዜ ትግሉ ከገረሰሰ በኋላ አገኝቶት በነበረው የዲሞክራሲ ጭላንጭል ጠላቶችን በመጠኑም ቢሆን አንበርክኳቸው እንደነበር በአይናችን ስር ያለፈ ሃቅ ነው:: ዛሬም በኢት ምድር ላይ የሚታዩት ተራማጅ መፈክሮች ቢሮክራሲው ይሰበር፤ ወዝአደር ፓርቲ በአስቸኳይ ይመስረት፤ ሰፊው ህዝብ ይንቃ፤ ይደራጅ፤ ይታጠቅ ወዘተ ለአድሃሪያዎች ሴራ ፋታ ባይሰጥ በስራ ሊተረጎም የሚችለው የዲሞክራሲ ጥያቄ መልስ ሲያገኝ ብቻ ነው:: ሰፊው የኢት ጭቁን ህዝብ ዛሬ የዲሞክራሲ መብቱን ይሰጠኝ ብሎ የሚታገልበት ዋና ምክንያት በአብዮት ጎዳና ላይ የሚያጋጥሙትን እክሎች ለመጥረግና ትግሉን ወደፊት ለማራመድ የሚገለገልበት መሣሪያ መሆኑን በማወቅ ነው::

የዲሞክራሲ ጥያቄ የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት መሠረታዊ ጥያቄ እንደመሆኑ መጠን የየካቲት 66 አብዮት ኢት ውስጥ ከፈነዳበት ጊዜ ጀምሮ ሰፊው ህዝብና ተራማጆች ያላንዳች ማቋረጥ ታግለውለታል:: የጊ ወ አ ደርግ በፕሮግራሙ ላይ ለሰፊው ጭቁን ህዝብ ዲሞክራሲ ያለገደብ እንደሚሰጥ አስፍሯል:: ከዚህም በላይ በስራ በአስቸኳይ እንደሚተረጎም ደጋግሞ ቃል ገብቷል:: ይህ ሆኖ ሳለ ጊ ወ አ ደርግ እስከ አሁን ድረስ ቃሉን ሳያከብር የዲሞክራሲን ጥያቄ አፍኖ በመያዝ አብዮታችንን ወደ ተከሳካይነት እንዲያፈገፍግ አድርጓታል::

የሰፊው ህዝብ የዲሞክራሲ መብቶች አለመታወቅ የሚጠቅመው አድሃሪ ቢሮክራቶችንና ፀረ-አብዮተኞችን በመሆኑ የሚሸርቡትን ፀረ-አብዮት ሴራ እንዲሳካላቸው ይረዳል:: ይህ ሴራቸው ከተሳካ በሰፊው ህዝብ ላይ ከፍተኛ አደጋ ያስከትላል :: ስለሆነም:-

– ሰፊው ህዝብ ነቅቶ፤ ተደራጅቶና ታጥቆ አብዮቱን ወደፊት ለማራመድና ከአሁን በፊት የተቀዳጃቸውን ድሎች ለማስከበር፤

– የወዝ አደር ፓርቲ፤ ህዝባዊ አብዮታዊ ግንባር፤ የህዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት ለማቋቋም የሚደረገው ትግል እንዲፋፋም፤

– ፀረ-ህዝብ ፀረ-አብዮት የሆነውንም ቢሮክራሲ ሆነ አድሃሪ ሃይሎችን በሰፊው ለማጋለጥና የእነዚህም አድሃሪ ሃይሎች ምንነትን ጭቁኑ ህዝብ በደንብ ተረድቶ ለመደምሰስ እንዲችል፤

— በአጠቃላይ አብዮት ሰሪው ሰፊው ህዝብ ስለሆነ በሚገጥሙት ችግሮች ላይ በግልጽ ለመወያየትና መፍትሄ እንዲያገኝላቸው፣ አብዮቱ ወደፊት እንዲያራምዱ፣ የመፍጠር ችሎታውንም እንዲዳብር የዲሞክራሲ ጥያቄ ዋና መፍትሄ በመሆኑ ይህ ጉባኤ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ አሁኑኑ እንዲለቀቅ ይታገላል::

— ዛሬ ሰፊው ህዝብ ከዳር እስከ ዳር የሚያስተጋባቸው መፈክሮች የቀደመውን ስርአት አውታሮች ለመስበር የዲሞክራሲ ጥያቄ የሚያነሱ ሆነው ሳለ በዚህ አንገብጋቢ የአብዮት ጥያቄ ላይ የወዝና የሰደድና የማሌሪድ ቀኝ አድርባዮች በመንሸራተት ሰፊውን ህዝብ በማወናበድ ''ዲሞክራሲ ለጭቁኖች በትግላችን''፣ ''ያለውን ዲሞክራሲ እንጠቀምበት''፣ ''ዲሞክራሲ ከደርግ ለመጠየቅ አይቻልም''... ወዘተ የሚሉ ወሸንጋሮችን በመንዛትና በአሁኑ ወቅት ዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ እንዲለቀቅ የሚታገሉትን አብዮታውያንንና አገር ወዳዶች የሰፊውን ህዝብ ወገኖችን ለስልጣን የቋመጡና አድሃሪዎች አስመስሎ ለማቅረብ የሚያደርጉትን ከፍተኛ ፀረ—አብዮት ሴራ ይህ ጉባኤ በጥብቅ ያወግዛል:: በተጨማሪም የእነዚህን ቀኝ አድርባዮች ሴራ ከሰፊው ህዝብና ከሃቀኛ ተራማጆች ጎን ተሰልፎ ያለ ርህራሄ ይታገላቸዋል::

## ስ ለ ብ ሔ ረ ሰ ብ

— ማህበራችን ጭቁን ብሔረሰቦች የራሳቸውን እድል በራሳቸው የመወሰን እስከ መገንጠል ድረስ ያላቸውን መብት እንደሚያውቅ አሁንም ደግሞ ያረጋግጣል:: በዚህም መሠረት የብሔረሰቦች አንድነት በመፈቃቀድ፣ በእኩልነትና በወንድማማችነት ላይ እንዲመሠረት ከሚታገሉ ሃቀኛ ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች፣ ተራማጆችና የብሔረሰብ ንቅናቄዎች ጎን በመሰለፍ ይታገላል::

— በአሁኑ በኢት ተጨባጭ ሁኔታ የብሔረሰብ ጥያቄ ከሁለተኛ ደረጃ ጥያቄ አያልፍና አስጊ ሁኔታ ላይ ደርሶዋል ብንል ከእውነት የራቅን አይመስለንም:: (የብሔር ጥያቄ የዲሞክራሲ ጥያቄ እንደመሆኑ መጠን የዲሞክራሲ መብቶች ታፍነው በመያዛቸው የተነሳ ቅራኔው እየተፋፋመ በመሄዱ ላይ ይገኛል::)

በብዙ ሥፍራዎች በተለይ በሰሜንና በደቡብ የብሔር ትምክህተኝነት ነግሶ የጭቁን ብሔረሰብ፣ አርሶ አደሮችና ወዝአደሮች ሰብአዊ መብታቸው ተገፎ በቀደሞ ነፍጠኞች በአድሃሪ ቢሮክራሲና አድሃሪ የደርግ አባሎች ይጨፈጨፋሉ:: በእነዚህ ሥፍራዎች የሚገኙ ህዝባዊ ድርጅቶች በመፈራረስ ላይ ናቸው:: በብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም ላይ የበፊት መርሆች በስራ ላይ ሲውሉ ቀርተው የተገላበጠ የጭቁን ብሔረሰብ ታጋዮች፣ ከዱሮዎች እየታደኑ ይታሰራሉ፣ ይሰቃያሉ:: በአሁኑ ወቅት በብዙ በታዎች ከሁለተኛ ደረጃ ወደ





አንደኛ ደረጃ በተፋጠነ መንገድ እያደገ በመሄዱ ላይ የሚገኘው የብሔረሰቦች ጥያቄ በአስቸኳይ መፍትሄ ካልተገኘለት በጭቁኖች መሃከል መኖር የሚገባውን የትግል አንድነት ስለሚያፋልስ፣ የጭቁኖችን አብዮታዊ ተሳትፎ ስለሚቀንስ ይህ ደግሞ በበኩሉ የፀረ—አብዮት ሃይሎችን ስለሚረዳ ዛሬ ደርግ የቀኝ አድርባዮች ከአድሃሪው ቢሮክራሲና ከነፍጠኞች ጋር በተባበር በመሰለፍ በጭቁን ብሄረሰቦች ላይ የሚያካሄደውን ጭፍጨፋ ጉባኤው በጥብቅ እየተቃወመ፣

— በብሔረሰቦች መካከል በጋራ ጠላቶቻቸው ላይ ያላቸው የትግል አንድነት እንዲጠነክር፣

— ጭቁን ብሔረሰቦች በአብዮቱ ውስጥ የእኩልነት መብታቸው ታውቆና ተከብሮ ሙሉ ተሳትፎ ሊያደርጉ እንዲችሉ፣

— ጭቁን ብሔረሰቦች በአስቸኳይ እንዲነቁ፣ እንዲደራጁና እንዲታጠቁ ለዚህ የሚያበቁ ዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ አሁኑኑ መለቀቅ ይኖርበታል:: ይህ ጉባኤ በጭቁን ብሔረሰቦች ላይ የሚደረገውን ግናቸውንም ጭቆና አያወግዝ፣ በየ እስር ቤቱ ታስረው የሚንገላቱ ተራማጅ የጭቁን ብሔረሰብ ታጋዮች በአስቸኳይ እንዲፈቱ ይጠይቃል:: ለዚህም ከሃቀኛ ተራማጆች፣ ከጭቁን ብሔረሰብ ታጋዮች ጎን ቆሞ ይታገላል:: በተጨማሪም የአፋር ብሔረሰብ ነፃ አውጪ ንቅናቄና /አብነአ/ የኦሮሞ ብሔረሰብ ዲሞክራቲክ ንቅናቄ /ኦብዲን/ ሰጥቷቸው የነበረውን ሙሉ ድጋፍ እንደገና ያዳብል፣ ከጎናቸውም ቆሞ ይታገላል::

— ዛሬ በኤርትራ ውስጥ በወንድማማቾች መሃከል የሚደረገው ከንቱ የደም መፋሰስ እንዲቆም:: ደርግ የኤርትራ ጥያቄ ለመፍታት የወታደራዊ መፍትሄ በተቀዳሚ መውሰዱን አቁሞ ችግሩን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ ይኖርበታል::

## ተ ጀ ም ሮ ስ ለ ነ በ ረ ው ህ ብ ረ ት

የኢት አብዮት ከፈነዳበት ጊዜ ጀምሮ የወዝ አደር ፓርቲ ለመመሥረት የሚታገሉ ተራማጅ ድርጅቶች እንዲፈጠሩና በየቦታው እንዲያብቡ፣ ያሉትም እንዲሰበሰቡ ማህበራችን ያልተቆጠበ ጥረት አድርጓል:: አሁንም ያደርጋል:: በዚህም መሠረት በጥር ወር 69 ዓ/ም አምስት የኢት ማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅቶች ማለትም መኢሶን፣ እጭአት፣ የወዝ አደር ሊግ፣ አብዮታዊ ሰደድና ማሌሪድ የኢትን አብዮት ወደፊት ለማራመድ በሚመለከቱ ዋና ዋና ጥያቄዎች ላይ በሙሉ ተስማምተው የትግል ህብረት ፈጥረው መታገል በጀመሩበት ጊዜ ማህበራችን

የዚህን ህብረት ይዘት በመመርመር በተለይ ከዋና ዋና ነጥቦችን መሠረት አድርጎ የወሰደው:—

- ስለ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት
- ስለ ወዝ አደሩ ፓርቲ አመሠራረት
- ስለ ቢሮክራሲ
- ስለ ዲሞክራሲ በነበራቸው አቋም ተመርኩዞ ድጋፋችንን እንደሰጠን ይታወሳል፡፡

ሆኖም ከጥቂት ጊዜአቶች ጀምሮ መኢሶንና አንዳንድ በድርጅቱ አብዮታዊ አቋማቸው ጸንተው በነቃ በተደራጀና በታጠቀ የህዝብ ክንድ የሚለውን መፈክር አንግበው አብዮቱ ወደፊት እንዲራመድ የቆሙ የኀብረት ትግል ሲያካሄዱ፣ በስተ ድርጅቶች ደግሞ ማለትም ማሌሪድ፣ ሰደድና ወዝ አነ ዚህን ከላይ የጠቀስናቸውንና ሌሎችንም አብዮታዊ ስምምነቶችን በመከዳታቸው በህብረቱ ስቢያ ሰጥቶት የነበረውን ድጋፍ ያነሳል፡፡ ለመኢሶንና ለሌሎች ሃቀኛ ተራማጆች ሰጥቷቸው የነበረውን ድጋፍ እንደገና ያፀናል፡፡ ለሃቀኛ የተራማጆች ህብረት እንዲፈጠር ለሚያደርጉት ትግል ይደገፋል፣ ለዚህም አብሮ በመሰለፍ ይታገላል፡፡

## ስለ አድርባይ ድርጅቶች (ማሌሪድ፣ ሰደድና ወዝ)

ተራማጆች በየጊዜውና በየወቅቱ አብዮቱን ወደፊት የሚያራምዱ ታክቲኮችን በመተለም ከሰፊው ህዝብ ጋር በነገበር ቀደምነት በመዋሃድ አብዮቱ ወደፊት እንዲራመድ ያልተቋረጠ ትግል ማካሄድ ይኖርባቸዋል፡፡ በየጊዜውና በየወቅቱ ከአብዮቱ ሂደት ጋር የሚነሱ መፈክሮች ን ትክክለኛና መልካቸውን በሰፊው ህዝብ ፊት አያስቀ ሰፊው ህዝብና ሃቀኛ ተራማጆች በእነ ዚህ መፈክሮች እንዲታገሉ መቀስቀስ ይኖርባቸዋል፡፡ በሌላ በኩል የአብዮታዊ መፈክሮች የተሳሳተ ትርጉም ለመስጠትና ሰፊውን ህዝብ ለማወናበድ የሚሞክሩትን አድሃሪያችና አድርባዮች በሰፊው ህዝብ ፊት አያጋለጡ ሰፊው ህዝብ እንዲታገላቸው መቀስቀስ ሲኖርባቸው፣ በአሁኑ ወቅት ወዝ፣ ማሌሪድና ሰደድ ይህን አብዮታዊ የትግል መስመር በመተው ሰፊውን ህዝብ በመክዳት ከደ ርግ የቀኝ ክንፍና ከቢሮክራሲው ጋር እጅ ለእጅ ተያይዘው በመተባበር አብዮታችን ወደፊት እንዳይራመድ ፀረ—አብዮታዊ ትግል ያካሄዳሉ፡፡ ወዝ፣ ማሌሪድና ሰደድ በአብዮቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ከፍተኛ መንሸራተት አድርገዋል፡፡ እነዚህ አድርባይ ድርጅቶች ሰፊው ህዝብ ትግሉን ወደፊት እንዳያራምድ በአንገብጋቢ ጥያቄዎች ላይ የሚያወናብዱ መፈክሮችን በማንገብና ወቸንበር በመጨመር የአብዮቱን ፈር ለማሳት ሽር ጉድ በማለት ላይ ይገኛሉ፡፡ በአድሃሪው ቢሮክራሲና ከደርግ አድሃሪያች ጋር በመሰጠር በሃቀኛ ተራማጆችና በአገር ወዳዶች ላይ በሚደረገው ጭቆና፣ ገዳይ፣ ማሰደድና የማሰር ዘመቻ ተባባሪ በመሆናቸው፣ የህዝብ ድርጅቶች ነፃነት በመጋፋት የነሱና የቢሮክራሲው ተቀጥላ ለማድረግ ይህ ነው የማ ይባል ፀረ—ህዝብና ፀረ—አብዮት ሴራ ያካሄዳሉ፡፡ ዛሬ እነዚህ አድርባይ ድርጅቶች አሁን





በያዙት አቋምም ሆነ በገቢር በአብዮቱ ውስጥ ባለው የሃይል አሰላለፍ በሚጫወቱት ሚና አን ድም የሃቀኛ አብዮታዊ ጠባይ ስለማይታይባቸው፣ በጠቅላላው ባላቸው አድሃሪ አቋምና በሚያደ ርጉት ፀረ—ህዝብና ፀረ—አብዮት ድርጊት ጉባኤው በጥብቅ ያወግዛቸዋል፡፡ ከሃቀኛ ተራማጆች ጎን ቆሞም እነዚህን አድርባይ ድርጅቶች እስከመጨረሻው ይታገላቸዋል፡፡

## ስለ መኢሶን (መላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ)

ይህ አብዮታዊ የማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅት በኢት ህዝቦች ታሪክ ውስጥ ያለው ቦታ ከፍተኛ ነው፡፡ ማህበራችን ከዚህ ቀደም የድርጅቱን ፕሮግራምና የሚከተለው የፖለቲካ መስመር በመመርመር አብዮታዊ ድጋፉን እንደሠጠው ገልፅ ነው፡፡ መኢሶን እስከ አሁን ድረስ በተካሄዱት የሰፊውን ህዝብ ትግል ውስጥ የሚጫወተው ገንቢር ቀደም ሚና ፍጹም አብዮታዊ በመሆኑ ማህበራችን፡—

- መኢሶን አብዮቱን በይበልጥ ለማጋለግል ተከፍቶ የነበረው ህጋዊ መስክ በመጥበቡ በግልጽ የታጋቱ አንዳንድ አባሎችን በህቡእ ማሰማራቱና ያደረገው የትግል ዘዴ ለውጥ ጊዜው የሚጠይቀውና ካለው የኢት ተጨባጭ ሁኔታ የመነጨ በመሆኑ ትክክለኛና አብዮታዊ ነው፣
- በሰፊው ህዝብ ድምፅ ቁጥር 64 ያደረገውን ለተራማጆችን ጥሪ አብዮታዊ ጥሪ መሆኑን ጉባኤው ተረድቶ ጥሪው እንዳለ ይቀበላል፣ ለሱም በስራ መተርጎም ይታገላል፡፡
- አሁን የሚያደርጋቸው ቅስቀሳና የሚያስተጋባቸው መፈክሮች በሙሉ አብዮታዊና የጊዜው አንገብጋቢ ጥያቄዎች መሆናቸውን ያምናል፣
- በሁኑ ወቅት ሃቀኛ የተራማጆች ህብረት ለመመስረትና እውነተኛውን የሠራተኛውን ፓርቲ ለማቋቋም በሚደረገው ትግል ውስጥ የወሰደውን እርምጃ ይደግፋል፣
- ማህበራችን መኢሶንን አብዮታዊ ፕሮግራምና የፖለቲካ መስመር መርምሮ የነበረውን ሙሉ ድጋፍ ይህ ጉባኤ በድጋሚ ያጸድቃል፣ ለአብዮቱ ገብ መሥታት በሚያደርገውም ትግል ከጎኑ በመሰለፍ አብዮታዊ ትግሉን ያካሄዳል፡፡

<u>ስ ለ ኢ ሴ አ ን (የኢት ሴቶች አብዮታዊ ንቅናቄ)</u>

የኢት ጭቁን ሴቶች ከየካቲት አብዮታዊ እንቅስቃሴ ጀምሮ ለነፃነታቸውና ለእኩልነታቸው የሚያደርጉት ትግል በየጊዜው እየጠመረና እየተፋፋመ አሁን ካለበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል። ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ከግቡ እንዲደርስ የሴቶች ተሳትፎነት አስፈላጊ መሆኑን የተገነዘቡ ሃቀኛ ተራማጅ ሴቶች ይህንን በይንበዊ ሃቀ በስራ ለመተርጐም በሚያዝያ 1969 ዓ.ም የጋጠውን የኢትዮጵያ ሴቶች አብዮታዊ ንቅናቄ ፕሮግራም ተራማጅና አብዮታዊ በመሆኑ፣ በልሳን ትግ ቀ በታጋይ ኢትዮጵያዊት አጣብኛነት በየጊዜው እንገበጋቢ ጥያቄዎች ላይ የምትሰጣቸውን ትንታኔና ትክክለኛነት በመገንዘብ ይህ ጉባኤ ለዚሁ ንቅናቄ ያልተቆጠበ ድጋፉን ይሰጣል። ተጨማሪ ጋራት ጋዜህ በኒዎናቸው መሪነት በሚጠረጠሩት አበሳትና ሌሎች ታጋይ ሴቶች ላይ የሚደረገው ግድያ፣ ማሰርና ማባደድ ዘመቻ ጉባኤው በጥብቅ ያወግዛል። ስለሆነም፦

— የታሰሩት የህዝብ ወገን የሆኑ ተራማጅ ሴቶች በአስቸኳይ እንዲፈቱ፣

— ዛሬ ደርግ፣ አድሃሪያትና ቢሮክራሲው በተራማጅ ሴቶች ላይ የሚያደርገውን ግድያ፣ እስራትና ኢሰብአዊ ማሰቃየት አሁኑኑ እንዲቆም፣

— የታሰሩት ሃቀኛ ተራማጅ ሴቶች በአስቸኳይ ተፈተው ትግላቸው እንዲያፋፍሙ፣ ጉባኤው አጥብቆ ይጠይቃል። ለዚህም አብሮ ይታገላል።

— በአሁኑ የኢት ተጨባጭ ሁኔታ የሴቶችን አብዮታዊ ተሳትፎ ከፍ ለማድረግ፣ ሴቶች በበለጠ ለማንቃት፣ ለማደራጀትና ለማስታጠቅ ዲሞክራሲ መብቶች ለጭቁኖች አሁኑኑ እንዲለቀቁ ጉባኤው አጥብቆ ይጠይቃል። ለዚህም እስከ መጨረሻ ድረስ ይታገላል።

<u>ስ ለ ኢ አ ወ ን (የኢት አብዮታዊ ወጣቶች ንቅናቄ)</u>

የኢት ወጣቶች በተለይ ተማሪው የሃይለስላሴን የፊውዶ ቡርዥ መንግሥት ተንከትክቶ እንዲወድቅ ከታገሉት የህዝብ ክፍሎች ውስጥ አንዱ ነው። ይህ ትግል በኢት ህዝቦች የት ግል ታሪክ ውስጥ ህያው ሆኖ ይኖራል። ሆኖም በየካቲት የፈነዳው አብዮታዊ እንቅስቃሴ ከዚያም በኋላ የተካሄዱት የመደብ ትግሎች ወጣቱን እንዳለ ከአብዮቱ ጉን እንዲሰለፍ አላደረጉም። ይህ የአብዮት ሂደት እንደ ጥንቱ ወጣት በጅምላ ተራማጅ እንዲሆን አልፈቀደለትም። ይህም ሊሆን እንደማይችል ከኢት ወጣቶች ታሪክ ብቻ ባይሆን ከሌሎች አገሮችም ተሞክሮ የተረጋገጠ ያለው ሃቅ ነው።





በኢት አብዛኛው የወጣት ክፍል አብዮቱ እንደፈነዳ ሰሞን በኢህአፓ የተሰበሰ የትግል መስመር ሥር ተሰልፎ ብዙ ፀረ-አብዮት የሆኑ እርምጃዎችን በመውሰዱ የአናርኪስቶች መጠቀሚያ ሆኖ ነበር። በወጣቱ ውስጥ በተደረገው መራራ ትግል አሁን ከአብዮቱ የአራት አመት የትግል ሂደት በኋላ (በሙሉም ባይሆን፣ ሊሆንም አይችልም) ብዙ የወጣት ክፍል ወደ አብዮቱ ሠፈር ለመመለስ ተችሏል። በዚህ ትግል ውስጥም ገንበር ቀደም ብሎ የተቋቋመው ኢአወን የተባለው የመኢሶን የወጣት ክንፍ መሆኑ ግልጽ ነው።

በኢት ውስጥ ካሉት የወጣት አብዮታዊ ድርጅቶች ውስጥ ኢአወን ገንበር ቀደም ብሎ የተቋቋመ ድርጅት ነው። ስለሆነም ጉባኤው፦

— የኢአወንን ፕሮግራም አብዮታዊ ይዘት በመመርመር፣

— አብዮቱ ከፈነዳበት ጊዜ ጀምሮ በልሳኑ በአብዮታዊ ሩና ያካሄዳቸውን የቀን ተቀን ትግል በማጤን፣

— እስከ ዛሬ ድረስ በኢት ትግል ውስጥ ከፍተኛ ሚና የተጫወተው የማርክሲስት ሌኒኒስት ድርጅት የመኢሶን የወጣት ክንፍ በመሆኑና ይህንንም የወጣት ድርጅት ከመኢሶን ጋር ነጣጥለን ስለማናየው፣

ይህ ጉባኤ ለዚህ አብዮታዊ ወጣት ድርጅት ሙሉም ያልተቆጠበ ድጋፉን በመስጠት በሚያደርገው ትግልም ከጎኑ መሰለፉን ይገልጻል።

<u>ስ ለ ው ጭ እ ር ዳ ታ</u>

የኢት ጭቁን ህዝቦች አብዮት የዓለም አቀፍ አብዮት አንድ አካል እንደመሆኑ መጠን ከሶሻሊስት አገሮች፣ ከዓለም አቀፍ ዲሞክራቲክና ተራማጅ ሃይሎች የሞራልና የማቴሪያል እርዳታና ድጋፍ ያስፈልጉታል። ሆኖም ይህ ከውጭ የሚገኘው እርዳታና ድጋፍ ሰፊው ህዝብ ለሚያካሄደው ትግል ረዳት እንጂ ወሳኝ መሆን የለበትም። ለአብዮታችን ገብ መታት በተቀዳሚ ደረጃ ሙሉ ቀስትና ሊሆን የሚችለው የኢት ጭቁን ህዝቦች የተባበረ ክንድ፣ የአገር ፍቅር፣ የመፍጠርና የመታገል ችሎታ በተቀዳሚ ሆኖ የውጭ እርዳታን እንደ ረዳት አድርጎ የወሰዱን እንደሆነ ብቻ ነው። የአገራችንን ብሔራዊ ነፃነት ስናስደፍርና አብዮታችንን ስናኮላሽ ከግቡ ለማድረስ የምንችለው ራስ በራስ መተማመን የሚለውን አብዮታዊ መርሆ ተከትለን በሰፊው ህዝብ የመፍጠር ችሎታና ሃይል በተቀዳሚ ተማምነን የውጭ እርዳታን እንደ አጋዥ አድርገን የወሰድን እንደሆነ ብቻ ነው። ነገር ግን ይህንን ባይንበዊና አብዮታዊ መርሆ ረስተን የውጭ ሃይልና እርዳታን እንደተቀዳሚ የሰፊውን ህዝብ የመፍጠር ችሎና ሃይል

እንደ አጋዥ አድርገን የወሰድን እንደሆነ የአገራችንን ብሔራዊ ነፃነትና አብዮታችንን አከሳሸን ማለት ነው፡፡ ዛሬ ደርግ የሰፊውን ህዝብ የመታገልና የመፍጠር ችሎታ እንደ አጋዥ የውጭ እርዳታን እንደ ወሳኝ አድርጎ በመውሰዱ የአገራችንን ብሔራዊ ነፃነትና የአብዮታችንን ህልውና ከፍተኛ አደጋ ላይ ጥሎታል፡፡ ስለሆነም ይህ ጉባኤ ዛሬ የውጭ እርዳታን እንደ ወሳኝ የሰፊውን ህዝብ ትግልና የመፍጠር ችሎታ እንደ አጋዥ አድርጎ ለመውሰድ ደርግና አድርባዮች የሚያደርጉትን ጥረት ያወግዛል፡፡ በጠቃላይ የሰፊውን ህዝብ ታሪካዊ ሚና ዝቅ አድርጎ መመልከትን፣ በአብዮቱ ባለቤት ላይ እምነት ማጣትን፣ የአብዮቱን ባለቤት መፍራትን ወዘተ ንዑስ ከበርቴው መደብ ከአብዮቱ ሠፈር መንሸራተት ነጥለን እንመለከተውም፡፡ ስለሆነም ይህን የአድርባይ መስመር አጥብቆ ይታገላል፡፡

ስ ለ ሱ ማ ሊ

የሱማሌ ገዥ መደብ በ''ታላቋን ሱማሊ''ህልም የመሸፈሩት አለማውን ከግብ ለማድረስ ብዙ ጥረት አድርጓል፡፡ ለብዙ ዓመታት ቀጥሩ የበዛ መሣሪያ ሰብስቧል፡፡ በዚህና በኢምፔሪያሊስቶችና በአድሃሪ የአረብ አገር ገዥዎች አበረታችነት፣ በአብሪተኝነት የአገራችንን ድንበር ጥሶ መግባቱን ተቃውመናል፡፡ የአገራችንን ድንበር የሚጥስን ሁሉ እንቃወማለን፣ ለብሔራዊ ክብራችንና ነፃነታችን እንቆረቆራለን፡፡ አድሃሪው የሸይዱ ባሬ መንግሥት አገራችንንና አብዮታችንን የሚገኝበት አመቺ የጭንቀት ጊዜ መርጦ በአካሄደው ወረራ በዚህ ስፍራ በሚገኙ ጭቁን ህዝቦች ላይ ይህ ነው የማይባል ደም መፍሰስ ማስከተሉ ይታወቃል፡፡ ህዝባዊ ሠራዊቱ ወደዚህ አካባቢ በዘመተበት ወቅት አብዮታዊ አመራር በማጣቱና በቢሮክራሲው አሻጥር ብዙ ገፍና መሸነፍ ደርሶበታል፡፡

ሆኖም ዛሬ የኢት ጭቆኖች ይህ ነው የማይባል መስዋዕትነት በማድረግ የአገራቸውን ዳር ድንበት አስጠብቀዋል፡፡ ጉባኤው ይህን ጊዜያዊ የሆነ ድል አያከብረ በአካባቢው ያለው ችግር አሁንም ቢሆን መፍትሄ ስላላገኘ ለአካባቢው ችግር የሆነው የብሔረሰቦች ጥያቄ አለመፈታት ዋናው መፍትሄ የዲሞክራሲ መብቶች መሰቀቅ ስለሆነ ጉባኤው ለዚህ በጥብቅ ይታገላል፡፡

ለ ሠ ራ ዊ ቱ ጥ ሪ

የኢት ጭቁን ሠራዊት የሰፊው ህዝብ አካል ነው፡፡ ጥቅሙና ስሜቱ ከኢት ጭቆኖች ጋር አብሮ እንደሆነ አለ የማይባል ሀቅ ነው፡፡ መለዮ ለባሹን ያለፈው ሥርአት በክብዘታል፣ አስቃይቶታልም፡፡ ይህንንም ሥርአት ገርስሶ ለመጣል ከሰፊው ጭቁን ህዝብ ጋር ሠራዊቱ በመሰለፍ ይህ ነው የማይባል አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ስለዚህም ሰፊው ሠራዊት፡-





- የብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት ፕሮግራም ከስራ ላይ እንዲውል የሚያደርገውን ትግል እንዲያፋፍም፣
- የአብዮቱ ዋስትና የሆነውን ነፃነት፣ ድርጅትና ትጥቅ በአፋጣኝ ስራ ላይ እንዲያውል፣
- በአድሃሪው የሲቪል ቢሮክራሲና በሚሊቴሪው ቢሮክራሲ ላይ ቆራጥና አብዮታዊ እርምጃ እንዲወስድ የሚደረገውን ትግል እንዲያፋፍም፣
- የታሰሩት የህዝብ ወገኖች ማለትም ጭቁን ገበሬዎች፣ ሃቀኛ አብዮታውያን፣ ወዝ አደሮች፣ ጭቁን ሴቶች ፣አብዮታዊ ወጣቶችና አብዮታዊ መለዮ ለባሾች ላይ የሚደረገው አደናና ገዲያ የመቃወም ትግሉን እንዲያፋፍም ይህ ጉባኤ አብዮታዊ ጥሪውን ለሰፊው ለኢት ጭቁን ሠራዊት ያቀርባል፡፡

ይህን ውሳኔ ያሰለፉት

1— በኖርዌ የኢት ተማሪዎች ማህበር
2— በሬንላንድ የኢት ተማሪዎች ማህበር
3— በስዊድን የኢት ተማሪዎች ማህበር
4— በዴንማርክ የኢት ተማሪዎች የጥናት ክበብ

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር
መጽሔት አዘጋጅ ቦርድ
The Ethiopian Students' Union in Europe
Editorial Board

## ማሳሰቢያ

ውድ አንባቢያችን፤

የወያኔ ገቀና ቁ ከወሰን ሆኖ ቦርቦር ለማጀከም ያደረገው ሙከራ በሳሰ ተካካለት አርሱን ከገቀና ቁያቸን ያገለለው ፀረ ሕዝብ ቡድን ከቀርበ ጊዜ ጀምሮ፤ከአስር ዓመት በላይ በሰራው ሕዝብ ጉን በመሰለና ያለማቋረጥ ያለመታከት ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ ፊውዳሊስት ትግሉ ሲያካሄዱ በኖረው ማህበራችንና በነዚህም አስር ዓመታት ያስተጠጣቸውን ነፃነት በመገጠቁ የሰፊውን ሕዝብ ድምፅና ትግሉ ሲያስተጋቡ በኖረት፤ከየተናወም የተማሪ ማህበራት መጽሔት በላይ የሰፊው ሕዝብ ማስተማሪያና መሳሪያ ሆነው በቆየት በ<u>ታወቅና</u> በ<u>ትግላቸን</u> ስም መጠቀም ደምረዋል። የዚህ ፀረ ሕዝብ ቡድን ዓላማ ማህበራችን እንጊዚህ <u>ታወቅና</u> <u>ትግላችን</u> በአስር ዓመት ቆራጥ ትግሉ ባተረፈት ስም ተጠቅሞ ፀረ ሕዝብ ፖለቲካውን ለመሸፈን ነው።እንጊዚህም ከወሰን ሆኖ ያታለውን የኢትዮጵያ ተማሪያችና ተራማጆች አንድነት የማፍለስ ሙከራ ከወጥ ሆና ወሸገገበር በመገዛት ለማፋፋም ነው።ይህም አንደማይሳካ የተረጋገጠ ነው። ለማገናዘም፤የተለመደው መጽሔት አዘጋጅ ቦርድ አድራሻ/ማለትም P.O.BOX 3198 10364 STOCKHOLM - SWEDEN ያለ ያዘ፤የዓለም ዓቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪያች <u>ማህበር</u> አባለነትን የሚቀበለት ገን የማህበራችን መጽሄቶች ስም የያዙ መጽሄቶች ወዘተ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪያች ማህበር መጽሄቶች አለመሆናቸውን እንገልጻለንና እንዲያስታውቁለን እንጠይቃለን።ለእነዚህ አይነት መጽሄቶች ተጠያቂው ''ዓለም ዓቀፍ ፌዴሬሽን'' በሚባል ስም የታወቀው የነ አስፋወሰን — መንገሻ ሥዩም የወጣቶች ድርጅት ነው።

ከፋፋዮችና አወናባጆች ከፊውዳሊዝምና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ይውደሙ!
የእውነተኛ አብዮታዊያንና ተራማጆች አንድነት ይኑር!
ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው!

በአኢተማ መጽሄት አዘጋጅ ቦርድ